# ክፍል ሁለት

## አብይ ጽኑ እምነቶች

በክፍል ሁለት ታሪኬ ውስጥ በአገልግሎቴ ጅምር ላይ እግዚአብሔር ስለሰጠኝ አራት መሰረታዊ ጽኑ እምነቶች ልነግራችሁ እፈልጋለሁ።

መልካሙን ዜና ለመስማት ወደሚፈልጉት መሄድ እንዳለብንና የሰሙትም እንዲሰወጡ ማስተማር እንደሚገባን እግዚአብሔር በግልጽ ነግሮናል።

*«እንግዲህ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ? ያለ ሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ?» (ሮሜ 10 ÷14)። ምዕራፍ አስር የሚያንፀባርቀው በክርስቶስ ኢየሱስ ስለሚኖረው ጽኑ እምነት ነው።*

ንብ በቀፎ እንደሚሰበሰብ አማኞችም ተሰብስበው ማህበር ይሆናሉ። ለአፍታ እንኳን ስለዚህ ጽኑ እምነት ጥያቄ አልጠይቅም። ሐዋርያው ጴጥሮስ ያየውን እኔም ለማየት እጠብቃለሁ።

*«በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እየተጉ በቤታቸውም እንጀራ እየቆረሱ፣ በደስታና በጥሩ ልብ ምግባቸውን ይመገቡ ነበር፤ እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ በሕዝቡ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው። ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር።»* (የሐዋ. ሥራ 2÷46-47)።

ለረዥም ጊዜያት ከአማኞች ህብረት ጋር መቆየት የእኔ ፍላጐት አልነበረም። ለእነርሱ የሚያገለግላቸውን እና የሚያግዛቸውን አገልጋይ እግዚአብሔር እንዲሰጣቸው እመኛለሁ። በምዕራፍ ስምንት ለመግለጽ የሞከርኩት ጽኑ እምነት ያ ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ የሚያንፀባርቀውን እና የሚለውን አምናለሁ። «እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት፣ ሌሎቹም ነቢያት፣ ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች፣ ሌሎቹም እረኞች እና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ። » ኤፌ. 4÷11-12)።

ሌላው የጽኑ እምነቴ መሰረት ስለ ምዕራፍ ዘጠኝ የሚለው ነው። ይኸውም የትም ቦታ መልካሙን ዜና ለሁሉ ሰው የሚናገረው ነው። እግዚአብሔር የሰጠን ስራ ተፈጽሟል ብዬ ያሰብኩበት ጊዜ አልነበረም።

ወንጌል ባልተሰማበት አካባቢ የሚኖሩ አያሌ ህዝቦች እንዳሉ አውቅ ነበር። እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ ፦ *«እንዲሁም በሌላው ሰው መሠረት ላይ እንዳልሠራ የክርስቶስ ስም በተጠራበት ስፍራ ሳይሆን ወንጌልን ለመስበክ ተጣጣርሁ» (ሮሜ 15፡20)*።



በመጨረሻም ጽኑ እምነትን ከሚካፈሉ ሁሉ ጋር ለመስራት እፈልጋለሁ። ምናልባት የእኔ ትልቁ እና መሰረታዊ ፅኑ እምነት የእግዚአብሔር ቃል መለኮታዊ ችሎታ ያለው መሆኑን ማወቁ ነው። *«የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና፣ የሚሠራም፣ ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው፣ ነፍስንና መንፈስንም፣ ጅማትንና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል፣ የልብንም ስሜት እና አሳብ ይመረምራል።»* (ዕብ. 4÷12)።

የእግዚአብሔርን ቃል በምንሰብክበት ጊዜ በሰዎች ልብ ውስጥ ሳይረሳ የመቆየትና የመለወጥ ኃይል አለው። በቃሉ ውስጥ መለኮታዊ ስልጣን አለውና ሕይወትን ይለውጣል። ይህንን ጽኑ እምነት በምሳሌያዊ ታሪክ ላስረዳ።

## ከአርባ ዓመት በፊት

የረዥም ጊዜ ወዳጄ ኩማሎ ከአንድ ሽማግሌ ሰው ጋር ቆሞ ወንጌልን ያካፍለው ነበር። በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ተከታይ በሆነ ሰው ቀብር ላይ ነበርን፤ እና ኩማሎ የሚያናግረውን ሰው አወቅኩት። እርሱ አላወቀኝም እንዲያውም ወደ እኔ አልተመለከተም።

አንዳንድ ጊዜ ቶሎ አለመታየት ወይም አለመታወቅ የራሱ ጥቅም አለው። ሰውየው ማንነቴን ባለማወቁ በጣም ተጽናናሁ። «ሞት ወደሁላችን ይመጣል፣ ማናችንም ማምለጥ አንችልም። ኢየሱስ ግን በሞት ሊነካ የማይችለውን ሕይወት ሊሰጠን ይችላል።» ነገር ግን ከልባቸው አያውቁትም። በዚህ አትስማማም? አልኩ። ኩማሎ የሚያነጋግረው ሰውዬ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አባል ነበር እና የመጽሐፍ ቅዱስ መልዕክት ለእርሱ እንግዳ አልነበረም። ሰውዬውም ለኩማሎ መልሶ ይህ የሚያስደስት ነው ከአርባ ዓመት በፊት አስታውሳለሁ አለው። እኔም የውይይታቸው ተሳታፊ ሆንኩኝ። ልክ እንደ ትላንትናው ሆኖ በግልጽ ይታወሰኛል።

በጣም ጠዋት ስሰብክት ከቤት በወጣሁ ጊዜ ነበር በመንገድ ላይ ይህን ሰውዬ የተገናኘሁት። «በእጅህ ያለው ምንድን ነው?» ብሎ ጠየቀኝ፣ የእግዚአብሔር ቃል የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ነው አልኩት። ቀጠልኩ እና ይህን ታሪክ ለሁሉም ሰው እናገር ዘንድ እግዚአብሔር ነግሮኛል አልኩት። የት ነው የተማርከው? ስለ እግዚአብሔርስ ቃል ምን ታውቃለህ ብሎ በቁጣ ጠየቀኝ።

የአማርኛን ፊደል ማንበብ የሚችሉ ሁሉ ይህ ቃል ምን እንደሚል ማወቅ ይችላሉ። ልጆች እንኳን ሳይቀሩ ሊረዱ ይችላሉ አልኩት። ኃጢአተኛ ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ካላመነ በቀር ወደ ፍርድ እንደሚሄድ ይነግረናል። ነገር

ግን ኢየሱስ ስለ ኃጢአታችን ሞቶልናል። ካመንነውም ከፍርድ እናመልጣለን አልኩት።

የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አባል እንደመሆኑ መጠን ወደ ማሪያም ስለ መፀለይና፣ የፆም ቀናትን ስለ መጠበቅ ሁሉ ጠየቀኝ። ስለዚያ ጉዳይ መነጋገር የእኔ ጉዳይ አይደለም። ስለ እነዚያ ጉዳዮች ለማወቅ ብትፈልግ ቄሶችን ጠይቅ። ለጥያቄህ እነርሱ መልስ ሲኖራቸው ይችላል። እኔ ልነግርህ የምፈልገው ግን ኢየሱስ ብቸኛ አዳኝ ስለመሆኑ ነው አልኩት። እርሱ ስለ ኃጢአታችን ሞቶልናል። በሦስተኛውም ቀን ተነስቷል በእርሱ ብናምን እንድናለን ካላመንነውም አንድንም ብዬ ነገርኩት።

አትኩሮ ሲመለከተኝ ቆየና ልክ ነህ! ልክ ነህ! ብሎኝ መንገዱን ቀጠለ። ያ ከአርባ ዓመት በፊት ነበር። ያ ሰው ከአርባ ዓመት በኋላ ከአጠገቤ ቆሞ ከኩማሎ ጋር እየተነጋገረ ነው። ከአርባ ዓመት በፊት አነጋግሬው የነበርኩ ሰው ስለመሆኔ የሚያውቀው ነገር አልነበረም። ነግሬው የነበረውን እውነት ግን ለማስታወስ ችሏል። ለምን አስታወሰ? ምክንያቱም የነገርኩት የእግዚአብሔር ቃል ስለሆነ ነው። ዳግመኛ ሲነጋገሩ ዝም ብዬ አዳምጣቸው ነበር።

*«አስታውሳለሁ ከአርባ ዓመት በፊት አንድ አጭር ሰው ምናልባት ከወላይታ ይመስለኛል አሁን የምትነግረኝን ተመሳሳይ ቃል ነግሮኝ ነበር። እናንተ እንደምታምኑት በኢየሱስ አላመንኩም ነበር። ነገር ግን ያ ሰው የነገረኝን ቃል አልረሳሁትም። ሁል ጊዜም እያሰላሰልኩ ኖሬያለሁ።»*አለው።

ያ ማለት ለእኔ ከግማሽ ምዕተ ዓመት በኋላ እግዚአብሔር የሰጠኝ የጽኑ እምነቴ ጠንካራ ማረጋገጫ ነበረ ማለት ነው።

የእግዚአብሔር ቃል አይበሰብስም፣ ወይም በነቀዝ አይበላም፣ ወይም አይለወጥም ፣በተዘራበት ይቆያል ፡- ሕዝብም ይሰራበት ዘንድ ብዙ አጋጣሚዎችን ይሰጣል። ይህ በእርግጥ እግዚአብሔር በኢሳይያስ 55፥10-11 የተናገረው ነው።

«ዝናብና በረዶ ከሰማይ እንደሚወርድ፣ ምድርን እንደሚያረካት፣ ታበቅል እና ታፈራም ዘንድ እንደሚያደርጋት ፣ ዘርንም ለሚዘራ እንጀራንም ለሚበላ እንደሚሰጥ እንዲሁ ወደ ሰማይ እንደማይመለስ፣ ከአፌ የሚወጣ ቃሌ እንዲሁ ይሆናል»፤ የምሻውንም ያደርጋል። የላክሁትንም ይፈጽማል እንጂ ወደ እኔ በከንቱ አይመለስም።»

ስለ እግዚአብሔር ቃል ያለኝ ጽኑ እምነት ወጣት በነበርኩ ጊዜ ውድ ንብረቴን ሽጬ በሌላ ቋንቋ የተጻፈውን መጽሐፍ ቅዱስ እንድገዛ እና ለማንበብ እንድማር አድርጉኛል።



# ምዕራፍ ስድስት

## የመጀመሪያ ስብከቴ በአርኬ መንደር

በወላይታ አንድ ወር ቆይቼ ስመለስ ቦኮ እና ቤተሰቡ በጣም ደስ አላቸው። በተለይም ከወር በኋላ ባለቤቴ እንደምትመጣ ሲሰሙ ተደሰቱ። በወላይታ ያሉት ሰዎች ወደ ሲዳማ እንዳልመለስ ተስፋ ሲያስቆርጡኝ ሞክረው እንደነበርም ነገርኳቸው። ብዙዎቹ እያለቀሱ በወላይታ ሆኜ ወንጌልን እንድሰብክ ሊያሳምኑኝ ሞክረዋል።

ሰቦኮ ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ በወሰነ ጊዜ ያለውን ታሪክ ነገርኩት። ጳውሎስ ለእነዚያ ለሚወዱትና ወደ ኢየሩሳሌምም እንዳይሄድ ላልፈለጉት፦

*እያለቀሳችሁ ልቤንም እየሰበራችሁ ምን ማድረጋችሁ ነው? እኔ ስለ ጌታ ስለ ኢየሱስ ስም በኢየሩሳሌም ለመሞት እንኳ ተሰናድቼአለሁ እንጂ ለእሥራት ብቻ አይደለም" አለ (የሐዋ.ሥራ 21፥13)።*

ወደ ሲዳማ ስመለስ ለሚደርስብኝ ነገር ትኩረት አልሰጥም። ተመልሼ ከቦኮና ከቤተሰቡ ጋር በመሆኔ ደስ ይለኛል። ምክንያቱም እግዚአብሔር የወሰነልኝ ቦታ ይህ እንደሆነ አውቅ ነበር።

## ክርስቶስን መቀበል

ምናልባት ክርስቶስን መቀበል ማለት በዚህ አገባብ ምን ማለት እንደሆነ ብትመለከቱት ትደነቁ ይሆናል። ያንን ጥያቄ ለምን እንደጠየቃችሁ ይገባኛል። እኛ ሁለት ሰዎች ከወላይታ የመጣን ለሲዳማ ቋንቋና ባህል ፍፁም እንግዶች ነበርን።

ለራሳችሁም በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሰው ምን ተረድቶ ነው በኢየሱስ የሚያምነው? ካላችሁ እደነቃለሁ። እንዴትስ እንዲገባን እናደርጋለን? መላው ቤተሰብስ እንዴት ለወንጌል ትርጉም ያለውን መልስ ይሰጣል?

እነዚህ ነገሮች ሁሉ በቀላሉ ሲከሰቱ ስናይ በእርግጥ ወንጌልን መስበክ የእግዚአብሔር ሥራ እንደሆነ እንረዳለን። እኛ የእግዚአብሔር መልዕክተኞች ነን፣ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳንም ነበረን "ብርሃንም በጨለማ ውስጥ ይበራል" (ዮሐ. 1፥5)።

በሕይወታቸው ውስጥ የሚሠራው የእርሱ ቃል ነው። የሕዝቡን ሕይወት የሚለውጠው መንፈስ ቅዱስ ነው። ሰይጣን ግን ሰዎች በጨለማ ውስጥ ብቻ እንዲኖሩ ጥረት ያደርጋል። «የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን አሳብ አሰወረ» (2ጢሞ. 4፥4)። እግዚአብሔር ግን ብርሃንን ለማምጣት የወንጌልን

መልዕክት ይጠቀማል:: «የቃልህ ፍቺ ያበራል» (መዝ. 119÷130) የሚሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃሎች ለእኛ የተሰጡ መመሪያዎች መሆናቸውን እንገነዘባለን::

## ስብከት

እግዚአብሔር ወደ ለሚናዊ ሲዳማ የጠራኝ መልካሙን ዜና እንድሰብክ ነው:: ከወላይታ ተመልሼ በተቻለኝ መጠን ረዥም ጊዜዬን እያገለገልኩ ለማሳለፍ የፈለግኩትም ስለዚህ ነበር::

በእኔ ልምምድ ስብከትና ፀሎት የማይለያዩ ናቸው:: በምሰብክበት ጊዜ ለሕዝቡ እግዚአብሔር ያለውን እነግራለሁ:: በምንፀልይበት ጊዜ እግዚአብሔር በሰዎች ሕይወት ውስጥ ምን እያደረገ እንዳለ ከእርሱ ጋር እንነጋገራለን:: ስለ ሁሉም ነገር እንፀልያለን ለሁሉም ሰው ወንጌልን እንሰብካለን::

የትም ቦታ ስንሄድና ከማንም ጋር ስንነጋገር እንድ የጋራ ስሜት ያዘለ «ፍርሃት» ነበር:: ስንሰብክም ሆነ ስንፀልይ እንድ መልዕክት ነበረን:: ለሕዝቡ ቃል ኪዳን የምንነባው በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ከፍርሃት ነፃ ሊሆኑ እንደሚችሉ በማረጋገጥ ነው:: በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ እንደምናነበው፣ ምልክቶችና ድንቆችም ተመሳሳይነት ያላቸውና በሲዳማም በጋራ የሚታዩ ነበሩ::

እየሰበክን በምንፀልይበት ጊዜ እግዚአብሔር ኃይሉን በግልጽ እያሳየ ሕዝቡን ከመንፈሳዊ፣ ከሥጋዊና ከሥነ ልቦናዊ እሥራት ይፈታቸው ነበር:: ከሌሎች ከተለያዩ ማሰትም ከምጣኔ ሀብት፣ ከባህላዊ፣ ከሃይማኖታዊና ማህበራዊ እሥራቶች ተፈትተዋል:: የተለወጡ ግለሰቦች የተለወጡ ቤተሰቦችን ይፈጥራሉ:: የተለወጡ ቤተሰቦችም የተለወጡ ህብረተሰቦችን ይፈጥራሉ::

## ተወዳጅ መልዕክት

በየቦታው እየሰበክሁ በምንቀሳቀስበት ጊዜ (ዮሐ. 3÷14-16) ተወዳጅ ምንባቤ ነበር::

> *«ሙሴም በምድረ በዳ እባብን እንደሰቀለ እንዲሁ፣ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ይሰቀል ዘንድ ይገባዋል:: በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና::»*

በተቻለኝ መጠን ብዙ ጊዜ እየዞርኩ እሰብካለሁ:: ስብከት አስቀድማለሁ፣ ስለ ቤቴና ስለ እርሻዬ የማስበው በሁለተኛ ደረጃ ነው:: እስከ ሁለተኛው ወር



ማንም በኢየሱስ ክርስቶስ አላመነም:: እኔ ዘሩን ዝም ብዬ እየዘራሁ እቆያለሁ:: አንድ ቀን ግን እንደሚጫድ አውቅ ነበር:: ይህም ማለት በለዎች ልብ የዘራሁት የቃሉ ዘር ጊዜውን ጠብቆ እንደሚበቅልና ፍሬ እንደሚያፈራ አልጠራጠርም::

## የመጀመሪያ ቤተሰብ

ቦኮ እና ቤተሰቡ ከቤተሰቦቻቸው ሲወርድ ሲዋረድ ከመጣው ሃይማኖት ለመላቀቅና ክርስቶስን ለመከተል ያደረጉት ውሳኔ ከመጀመሪያ ጀምሮ ግልጽና ቁርጥ ያለ ነበር:: ክርስቲያኖች በመሆናቸው ምንም የሚለማቸው ፍርሃት አልነበረም::

የቦኮ የቅርብ ዘመዶቹና ጎረቤቶቹ ሁሉ ይቀልዱበት ነበር::

*«እነዚህ ወንጌላውያን በቤትህ እንዲቆዩ የፈቀድከው ለምንድን ነው? ከዚህ በፊት እንደዚህ ዓይነቶቹን ሰዎች ለይተን አይተን ነበር:: እነዚህ የወላይታ ሰባኪዎች እንስትህን ሊፈጁብህ ነው የመጡት:: በልተው ከጠገቡ በኋላ ወደመጡበት ወደ ወላይታ ይመለሳሉ፣ አንተ ግን ብቻህን ትቀራለህ»* ይሉት ነበር:: እብዛኛዎቹ የቦኮ ዘመዶችና ወዳጆች ብዙም አይናገሩም:: ነገር ግን «እስቲ እየቆየን እናያቸዋለን» ማለትን ይመርጡ ነበር::

«ይህ ትምህርት መልካም ከሆነ ቦኮ በጤንነቱ ይስነብታል፣ ከብቶቹም አይታመሙበትም፣ በሚነግድበት ጊዜም ያተርፋል:: ነገር ግን ክፉ ነገር ካጋጠመው በኢየሱስ ማመኑ ጥሩ እንዳልሆነ እናውቃለን»ይሉ ነበር:: ቦኮና ቤተሰቡ በክርስቶስ በማመናቸው ከህብረተሰቡ የደረሰባቸው ግልጽ ተቃውሞ አልነበረም:: ጎረቤቶቹም የቦኮ ምርጫ ተቃራኒ ጉዳት ያደርስብናል የሚል ስሜት አልነበራቸውም::

የሲዳማ ሕዝብ ሃይማኖትን እንደ ህብረተሰቡ ሃላፊነት፣ ሳይሆን እንደ ቤተሰብ ጉዳይ ያይ ነበር:: ስለዚህ የቦኮ ምርጫ ህብረተሰቡን የሚጎዳ ነው ተብሎ አይገመትም::

## የመጀመሪያ ቤት

ከወላይታ እንደተመለስኩ ያቀድኩት የመጀመሪያ ሥራዬ ለእኔና ለባለቤቴ መኖሪያ የሚሆን ትንሽ ቤት መሥራት ነበር:: ከዚያም በኋላ ቦኮና እኔ ሌላ ትንሽ ቤት ማለትም የመጀመሪያ ፀሎት ቤታችን የሚሆን በቤታችን አጠገብ ለመሥራት ወሰንን::

እርኬ ከሌላው ቦታ የተለየ ነው፣ ምክንያቱም ለቦኮና ለቤተሰቡ እሁድ እሁድ ለማምለክ የሚሄዱበት ቦታ እልነበራቸውም:: ለአያሌ ወራት እራታችን

በየሳምንቱ ሐሙስና እሁድ እንሰበሰብ ነበር፣ ነገር ግን ተሰብስበን ለመፀለይ፣ ለመዘመርና ስመስበክ የተለየ ቦታ ነበረን::

ያንን ቤተክርስቲያን « አላቦ አርኬ ቤተክርስቲያን » ብለን ሰየምን:: በሲዳማም ሆነ በወላይታ የቤተክርስቲያን ስም የሚሰየመው በመልክአ ምድር ወይም አካባቢ ስም ነው፣ ሌላ ስም አይሰጠውም::

አላቦ አርኬ በሰሜናዊ ሲዳማ ከተቋቋሙት ቤተክርስቲያኖች የመጀመሪያው ነበር:: በአካባቢው ተበታትኖ በተለይም በምሥራቅና ሰሜናዊ ደቡብ መንገድ አጠገብ ሁለት ትናንሽ የአማኞች ህብረት ነበር፦ እርግጠኛ ግን አይደለሁም::

እኛ በሰፈርንበት አካባቢ ጥቂት ክርስቲያኖች ነበሩ፣ ምናልባት ሾንጋ የሚባለው ሰባኪ የነበረበት ቦታ ይሆናል:: እርሱ በአካባቢው ብዙ ይንቀሳቀስ ነበር:: በተጨማሪም በሼሎ የጉጂ አማኞች ነበሩ::

ከወላይታ አንዳንድ ወንጌላዊያኖች በደቡባዊ ሲዳማ በአለታ ይሰብኩ ስለነበር ጥቂት ቤተክርስቲያኖች በዚያም አካባቢ ተመሥርተዋል:: የመጀመሪያው የጥምቀት ሥነ-ሥርዓት የተፈጸመው በደቡባዊው ሲዳማ ሲሆን እኔም ወደ ሰሜናዊ ሲዳማ የገባሁበት ወቅት ነበር::

ያ አካባቢ የመጀመሪያው ጥምቀት አገልግሎት በሃይማኖታዊ ድርጅታችን የተከናወነበት ሲሆን ጊዜው 1924 ዓ.ም የገና ዕለት ነበር::

## ክርስቲያኖች መባል ሳይሆን አማኞች መባል

በሲዳማም እንደ ወላይታ በኢየሱስ የምናምን ሁላችንም ክርስቲያኖች ከመባል ይልቅ አማኞች ተብለን እንጠራ ነበር:: አዳዲስ አማኞችንም የምንጠራው በዚያው ስም ነበር:: ይህም ምክንያቱ የክርስትና እምነት በአካባቢው አዲስ ስላልነበረ ነው:: ክርስቲያን የሚለው ቃል በዚያን ጊዜ ሌላ ትርጉም ነበረው:: ይኸውም ሰዎች ከኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ጋር ስላያያዙት ነበር::

የሲዳማ ሕዝብ የምንሰብከውን መልካም ዜና ለመስማት መዘጋጀቱና ወዲያውም አለመቀበሉ የሚያመለክተው ስለ ክርስቶስ ሲወራ ብዙ ጊዜ የሰማ በመሆኑ ነበር:: ነገር ግን የተነገራቸው መንገድ ከህይወታቸው ጋር የተዋሃደ አልነበረም:: በሲዳማ ሕዝብ አዕምሮ ውስጥ ክርስቲያን መሆን ማለት የኦርቶዶክስን ቤተክርስቲያን እምነት ብቻ እንደመከተል ይቆጠር ነበር::

በሲዳማ ስለነበረው ሰጋ ክርስትና እግዚአብሔር ይመስገን ትግላችን ሰረኘርም ጊዜ የሲዳማን ቋንቋ ስማወቅ ያደረግነው ጥረት ነበርና ተሳክቶልናልም::



## የወር ጉባኤ

በሰሜናዊው ሲዳማ አማኞችና ወንጌላውያን በወር አንድ ጊዜ የህብረትና የመጽናናት ጊዜ ነበራቸው:: በህብረት እንፀልያለን እንጽናናለንም:: ስለ ቤተክርስቲያን ጉዳይ የሚደረግ ብዙ ውይይት አልነበረም:: ስለ ሰሜናዊ ሲዳማ ማህበር አጀማመር እንወያይም ነበር::

ቀስ በቀስ ብዙ ቤተክርስቲያኖች እየተተከሉ ሲሄዱ ያ ወርሃዊ ስብሰባ በወላይታም መዋቅር በመዘርጋት ይካሄድ ጀመር:: በኋላም በሰሜናዊና በደቡባዊ ሲዳማ የሚገኘው የቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያን በየወሩ የህብረት ስብሰባ ጀመረ:: የማህበሩ መሪዎች ግን ስለ ሥራቸው የሚወያዩበትን ስብሰባ ያካሂዱ ነበር::

በመጨረሻም ሁላችንም የብሔራዊ ሃይማኖት ማለትም የቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያን አካል የሆነን አገልግሎታችንን ማስፋፋት ጀመርን::

## ቤተ ክርስቲያንን መትከል

በአርኬ ስመጀመሪያዎቹ ጥቂት ወራቶች ስብቻ የምንሰበሰብበት ፀሎት ቤት አልነበረንም:: ሰበክና ስባለቤቱ ቤተክርስቲያን ማለት ምን ማለት እንደሆነ አስተምረናቸዋል:: ጠዋት በቡና ጊዜ እና የማታው እራት ጊዜ የአምልኮ ሰዓቶቻችን ናቸው::

ለተወሰነ ጊዜ እራታችን ብቻ በህብረት እናመልክ ነበር:: ነገር ግን እንደ ቤተክርስቲያን አድርገን ነበር የምናከናውነው:: ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን አስተምሬአቸዋለሁ:: እንዴት እንደሚፀልዩም ተምረዋል:: የሲዳማን ቋንቋ ስለማንችል የምንዘምረው በሦስተኛው ቋንቋችን በአማርኛ ነበር:: በወላይታ የአማርኛ መዝሙሮችን ተምረን ስለነበር እነርሱም በአማርኛ እንዲዘምሩ አስተማርናቸው::

«መጣሁ ወደ መስቀልህ»፣«ወደ አምላክ ልብ የሚያደርስ»፣«መንገዱ ጠባብ ነው»፣«ያ ታላቅ ሐኪም»:: የሚባሉትን መዝሙሮች አስተምሬአቸዋለሁ::

## ዕድገት በአላቦ አርኬ ውስጥ

በአላቦ አርኬ ለአምስት ዓመት ያህል ማለትም ከ1943-1947 ዓ.ም ድረስ ሰብኬአለሁ:: በመጀመሪያዎቹ አምስት ዓመታት ውስጥ ማህበሩ ያሳየው ዕድገት ዝቅ ያለ ነበር::

ያ ለእኔ ሃሳብ አልሆነብኝም:: እኔ ከዘራሁኝ አንድ ቀን ራሴ ወይም ሌሎች ያጭዱታል:: ከአንድ ወይም ከሁለት ዓመት በኋላ ፀሎት ቤታችንን 40 ሰዎች የሚይዝ አድርገን አስፍተን ሠራን:: በኮ የመጀመሪያው አማኝ እንደመሆኑና

የመሬቱም ባለቤት እንደመሆኑ ሁልጊዜ ልዩ የሃላፊነትን ቦታ ይይዛል። የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ወይም እረኞች የሚመረጡበት ጊዜ እስኪደርስ አንድና ሁለት ሰዎችን መርጬ ሃላፊነት እንዲሰማቸው አደርግ ነበር።

በአካባቢው የመጀመሪያዎቹ አማኞች ብዙውን ጊዜ ልዩ ሰዎች እንደሚሆኑ ልምድ አግኝቼአለሁ። ስለ እነርሱ በኋላ እነግራችኋለሁ።

አታሮ ሌላው ክርስቲያን ነበር። ቀጥሎም ተስፋዬ ወየሳና ባጥሶ አማኞች ሆኑ። ሚስቶቻቸውም በኢየሱስ ክርስቶስ አመኑ። ወዲያው ስድስት ቤተሰቦች በአንድ ቤተክርስቲያን መሰብሰብ ጀመሩ። ሰዎች እግዚአብሔርን የሚፈልጉት ብዙውን ጊዜ ህመም ሲያጋጥማቸው ሲሆን፣ ከእነዚህ ቤተሰቦች መካከል በህመም ምክንያት ክርስቶስን የተቀበሉ የሉም። ሁሉም ወንጌልን ሰምተው የተመለሱ ናቸው።

ህብረተሰቡም÷እኛ አዲስ መሆናችንንና ከእነርሱ የተለየ ሕይወት እንደምንኖር ያዩን ነበር። ይህን ለውጥ ያመጣልን ወንጌል ነው። ለሌሎች የምናካፍለውም ይህንኑ ወንጌል እንጂ የግል ኑሮአችንን አይደለም።

«ጻድቅ በእምነት ይኖራል ተብሎ እንደተጻፈ የእግዚአብሔር ጽድቅ ከእምነት ወደ እምነት በእርሱ ይገለጣልና» (ሮሜ 1÷17)። እኛ የእምነት ህብረተሰብ ሆነናል። የእግዚአብሔርን ቃል የተቀበልንና የተቀበልነውንም ቃል ለሌሎች የምንሰብክ ነን።

## ፍርሃትና ነፃነት

እንደ በኮ ያሉ ሰዎች የወሰዱትን ውሳኔ በቀላሉ ለመረዳት ሁለት ቃሎችን ማለትም «ፍርሃትና ነፃነት» የሚለውን ማሰብ ያስፈልጋል።

በሰሜናዊ ሲዳማ ሰዎች በፍርሃት ውስጥ ይኖሩ ነበር። ያም የተለየ ፍርሃት የሰዎችን ሕይወት በሰሜታዊ እሥራት የሚጨምር ነው። በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ለእያንዳንዱ ሰው ከፍርሃት ነፃ መሆን እንደሚቻል ቃል ኪዳን እንገባላቸው ጀመር። ፍርሃትና ነፃነት በህይወታቸው የተሰማመዱት ነበር።

ሰዎች ከፍርሃታቸው ነፃ የሚወጡት ክርስቶስ የሚሰጠውን ነፃነት ለመቀበል ሲዘጋጁ ነው። ፈጣሪያችን ሩቅ አለመሆኑን ነግረናቸዋል። የሰላምና የደስታ ሕይወት እንዲያገኙ መንገድ ያበጀላቸዋል። እርሱ የመቀበልንና ያለመቀበልን ምርጫ በየጉኑ አስቀምጧል።

ሰዎች ክርስቶስን እንዲቀበሉ እንጋብዛቸዋለን፣ ይህንን ለማድረግም ሰይጣንን መካድ ይገባቸዋል። ከቋንቋ ችግራችን የተነሳ ስብከታችን ቀለል ያለ ነበር። ነገር ግን ቀለል ያለው መልካሙ ዜና መንፈስ ቅዱስ ተጠቅሞበት



የሕዝብን ሕይወት ይለውጥ ነበር። ይህም ሰዎች የአንድን ነገር መረጃ ለሌላው እንደማድረግ አይደለም። ከእውነት የሚርቅ ምንም የለም። በፍርሃት ውስጥም ሲኖር የሚፈልግ አልነበረም። ሕዝቡ ነፃነትን ይፈልጋል። እኛም ቃል እንገባላቸው የነበረው ያንን ነፃነት እንዲያገኙ ነው። ምናልባት የዚህን ዓይነት ስብከት የድንገት ግንኙነት ብለን ለመሰየም እንችላለን ካልን መልካም!! ለዚህ ኃይል ስሜት የሚቀሰቅስ ድንገተኛ ነገር ከሚያምኑትም ሆነ ከማያምኑት አልነበረም።

## ሕይወት በሲዳማ

ሩቅ መንገድ ለመጓዝ በሲዳማ በቅሎ የነበራቸው ሰዎች ጥቂቶች ነበሩ። ከእኔም ጭምር ብዙ ሰዎች ወደፈለግንበት በእግራችን እንሄድ ነበር። ሁሉም፣ ሰው በእግር ይጓዛል፣ የቦታ ርቀት ምንም አያሳስበንም።

ብዙ የጉልበት ሥራ የሚፈለገው በአዲስ መኖሪያ አካባቢ ነው። ለም መሬት ለማግኘት ከባድ ነበር። ምክንያቱም እኔ ስሌሎቹ የጉልበት ሥራ ስለማላግዛቸው እንዲያግዙኝ ለመጠየቅ አልቻልኩም። በተጨማሪም የእርሻን ሥራ ስሚያግዙ ቡድኖች ጠላ ተጠምቆ ስለሚጋበዙና ክርስቲያኖች ግን ስለማይጠጡ ሌሎችንም ጠላ ስለማይጋብዙ እርሻችንን ስናርስ ሊያግዙን ፈቃደኛ አይሆኑልንም።

ቀስ በቀስ ግን እኔ በቆሎና ሌላም የእህል ዓይነቶች መዝራት ችዬ ነበር። በየቀኑ ከገበያ ሰቤት የሚያስፈልጉንን ጥቃቅን ነገሮች ለመግዛት ገንዘብ ያስፈልገናል። ለምሳሌ ጨው፣ ስኳር የመሳሰሉት ማለት ነው።

የጳውሎስ እናት በሚያስደንቅ ሁኔታ ሁልጊዜ የቀን ወጪያችንን በመሸፈን ታግዘኛለች። ከገበያ ጥጥ እየገዛችና እየፈተለች ቡልኮ፣ ቀሚስና ነጠላ ለሚሠሩ ሸማኔዎች ትሸጣለች። ደግሞም እንጀራና ወጥ እያዘጋጀች በየቀኑ በሚውለው ገበያ ትሸጣለች።

በሲዳማ እንሰት ዋና ምግብ ነው። እንሰት ለምግብነት ከመድረሉ በፊት ለማደግ ብዙ ዓመት ይፈጃል። ስለዚህ ለመጀመሪያዎቹ ጥቂት ዓመታት እንሰትን ከሲዳማ ሰዎች በገንዘባችን እንገዛ ነበር። በመጀመሪያዎቹ ሁለት ዓመቶች የጳውሎስ እናት በህብረተሰቡ መካከል በጣም ችግር ነበረባት። በምግብ አሠራር በጣም ባለሙያ ስለሆነች የምትሠራው ምግብ በገበያ በጣም ይፈለግ ነበር። ስለዚህ መናኛ ምግብ የሚሸጡ ሴቶች የእርሷ ምግብ እንዳይሸጥ ለመከልከል ይሞክሩ ነበር።

የራሳቸውን ምግብ ሸጠው እስኪያጠናቅቁ ድረስ የእርሷን እንዳትሸጥ ያቆሙባት ጊዜም ነበር። ይህም ሁኔታ በገበያ ረዥም ጊዜ እንድትቆይ ወይም ምግቧን ሸጣ እስክትጨርስ እንድትዘገይ ያደርጋት ነበር።

ወደ ሲዳማ እንደደረስን መግዛት የነበረብን የመጀመሪያው ነገር የወተት ላም ነው:: በወላይታ ወተት ሁልጊዜ ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠው ስለሆነ ላም ያስፈልገናል:: ከብቶቻችንን እግዚአብሔር ጠብቆልን ስለነበረ ለአያሌ ዓመታት ወተት እየጠጣንና ጥጆቻቸውን እየሸጥን በቀላሉ የማይገመት የገንዘብ ገቢ አግኝተናል::

ከአምስት ዓመት በኋላ ወደ ሌላ ቦታ በተዛወርን ጊዜ እንኳን በአርኪ እናገኝ የነበረውን ጥቅማ ጥቅም አላጣንም:: በመጀመሪያ እንደደረስን የተከልነውን እንስትና ሌላም እህል በቅርብ ለመንከባከብ ችለናል::

## በገንዘብ መረዳት

በአርኪ በነበርንበት በመጀመሪያዎቹ ሁለት ዓመታት ከወላይታ ማህበር ወይም ከዱትና ቤተክርስቲያን ምንም ገንዘብ አልተቀበልኩም:: በሦስተኛው ዓመት ከወላይታ ቤተክርስቲያን በርድ ጥቂት ገንዘብ መቀበል ጀምሬ ነበር:: ስጥቂት ዓመት የእኔም ስም ከወላይታ ድንበር አልፈው በመሄድ ከሚያገለግሉ ወንጌላውያን ጋር ተመዘገበ::

በዚያን ጊዜ በየወሩ አራት ወይም አምስት ብር እቀበል ነበር:: ያም ማለት በቀን አሥር ሰዓት ለሚሠራ ሠራተኛ ከስምንት እስከ አሥር ቀን ድረስ የሚከፈል ሂሳብ ነበር ማለት ነው::

በ1940 አካባቢ ውስጥ ገንዘብ ይዞ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ መዘዋወር ብዙውን ጊዜ አስቸጋሪ ነበር:: አንዳንድ ጊዜ የውጪ ሚስዮናውያን ከሶዶ ወደ ወንዶ ኤስ አይ ኤም ሚስዮናውያን በአዲስ አበባው ዋና ጽ/ቤታቸው በኩል እየላኩ ወደ ወንዶ በሄድኩ ጊዜ እቀበል ነበር:: አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ከወላይታ ወደ ሲዳማ የሚጓዝ ሰው ሲያገኙ ይልኩልኛል:: አንዳንዴ የሚላክልኝ ገንዘብ በጣም ዘግይቶ ከመድረሱ የተነሳ ያለፈውን መቼ እንደተቀበልኩ እዘነጋለሁ::

አንዳንድ ጊዜ የአራትና የአምስት ወር ደሞዜን አጠራቅመው ይልኩልኛል:: የሚልኩልኝን ገንዘብ በጣም አስፈላጊ ስሆኑ ለአንዳንድ ነገሮች እንጠቀምበታለን እንጂ በእነርሱ ተስፋ አድርገን የየቀኑን ወጪያችንን ለመሸፈን አንጠብቅም ነበር::

## የትውልድ ቦታዬ ቤተ ክርስቲያን

ወደ ወላይታ ሐመሱ ሄጄ በሚቀጥለው ሐመስ ተመለስኩኝ:: በእርግጥ የተመለስኩት ከሲዳማ ነጋዴዎች ጋር ነበር:: በወላይታ ቆይታዬ ወደ ቤተክርስቲያኔ ሽማግሌዎች ሄድኩኝና:



*በሰሜናዊ ሲዳማ ሰባኪ ወንጌላዊ እሆን ዘንድ እግዚአብሔር ጠርቶኛል፣ ደዳና እኔ ለአንድ ወር እዚያ ነበርን፣ አንድ ቤተሰብም አምኗል፣ አሁንም ተመልሼ ወደ ሰሜናዊ ሲዳማ መሄዴ ነው::»* አልኳቸው::

ሽማግሌዎቹም «ያ መልካም ዜና ነው፣ በርታ» ብቻ ብለው ሸኙኝ:: ወደ ትምህርት ቤት መሄዴ ነው ያልኩ ነበር የመሰላቸው እና ምንም ሲሰጡኝ አልፈለጉም:: ከእነርሱ ተልኬ እንደሄድኩም ግምት ውስጥ አላስገቡኝም::

«መልካም ጉዞ ይሁንልህ» ብቻ ነበር ያሉኝ:: እኔ ከሄድኩኝ ከአንድ ወር በኋላ የጳውሎስን እናት ወደ ድንቶ ገበያ በመውሰድ እንዲረዷት ጠየቅኳቸው:: ያንን እንደሚያደርጉ ተስማሙልኝ:: እኔም በተቀጣጠርነው ቀን ወደ ድንቶ ገበያ በመምጣት የጳውሎስን እናት ወደ ሲዳማ እንደምወስዳት ነገርኳቸው::

## ከወላይታ መገናኘት

ከወላይታ ውጪ የሚሠሩ ብዙ ወንጌላውያን ሥራቸውን ከእኔ ሥራ ለይተው ይመለከቱታል:: ብዙዎቹ ወንጌላውያን ወደ ሲዳማ የመጡት ተቀማጭነታቸው እዚያው ወላይታ ሆኖ እየተመላለሱና ጥቂት ቆይታ እያደረጉ ለመሥራት ወይም ለማገልገል ነበር::

በወላይታ ቤተሰቦቻቸውና እርሻም ስላላቸው ረዥሙን ጊዜ ቤተሰቦቻቸውንና እርሻቸውን እየተንከባከቡ ያሳልፋሉ:: ለብዙዎቻቸው በወላይታ እርሻ ማለት ዋነኛው የገቢ ምንጫቸው ነበር:: የእኔ እቅድ ግን እንደዚያ አልነበረም::

ከወላይታ ድንበር ውጪ ሄደን ስምንሠራው ሁሉ በየዓመቱ ታላቅ የመጽሐፍ ቅዱስ ጉባኤ ማለትም ኮንፈረንስ ነበረን:: ያ ጊዜ ስፊ የህብረትና የመንፈስ መታደስ ጊዜ ይሆንልን ነበር:: አብዛኛዎቹ ወንጌላውያንና ሚስዮናውያን በየዓመቱ በገና ጊዜ የሚደረገውን ጉባኤ ለመካፈል ወደ ወላይታ ለመመለስ ጥረት ያደርጋሉ:: ያ ወቅት በተጨማሪ ወንጌላውያን ከጉባኤው የሚሰበሰበውን መባ የሚቀበሉበት ጊዜም ነበር::

በአርኪ አምስት ዓመት በሠራሁ ጊዜ ለዓመታዊ ጉባኤ ወይም ኮንፈረንስ ሁለት ወይም ሦስት ጊዜ ሄጄ ነበር:: የእኔ መኖሪያ ሲዳማ ሆኖ ሳለ ከወላይታ ጋር እንደ ሌሎቹ ምንም ትስስር አልነበረኝምና ዳግመኛ ስጉባኤው ስብሰባ አልሄድኩም::

## በሲዳማ መርካት

የጳውሎስ እናትና እኔ በአርኪ በመኖራችን ተደስተናል:: እግዚአብሔር እንድንኖር የፈለገን ቦታ መሆኑን እናውቃለን:: በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ ነገር

እናከናውናለን የሚል ህልም አልነበረንም:: እኛ መልካሙን ዜና ሳልሰሙት ለመስበክ እንፈልጋለን:: ያንን ካደረግን እግዚአብሔር የበኩሉን ለመፈጸም ታማኝ እንደሆነ እናውቃለን::

# ምዕራፍ ሰባት

## ቁጥር አንድ ቤተ ክርስቲያን ተመሠረተች

### የእግዚአብሔር ማረጋገጫ

እግዚአብሔር ሰባኪና ወንጌላዊ እሆን ዘንድ እንደጠራኝ ቅንጣት ያህል ጥርጣሬ አልነበረኝም:: እግዚአብሔር ወደ ሰሜናዊ ሲዳማ ተዛውሬ መልካሙን ዜና (ወንጌልን) እንድሰብክ የመራኝ ስለመሆኑ ፍፁም እርግጠኛ መሆኔን ቀደም ሲል ባለው ክፍል ገልጫለሁ::

ለጥሪውና ለባርኮቱ ከእግዚአብሔር የማያቋርጥ ማረጋገጫ እፈልግ ነበር:: ወደ ኋላዩም ወደፊቱም ለመመልከት በትክክለኛው መንገድ መቆሜን ለማወቅ እወድ ነበር::

እግዚአብሔር በተደጋጋሚ በአዲስ አካባቢ የመጀመሪያዎቹን አማኞች በመስጠት አረጋግጦልኛል:: እነዚያ አማኞች በመሠረቱት ቤተክርስቲያን ልዩ መሪዎች ለመሆንም በቅተዋል:: ሁልጊዜ ወደነዚህ ሰዎች ስመለከት ለእኔ የእግዚአብሔር ስጦታዎች እንደሆኑልኝ እገነዘባለሁ:: የእግዚአብሔርን ቃል በመስበክ የተገኙ ውጤቶች የእኔንም ጅምር ሥራ ቀጥለው የሚጓዙ የእርሱ ማህተሞች ናቸው::

በ1940 አካባቢ እግዚአብሔር በሰሜናዊ ሲዳማ መሪዎችና የቤተክርስቲያን መሥራቾች እንዲሆኑ ስላነሳሳቸው ሰዎች ለመናገር የፈለግኩትም ስለዚህ ነበር::

## የመጀመሪያ አማኞች በአርኬ

በአርኬ ያከናወንነው እያንዳንዱ ሥራ እግዚአብሔር የመጀመሪያ አባሎች አድርጐ ወደ ቤተክርስቲያኑ በጠራቸው ክርስቲያኖች ላይ የተደገፈ ነበር:: በእያንዳንዱ ቦታ የአዲስ ማህበር መሠረት እንዲሆኑ ሰዎችን እንደሚጠራና እንደሚያዘጋጅ ከልምዴ አውቃለሁ:: እነዚያ ሰዎች ቤተክርስቲያንን ለመመሥረት ያልተዘጋጁ ከሆኑ ምንም እንኳ ወንጌላዊው ጠንክሮ ቢሰራ ቤተክርስቲያን ልትመሠረት አትችልም::



የመጀመሪያዎቹ አማኞች ለሌሎቹ ምሳሌዎችና ሚና የሚጫወቱ እንዲሁም ለሰዎች መልካሙን ዜና ለማካፈል ጥልቅ ፍቅር ያላቸው ናቸው:: ለመስበክ ጥልቅ ፍቅር ባይኖራቸው ኖሮ አዲስ ማህበር አያድግም ነበር::

በአርኬ ቤተክርስቲያን ልዩ የሆኑትንና ለቤተክርስቲያኗ አምድ ወይም እንደ ምሰሶ የሆኑትን አምስት ሰዎች እግዚአብሔር አስነስቷል:: ለማህበሩም መሠረት ሲሆኑ የሚችሉትን ሰዎች እግዚአብሔር እንደመረጣቸው ሳውቅ በመተማመን አገልግሎቴን እንድቀጥልና ጌታ አምላክ ሥራውን የሚሠሩ መንፈሳዊ መሪዎችን እዚያ እንዲሠሩ ያዘጋጀ መሆኑን እገነዘብ ነበር::

እነዚያ ግለሰቦች ማደግ የሚችል የስብከት ልምምዳቸውን በማህበሩ ያሰራጩ ነበር:: ቤተሰብ ያላቸው ከሚስቶቻቸው ማበረታታትና ትልቅ ጥንካሬ ይመጣላቸው ነበር:: ሚስቶቻቸውም ከበስተጀርባቸው በመቆም በአገልግሎታቸው ብዙ ድጋፍ በማድረግ ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን ሳይቆጥቡ ማህበሩን ይገነባሉ:: ስለእነዚያ ስለ አምስቱ ሰዎች ጥቂት ልንገራችሁ፡-

እነዚህ አምስቱ ሰዎች እግዚአብሔር አምላክ ለአገልግሎቴ ማረጋገጫ አድርጐ የሰጠኝ ውጤቶች ናቸው::

## ቦኮ

በመጀመሪያ በአርኬ በመሠረትኩት ማህበር ውስጥ ቦኮና ባለቤቱ የመጀመሪያ ብቸኛ አማኞች አልነበሩም:: ነገር ግን እነርሱ የእኔና የሲዳማ አማኞች ማረፊያዎቻችንና እንግዳ ተቀባዮች ናቸው:: ለአምስት ዓመት ሙሉ የቅርብ ጐረቤታሞች ነበርን:: እርሱ ለእኔ እንደ ወንድም ሆኖኛል::

እንደምታስታውሱት ለመጀመሪያ ጊዜያችን ወደ ሰሜናዊ ሲዳማ ስንደርስ ያረፍነው በቦኮ ቤት ነበር:: በአገልግሎቴ ዓመታት ሁሉ እንደ እርሱ ረጋ ያለ ሰው አላየሁም:: ከመጀመሪያው ጀምሮ ሕይወቱን ለጌታ የሰጠ ነበር:: ምንም ሳይኖረው ያለውን ሁሉ የሚሰጥ ነው እየተባለ ይነገርለታል:: እግዚአብሔርን ለማገልገል በራሱ መንገድ ወጥቶ ይሄዳል:: በዚያ ስሜቱ እኛንም ይረዳን ነበር:: ከዚህም የተነሳ የጽኑ እምነቱ ተካፋዮች ሆንናል:: በማንኛውም ጊዜ የምንፈልገውን ማንኛውንም ነገር ለማሟላትና አገልግሎታችንም እንዳይስተጓጐል የሚጐድለን ነገር ካለ ለማስተካከል ሙሉ ፍላጐት ነበረው::

በሚቻለው ጊዜ ሁሉ ለስብከት አብሮኝ ይወጣል:: በእርግጥ ሌሎች የቤተሰቡ የግል ሃላፊነቶች አብሮኝ እንዲሄድ ባያስችሉትም ራሱ እንደሚቻል አድርጐ አብሮኝ ለስብከት በመሄድ ይተባበረኛል:: የእርሱ የሆነ ሁሉ የእኛ እንደሆነ ይቆጥራል::

በሰሜናዊ ሲዳማ ስለነበረው የጥምቀት ሥርዓት ወደ በኋላ አወጋችኋለሁ። ቦኮ በመጀመሪያ ከተጠመቁት ሰዎች አንዱ ነበር። «እኔ መጠመቅ የምችለው መቼ ነው?» ብሎ የጠየቀኝ ለመጀመሪያ ስለ ጥምቀት ባስተማርኩት ጊዜ ነበር። ሌሎች የሚጠመቁ ሰዎች በርከት ብለው ሲኖሩ ለጥምቀት እናመቻቻለን አልኩት። ሰዎች ክርስቶስን እንደተቀበሉ ወዲያው ማጥመቅ የእኛ ባህል አይደለም። ጊዜው ሲደርስ የቦኮ ባለቤት ተጠመቀች፣ እምነትን በተመለከተ በማንኛውም ነገር ሁልጊዜ ከጐኑ ነች። ሕይወቷን አጠቃልላ ለጌታ የሰጠች ናት።

ቦኮና ባለቤቱ ስድስት ልጆች ነበሯቸው። በዚያን ጊዜ በኢትዮጵያ ብዙ ሕፃናት እንደተወለዱ በመጀመሪያ ጥቂት ወራቶች ውስጥ ይሞቱ ነበር። ስድስቱም ልጆቹ በጤንነት አደጉለትና ተሰባስበው ትልቅ ቤተሰብ ሆኑ።

ቦኮ በአርኬ ቤተክርስቲያን ከነበሩት ሽማግሌዎች አንዱ ነበር። የሚያገለግለውም እንደ ጊዜያዊና እንደ ቋሚ ሽማግሌ ሆኖ ነው። ጊዜያዊ ሽማግሌዎች የተባሉት የመጀመሪያው የጥምቀት ሥነ ሥርዓት ከመፈጸሙ በፊት የተመረጡ ናቸው። እነርሱ ስለ ቤተክርስቲያን፣ ሽማግሌዎች ሃላፊነት የተማሩ ቢሆኑም በማህበሩ የተመረጡ ወይም በሥርዓት የተሾሙ አልነበሩም።

እኛ የወላይታን ቤተክርስቲያን ባህል የተከተልን ስለሆነ በእያንዳንዱ ቤተክርስቲያን አራት ሽማግሌዎችን እንሾማለን። በጥንት ጊዜ በወላይታ ቤተክርስቲያን አንድ ሰው ሽማግሌ ሆኖ ከተመረጠ ለረዥም ጊዜ ይቆይ ነበር። በኋላ ግን ምርጫ ተጀመረና ማህበሩ ራሱ የፈለገውን ሰው ይመርጥ ነበር።

የአርኬ ቤተክርስቲያን ፀሎት ቤት የተሠራው በቦኮ መሬት ላይ ነበር። ቦኮ ለፀሎት ቤት ግንባታ የሚበቃውን መሬት ቆርሶ ሰጥቷል። ስለዚህም የአርኬ ቤተክርስቲያን ለአያሌ ዓመታት በእርሱ መሬት በተሠራው ፀሎት ቤት እየተገለገለበት ቆይቷል። ከብዙ ዓመት ቆይታ በኋላ ማህበሩ ወደ ሌላ ቦታ ለመዛወር ወሰነ።

ቦኮ መደበኛ የሆነ የቀለም ወይም የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አልነበረውም። እኔ እዚያ ከመድረሴ አስቀድሞ አማርኛ ይናገር ነበር። ነገር ግን እኔ ማንበብ ያስተማርኩት ሲሆን፣ የራሱ ባልሆነ ቋንቋ በጥሩ ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ችሏል።

ከእኔ ፊደል ተምሮ በራሱም ጥረት ብዙ ከሞከረ በኋላ ተራ ወስዶ በየሳምንቱ ሐሙስ ቧት በነበረን ስብሰባ መስበክ ጀምሯል። ቀጥሎም በየእሁድ አገልግሎት ይሳተፍ ጀመር። ቦኮ ጥሩ ሰባኪ ነበር። ጥሩ ሰባኪ



የሆነበትም ምክንያት የተናገረውን በተግባር ስለሚያውለው ነው። የእርሱ ስብከት እንደ ማስታወቂያ እንዳልሆነ ሕዝቡ ያውቅ ነበር።

ከተማሪዎቼ አንዱ ከሆነው ስብከቱን ስለማ በጣም ረክቻለሁ። በማህበሩ መካከል ተግቶ ሲሠራ ይታያል። በተጨማሪም ከማህበሩ ውጪ ይሄድና ከሚጠበቀው በላይ ሠርቶ ይመለሳል። ወርሃዊው አጠቃላይ የማህበራት ስብሰባ ተራችን ሲደርስ የማስተናገድ ግዴታው የእኛ ይሆን ነበር።

ይህም ማለት ለስብሰባው የሚመጣውን እያንዳንዱን ሰው አራት ጊዜ እንመግባለን። ገና እንደመጡ መቆያ፣ ቀጥሎም ማታ እራት፣ በማግሥቱ ጧት ቁርስ እና በምሳ ሰዓት ምሳ መግበን ወደየቤታቸው እንሸኛቸዋለን።

ለአርኬ ዓይነቷ ትንሿ ማህበር ብዙ ሕዝብ ተቀብሎ ማስተናገዱ በጣም ከባድ ሥራ ነበር። ሰበቂ ምግብ አቅርቦት ከፍተኛ ገንዘብ ወጪ ማድረግም ቀላል አልነበረም። ማህበሩን ለማስተናገድ ተራችን ከመድረሱ ብዙ ወራት አስቀድሞ ቦኮ ከሚኖርበት ወደ ሰሜን አቅጣጫ ርቆ በእግር የአራት ሰዓት መንገድ በሚያስኬድ ቦታ ላይ ትንሽ መሬት ተከራይቶ ነበር። ያ ቦታ በቆሎ ለማምረት የተሻለ ቦታ ነው። በዚያን ዘመን በሬ ለመግዛት በጣም ውድ ስለነበር የሲዳማ ሰዎች በበሬ አያርሱም ነበር።

ነገር ግን የሾለ ብረት አዘጋጅተው በእጆቻቸው ለምለሙን ሣር በመንቀል ያርሳሉ። ቦኮም መሬቱን አርሶ በቆሎ ዘራበት። በቆሎውም ሲደርስ በመፈልፈል በጆንያ ካዘጋጀ በኋላ በትከሻው ተሸክሞ የእህል ወፍጮ ወደነበረበት ወደ ይርጋለም ወስዶ አስፈጨ፤ ዱቄቱንም ለክርስቲያኖቹ መስተንግዶ ምግብ ለማዘጋጀት እንድንጠቀም ይሰጠን ነበር። ቦኮ ካለ ሁሉንም መሥራት አይገደውም ማህበሩ እየሰፋ ሲሄድ ጥቂት ሰዎች የማህበሩ ሽማግሌዎች ሆነው ተመርጠው ነበር።

ቦኮ ግን በሽምግልና ከእነርሱ ጋር ሊሠራ አልፈለገም። ነገር ግን ጊዜውንና ጉልበቱን ለማህበሩ አገልግሎት በደስታ ያውል ነበር። በሕይወቱ ዘመን ሁሉ በትጋት ጌታን ሲያገለግል ቆይቷል። በኋላም ታመመና ሳያረጅ ሞተ። ለእኔ ቦኮ እውነተኛ ወዳጄና የቤተክርስቲያን ታላቅ ወንድም ነበር። ሲሞት ግን አጣሁት።

## ቆሬቶ

ቆሬቶ በአርኬ ከመጀመሪያ አማኞች አንዱ ነበር። በክርስቶስ ባመነም ጊዜ በዕድሜው ወጣት ነበር። ወጣትነቱ ግን ጠንካራ እምነቱን እልቀነሰበትም። እግዚአብሔር የሰዎችን ሕይወት ለመለወጥ ምን እንደሚሠራ ያውቃል የሚል ጽኑ እምነት አለኝ። ወጣቶች ወይም ሽማግሌዎች ማንም ቢሆን በቤታ ነገር መወሰኑ የእኔ ጉዳይ አይደለም። ቆሬቶ ወጣት ቢሆንም እንኳን በቤተሰቡ

ውስጥ የመጀመሪያ አማኝ ነበር። የቤተሰቦቹን ስሜት እንደገመትነው ይሞታል ብለው ያስቱ ነበር፣ ሆኖም ግን አላሳደዱትም ወይም አላገለሉትም። የሚደርስበትን ነገር በዝምታ ይጠባበቁ ነበር። እርሱ ግን እንደፈሩት አልሞተም።

ከብዙ ወራት በኋላ ቤተሰቦቹ በሙሉ ክርስቲያኖች ሆኑ እርሱና ወንድምየው ወየሳ ያመኑት በተመሳሳይ ጊዜ ነበር። በሲዳማ እያንዳንዱ ሰው በፍርሃት እንደሚኖር ሁሉ ቆሬቶ እና ቤተሰቡ ሰይጣን ምን ያደርገን ይሆን? በሚል ፍርሃት ውስጥ ይኖሩ ነበር። ለብዙ ጊዜ ስብከቱን ሳያዳምጥ ቆይቶ አንድ ቀን እጆቹን ከፍ አድርጐ ሰይጣንን በመካድ ክርስቶስን ወደ ሕይወቱ ጋበዘ። ወጣት እንደመሆኑ መጠን እንደ በኮ ፈጥኖ ማህበሩን ለማገልገል ተሳትፎ አላደረገም።

በዘመኑ ያላገቡት ወጣቶች በዕድሜያቸው ሲጋነት ምክንያት ካገቡት ሰዎች የተለዩ ናቸው። ቆሬቶም እስኪያገባ ድረስ ቤተክርስቲያንን ወደ ማስተዳደሩ ተግባር ከመግባቱ በፊት መቆየት ነበረበት። ነገር ግን እርሱም እንደ ሌሎቹ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ገዛና ማንበብ ተማረ። በዚህም ምክንያት የክርስትና እምነቱን ለማሳደግና በታማኝነትም የሐሙስንና የእሁድን ስብሰባዎች ለመካፈል በቅቷል። በግሉ የሚያደርገው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትም መሠረታዊውን የክርስትና እምነት እንዲረዳና አጥብቆም እንዲይዝ አስችሎታል።

በአርኬ የመጀመሪያዎቹ አማኞች በተጠመቁ ጊዜ ቆሬቶ ልጅ በመሆኑ ሊጠመቅ አልቻለም ነበር። በኋላ ግን ቆይቶ ተጠመቀና የማህበሩ ታማኝ አባል ሊሆን ችሏል። እንዲሁም ከአርኬ ማህበር ጋር ለብዙ ዓመት ሠርቷል።

እኔና ቤተሰቤ ከአራት ዓመት ቆይታ በኋላ ወደ ዋጮ ስንዛወር የቤተክርስቲያን ሽማግሌ ሆኖ ከ3 ሰዎች ጋር ያገለግል ነበር። ከጥቂት ዓመት ቆይታ በኋላ ቆሬቶ ሌላ ሃይማኖታዊ ድርጅቶች ዘንድ ለመግባት ወሰነ ገባ። ከዚያ በኋላ ከእርሱ ጋር ብዙ ግንኙነት አልነበረንም።

## ባጥሶ

የባጥሶ ቤተሰቦች በአካባቢው ካሉት ሰዎች የበለጠ ሀብታሞች ነበሩ። አባቱ ብዙ ከብቶች ነበሩት። ባጥሶ ወጣት እንደመሆኑ የከብት መንጋውን ወደ ቆላ እየወሰደ ያሰማራ ነበር። እዚያ በቆላ ከብቶቹን በሚጠብቅበት ጊዜ ነበር ወንጌልን የሰማው።

ሾንጋ የሚባል ሌላው የወላይታ ወንጌላዊ በዚያ በቆላማ አካባቢ አንድ ማህበር መሥርቶ ነበር። በቆላማው አምባ መሬት ዙሪያ ከብቶቻቸውን ለሚያሰማሩት ለብዙ ሰዎች ይሰብክ ነበር። ባጥሶም መልካሙን ዜና የሰማው



እዚያው በቆላማው ምድር ቢሆንም ወዲያው አላመነም። እርሱ ያመነው ወደ አርኬ ተመልሶ የቤተክርስቲያንን ስብስባ ከተካፈለ በኋላ ነው።

ባጥሶ በኢየሱስ ክርስቶስ ካመነ በኋላ ለቤተሰቦቹ ቃሉን መናገር ጀመረ። በተለይም አባቱ ከነበሩበት ፍርሃት ነፃ መውጣትና በሰይጣን ስለመጨቆን ሁሉ ተነገራቸው፣ ባጥሶም የራሱን አዲስ ሕይወት በግልጽ በማሳየት መልካም ምሳሌ ሆኗል።

አባቱ ስለሚነገራቸው የእውነት ቃል ምንም አልተደነቁም እንዲያውም በባጥሶ ላይ ጫና ይፈጥሩበት ጀመር። እርምጃቸው ግን ከፍርሃት የመነጨ ነበር። በሲዳማ በክርስቶስ የማያምኑትን ሰዎች ፍርሃት ያስቃያቸው ነበር። የባጥሶ አባት በሚያመልኩት መንገድ መሥዋዕት ካላቀረቡ ልጆቻቸውና ከብቶቻቸው እየታመሙ የሚሞቱባቸው ስለመሰላቸው ፍርሃት ሞላባቸው። ስለዚህም በፍፁም በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ሊያምኑ አልፈለጉም።

ከሰሜናዊ ሲዳማ ወንዶ ሄደው የቀለም ትምህርት ከተማሩት ባጥሶ የመጀመሪያው ነበር። ቤተሰቦቹ ለት/ቤትና ለቀለቡ የሚያስፈልገውን ሁሉ ለማሟላት በቂ ገንዘብ ነበራቸው። በኋላም ቆይተው ከተጠመቁት ሰዎች ጋር ተጠምቋል። መቼ እንደነበር ትክክለኛውን ጊዜ አላስታውስም። የቤተክርስቲያን ሽማግሌ ባይሆንም በማህበሩ ውስጥ ብዙ እገዛ አድርጓል። ትምህርቱን ሲገፋ ከመፈለጉ የተነሳ የሰባተኛው ቀን አክባሪ አድቬንቲስት ቤተ ክርስቲያን የነፃ ትምህርት ዕድል እንደሚሰጡ ያውጁ ስለነበር ባጥሶ ወደ እነርሱ ገባ። ከዚያ በኋላ ግንኙነታችን ተቋርጧል።

## አታሮ

አታሮ ከመጀመሪያዎቹ አማኞች አንዱ የነበረ ሲሆን፣ በክርስቶስ ሲያምን ዕድሜው ትልቅ ነበር፣ ባለትዳርም ነበር።

እንደ በኮ አታሮም ሕይወቱን ሙሉ በሙሉ ለጌታ የሰጠ ሰው ነበር። የእርሱ መሰወጥ እንደ ሌሎቹ ከልብ የመነጨ ነበር። መነሻው ምንድን ነው? ሲባል ከኃጢአት እሥራት የተፈታ መሆኑን በትክክል ስለተገነበበ ነው። በኋላም ስወንጌሉ መልዕክት ልምድ እንዴት ብቁ እንደሆነ ተረድቷል። በዚያን ጊዜ እንደ ሌሎቹ ክርስቲያኖች ፊደል ቆጥሮ ማንበብ በመቻሉ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ገዝቷል። መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ በጣም ይወዳል። ለክርስቲያኖችና ላላመኑትም በጣም ጥሩ አድርጐ ይሰብካል። በጣም ታሞ ይሰቃይ በነበረበት ጊዜ እንኳን ቃሉን እያነበበ ለመጡት ሁሉ ይሰብክ ነበር።

ከረዥም ጊዜ ሕመምና ሥቃይ በኋላ በ1987 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል። አታሮና ባለቤቱ ለአያሌ ዓመታት አብረው ሲኖሩ ልጅ አልነበራቸውም። አንዳንድ ጊዜ እንደዚህ ዓይነት ክስተት እግዚአብሔር

የአዳዲስ አማኞችን ማንነት ለማጣራት የሚያደርገው ይመስለኛል። ታዲያ እየፀለዩንላቸው ኖረን እግዚአብሔር ወንድና ሴት ልጅ ሰጣቸው። ወንዱ ልጅ ግን በእምነቱ የአባቱን ፈለግ አልተከተለም። ዳሩ ግን ራሱ በፈለገው አቅጣጫ ሄዷል። በዚያ ህይወት ውስጥ እንደነበረም ታሞ በወጣትነቱ ሞቷል። ሴቷ ልጅ ግን በሕይወት አለች።

አታሮ ለጊዜያቸውና ለገንዘባቸው ከማይሳሱት ሰዎች አንዱ ነበር። በማንኛ ውም ሥራ ከመተባበር ወደኋላ አይልም፤ ማንኛውንም ያለውን ነገር ሊያካፍለን ፍላጎት ነበረው። አንድ ነገር የፈለግን እንደሆነ ወዲያው ይሰጠናል። እርሱ ያለውን በስጠን ቁጥር የተረፈው ይበረክትለት እንደነበረ ስለምናውቅ የሚሰጠንን እህል ሳንግደረደር እንቀበል ነበር።

አታሮ አብዛኛውን ጊዜውን የሚያጠፋው በማህበሩ አገልግሎት ላይ ነበር። የሚሠራው ነገር በሚኖርበት ጊዜ ወዲያው ከተፍ ብሎ ከምንጠብቀው በላይ የሚሠራ ትጉህ ሰው ነበር።

# ወየሳ

ወየሳም በክርስቶስ ባመነ ጊዜ በዕድሜው በጣም ልጅ የነበረ ሲሆን፤ ነገር ግን ውሳኔው ብስለት የተሞላበት ነበር። ከነበረበት ፍርሃትና የኃጢአት እሥራት ኢየሱስ ነፃ እንደሚያወጣው ያውቅ ነበር። ወየሳ ከፍርሃትና ከኃጢአት እንዴት እንደሚያመልጥ ማወቁ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም እንዴት ማምለጥ እንደሚችሉ ለመንገር ይፈልግ ነበር።

በኢየሱስ ክርስቶስ ካመነበት ጊዜ ጀምሮ መስበክ የጀመረ ከመሆኑም በላይ ብዙም ሳይቆይ ጋብቻውን በመፈጸሙ ደስ ብሎኛል። ያ ማለት ሌላ ኃላፊነት የሚሰማው ባለትዳር ሰው በማህበራችን ተጨመረልን ማለት ነው። ስለዚህም ወየሳ ከማህበሩ መሪዎች አንዱ እንዲሆን አጋጣሚ ሁኔታ ፈጥሮለታል።

በአርኬ የመጀመሪያዎቹ ምዕመናን በተጠመቁ ጊዜ ወየሳ በዕድሜው ልጅ ስለነበረ ለመጠመቅ አልቻለም። በሕይወታቸው ስውጥ ካላሳዩ በስተቀር ሌሎቹን ላለማጥመቅ ጥንቃቄ እናደርጋለን።

ማንም ሰው በማንኛውም ጊዜ አማርኛ ማንበብ ቢፈልግ በቤተክርስቲያን ውስጥ ፊደል የማስተማር ክፍለ ጊዜ ነበረን። እርሱንም ማንበብ ካስተማርኩት በኋላ እንደ ሌሎቹ አዳዲስ አማኞች መጽሐፍ ቅዱስ ገዝቶ ለራሱ ማንበብ ጀመረ። ወዲያውም መልካሙን ዜና ለጎረቤቶቹ ከመስበኩም በላይ በየሳምንቱ ሐሙስና እሁድ ተራ እየወሰደ ያስተምር ነበር።

ወየሳ በወንዶ ኤስ አይ ኤም የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ከተከታተሉት የመጀመሪያዎቹ አማኞች አንዱ ነበር። የእርሱ ዋነኛው ብቃት የቀሰም



ትምህርት መማሩና የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ማግኘቱ፤ አንብቦም ፍሬ ሃሳቡን በግልጽ መረዳቱ ነው።

በተጨማሪም መልካሙን ዜና በይበልጥ ለሰዎች ለመስበክ የጋለ ምኞት አድሮበታል። እኔ ወደ ዋጮ በሄድኩኝ ጊዜ ወየሳ በአርኬ ቤተክርስቲያን ከአራቱ ሽማግሌዎች አንዱ ሆኖ ያገለግል ነበር። ጊዜውንና ጉልበቱን ለሚወደው ጌታ የሰጠ ሰው ሲሆን፤ ለተወሰኑ ዓመታት ወንጌላዊ ሆኖ በሲዳማ በተለያዩ ቦታዎችም ሠርቷል።

ወየሳ ወንጌልን ላልሰሙት እንዲያሰማና አዲስ ያመኑትንም ያበረታታ ዘንድ እግዚአብሔር ተጠቀሞበታል። በእምነቱ እንደ ዓለት ጠንካራ ነበር፤ ሁልጊዜም ከሚሰጠው የአገልግሎት ድርሻ በላይ ተግቶ ለመሥራት ይፈልጋል።

# ለመዛወር ጊዜ ደረሰ

እንደ ሰባኪና ወንጌላዊ በአርኬ እስከ 1947 ዓ.ም ድረስ ከሠራሁ በኋላ ወደ ዋጮ ተዛወርኩ። ወደዚያ ለመዛወር ያነሳሱኝ ሦስት ምክንያቶች ናቸው። የመጀመሪያው ምክንያት ስአዳዲስ አማኞች ጥቅም ስል ሲሆን፤ እኔ ከሄድኩኝና ብቻቸውን ከተውኳቸው የበለጠ ፈጥነው በመንፈሳዊነታቸው ብስለት ያገኛሉ ብዬ ስለማምን ነው። ዳሩ ግን ሙሉ በሙሉ አልተውኳቸውም። ሁልጊዜ እየሄድኩ ብጐበኛቸውም የአርኬን ማህበር በሃላፊነት አላገለግልም።

ስብከቴን በማከናወን የበለጠ ውጤታማ ለመሆን ከቦታ ወደ ቦታ መንቀሳቀስ ይገባኛል። እግዚአብሔር ወንጌላዊ እንድሆን የጠራኝ ስለሆነ ወንጌልን ላልሰሙት ሁሉ ሳላቋርጥ ለመስበክ እፈልጋለሁ። ይህንን ለማድረግ ዓይነተኛው መንገድ ከቦታ ወደ ቦታ በመዘዋወር ማገልገል ይመስለኛል። በኋላም ለሁሉም አካባቢ መካከለኛ የሆነ ቦታ መረጥኩና እዚያ መሥራቴን ቀጠልኩ።

ከቦታ ወደ ቦታ በመዘዋወር መስበክ የፈለግኩበት ሌላው ምክንያት በአንድ ቦታ የማህበሩ ሽማግሌና እረኛ ለመሆን ስለማልፈልግ ነው። በአንድ ቤተክርስቲያን ብቻ በሃላፊነት ቦታ ከተጠመድኩኝ እግዚአብሔር የሰጠኝን የአገልግሎት መጠን ያሳንስብኛል ወይም የተወሰነ ያደርግብኛል።

ከአርኬ ወደ ዋጮ በተዛወርኩኝ ጊዜ ማህበሩን ትቼ የሄድኩት በአራቱ የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች እጅ ነበር። እነርሱም ቦኮ፤ ቆሬቶ፤ ወየሳና አታሮ ነበሩ። በዚያን ጊዜ «እረኛ» የሚለውን ቃል አንጠቀምም ነበር። ማንኛ ውም ማህበር አንድን ሰው እረኛ ብሎ አይጠራም። እንደ እውነቱ ከሆነ

እነዚያ አራቱ አስተማሪ ሽማግሌዎች እረኞች ነበሩ፡፡ እናም ያስተደድራሉ፣ ያስተምራሉ፣ እንደ እረኛም ማህበሩን እያበረታቱ ቃሉን እየመገቡ ያሳድጋሉ፡፡

## በሰሜናዊ ሲዳማ የመጀመሪያ ጥምቀት ሥነ ሥርዓት

ሁልጊዜ በአዲስ አካባቢ የመጀመሪያ የጥምቀት ሥርዓት ሲከናወን ትልቅ ክስተት ይሆናል፡፡ ያም ማለት ብዙ ሰዎች የወረዳው ማህበራት አባሎች መሆናቸው የሚታወቅበት ነው፡፡

ከወላይታ ይዘን ካመጣናቸው ባህሎች አንዱ የጌታ እራትን /ቅዱስ ቁርባንን/ በህብረት መካፈል ነው፡፡ ይህም ማለት የጌታን እራት መካፈል የሚችሉት አምነው የተጠመቁት ብቻ ናቸው፡፡ በእኛ ልምድ ጥምቀት ለአምልኮት ከሚመጡት ምዕመናንና የቤተክርስቲያን አባሎች መካከል ያለው ልዩነት ሲሆን ያም ተለይቶ መታወቅ ያለበትና በጣም አስፈላጊ የሆነ ነገር ነው፡፡

ወደ አርኬ የደረስኩት በ1942 ዓ.ም ቢሆንም በአካባቢው እስከ 1944 ዓ.ም ድረስ የጥምቀት ሥነሥርዓት አልተፈጸመም ነበር፡፡ ሌላው ከወላይታ ያመጣነው ባህል የማህበር አስፈላጊነትን ነው፡፡ የአካባቢው ማህበራት አስፈላጊዎች ቢሆኑም እንደ ትልልቅ ማህበራት የሚታዩ አይደሉም፡፡ በወላይታ የአንድ ቦታ ማህበር ጥምቀትን አልተለማመድንም፡፡ ስለዚህም በአርኬ ቤተክርስቲያን የነበሩት ጥቂት ሰዎች ብቻ ይጠመቁ የሚል ሃሳብ አልነበረንም፡፡ ጥምቀት የሚከናወነው ከብዙ ማህበራት ጋር በአንድነት ነው፡፡ በነጠላ የሚከናወነው ጥምቀት ለእኛ እንግዳ እንደሆነ እንረዳለን፡፡ ምክንያቱም ሁሉም ካሉበት ቦታ እየዘመሩ በርከት ብለው ሲመጡ በአካባቢው ላሉት ላላመኑ ሰዎች ምስክርነትም ጥሩ ስለሆነ ነው፡፡

በ1944 ዓ.ም በሰሜናዊ ሲዳማ የሚገኙት ማህበራት የጥምቀት ሥነሥርዓት እንዲከናወን ወሰኑ፡፡ በአርኬ ማህበር ውስጥ እኔ ሳስተምራቸው የቆዩትና ለመጠመቅ የተዘጋጁ በርካታ ሰዎች ስለነበሩ በጣም ደስ አለኝ፡፡ ጊዜው ሩቅ በመሆኑ ከአርኬ ቤተክርስቲያን ስንት ሰዎች እንደተጠመቁ አላስታውስም፡፡

ሰዎች ካመኑ በኋላ መጠመቅ እንደሚገባቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ እናስተምራቸዋለን፡፡ ያም በህብረተሰቡ መካከል የእግዚአብሔር ቤተሰብ አካል የመሆናቸው ማረጋገጫ ነው፡፡ በተጨማሪም ከተጠመቁት አማኞች ጋር ህብረት ለመፍጠር የበሰጠ ጠቀሜታ ያለው ነው፡፡ በጊዜው በሰሜናዊ ሲዳማ ቢያንስ ሦስት ትናንሽ ማህበራት ነበሩ፡፡ እነርሱም ሂዳ፣ አርኬና ሃዌላ በሚባሉ ቦታዎች የነበሩ ናቸው፡፡ ሌሎችም ሊኖሩ ይችላሉ፣ እርግጠኛ አይደለሁም፡፡



ከወላይታ ያመጣነው ሌላው ባህላችን ሰባኪ ወንጌላዊ አያጠምቅም፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ማን እንደሚያጠምቅ አይናገርም፡፡ የባህሉ ዓላማ የማህበሩን አንድነት ለማጠናከር ነው፡፡

በተጨማሪም የወንጌላዊ ተግባር ወንጌልን መስበክ ነው፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ፣

«ከቀርስጶስና ከጋይዮስ በቀር ከእናንተ አንድ እንኳ ስላላጠመቅሁ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፡፡ የእስጢፋኖስንም ቤተሰቦች ደግሞ አጥምቄአለሁ፤ ጨምሬ ሌላ አጥምቄ እንደሆነ አላውቅም፡፡ ለማጥመቅ ክርስቶስ አልላከኝምና፣ ወንጌልን ልሰብክ እንጂ» (1 ቆር. 1÷14-17)፡፡

ወደ ሰሜናዊ ሲዳማ በደረስኩ በመጀመሪያዎቹ ጊዜያት ከሦስት ቡድኖች ጋር ተያይዤ ነበር፡፡ እነርሱም የወላይታ ማህበር፣ የሲዳማ ማህበርና ኤስ.አይ.ኤም ሚስዮን ናቸው፡፡ ያኔ «ሱዳን ኢንተርየር ሚስዮን» ይባል ነበር፡፡ ሦስቱም ቡድኖች ትክክለኛ ድርጅታዊ መዋቅር ከማጣታቸው የተነሳ አንዳንድ ጊዜ የግንኙነት ችግር ነበረባቸው፡፡

ከሦስቱ ሁሉቱ ቡድኖች በሰሜናዊ ሲዳማ በተፈጸመው የመጀመሪያው የጥምቀት ሥነ ሥርዓት ተሳትፈዋል፡፡ ከደቡባዊ ሲዳማም ተወካዮች ተገኝተው ሊሆን ይችላል፣ እርግጠኛ አይደለሁም፡፡

የወላይታ ማህበር የተሳተፈበት ምክንያት የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤቶች በመክፈት በትምህርት ዘርፍ ስለተያያዘ ነው፡፡ አሁንም ከደቡባዊ ሲዳማ መሪዎቹ ስለመሳተፋቸው እርግጠኛ ባልሆንም፣ በዚያን ጊዜ ከወላይታ ወንጌላውያን ከሰሜናዊ ሲዳማ ጋር ብዙ ግንኙነት የነበረ አይመስለኝም፡፡ ነገር ግን በአሰታ ወንዶ ወረዳ ውስጥ ሦስትና አራት ማህበር ብቻ ነበርና በመጀመሪያው ጥምቀት ከዚያ አካባቢ ተሳትፈው እንደሆነ አላስታውስም፡፡ ነገር ግን ሚስተር ደልማር እስቲቨንስ ከአለታ ወንዶ ኤስ አይ ኤም በጥምቀቱ ሥነ ሥርዓት ተገኝተዋል፡፡

ከደቡባዊ ሲዳማ የተወከሉ መሪዎች መጥተው ቢሆን ኖሮ ሚስተር ዳልማር እስቲቨንስ ባላጠመቁም ነበር፡፡ ስለዚህ ከወላይታ የመጡ የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎችና ሚስተር ዶልማር እስቲቨንስ አጥምቀዋል፡፡

ከወላይታ ሽማግሌዎች አንዱ አቶ ፍራንጅ ይባላሉ፡፡ የሌሎቹን ስም ግን አላስታውስም፡፡ የወላይታ ማህበር ሽማግሌዎች ለማጥመቅ ወደ ሲዳማ አንድ ጊዜ ብቻ መጥተዋል፡፡ ከመጀመሪያው ጥምቀት በኋላ የሰሜናዊው ሲዳማ ሽማግሌዎች ያጠምቁ ነበር፡፡

ጥምቀት ያን ጊዜ ልዩ መዋቅር ነበረው። ሰባኪ ወንጌላውያን ለመጠመቅ የተዘጋጁትን ሰዎች ስም ዝርዝር ያስቀምጣሉ። መዘጋጀት ማለት ግልጽ የሆነ የልብ ለውጥ ሲሆን፣ በአዲስ ሕይወት መመላለስ የሚረጋገጥበት ነው። ግለሰቡ በማህበሩ መካከል በሚያደርገው ክትትልና፣ ተሳትፎ ፍፁም ትክክለኛ ና ታማኝ መሆን ይጠበቅበታል።

ወንጌላዊው የማህበሩን አባሎች ሃሳብ ማዳመጥ አለበት። ከዚያም ሃሳቡን በቅርበት የተመለከቱበትን የማጽደቅና ያለማጽደቅ ውሳኔ ላይ ይደርሳሉ። በጥንቱ ጊዜ የጥምቀት ሥነ-ሥርዓት የሚካሄደው በእሁድ ቀን ነበር። በአሁኑ ጊዜ ግን በማንኛውም ቀን ቢሆን የሚያመጣው ለውጥ የለም። ከሳምንቱ በየትኛው ቀን እንደሚፈፀም እርግጠኛ አይደለሁም።

ለመጠመቅ የተዘጋጁ ሰዎች ጥምቀት በሚከናወንበት አካባቢ ቅርበት ባለው ቤተክርስቲያን ገብተው ያድራሉ። በሚያጠምቋቸው ሽማግሌዎች ስለ እምነታቸው አቋም ይጠየቃሉ። ስለ ሕይወታቸው በጥያቄ ይመረመራሉ። ያልገባቸው ነገር ካለም ግልጽ እንዲሆንላቸው ይደረጋል። በአጋጣሚ የተሰወረ ኃጢአት የሚገለጥበት ካለ ከመጠመቅ እንዲዘገይ ይደረጋል።

ከቤተክርስቲያኑ እስከ ማጥመቂያው ወንዝ ድረስ በተርታ ሰልፍ የሚጓዘው ሕዝብ ሰላ አስደናቂ እይታ ነበረው። በአካባቢ ካሉት ማህበራት አባላት የሆኑ አማኞች ሁሉ አብረው ሰልፉን መቀላቀል ይጠበቅባቸዋል።

እያንዳንዱ ሰው ያለውን ምርጥ ልብስ ስለሚለብስ፣ ሥርዓቱ የበዓል አከባበር ይመስል ነበር። ዝማሬው ከፀሎት ቤቱ ይጀምርና እስከ ማጥመቂያው ወንዝ ድረስ ይቀጥላል። ይህም የሚሆንበት ሁለት ምክንያት ነበረው። ይኸውም የአማኞችን ደስታ ለመግለጽና የአካባቢውን ነዋሪ ሕዝብ ትኩረት ለመሳብ ነው።

በምንዘምርበት ጊዜ ብዛት ያለው የአካባቢው ሕዝብ እየተከተለን ወደ ወንዙ በመሄድ የሚከናወነውን የጥምቀት ሥነ-ሥርዓት ይመለከታል።

ለሥነ ሥርዓቱ ሰልፍ ፈረሶችም ይጨመራሉ፤ የራሱ ፈረስ ያለውና ፈረስ ለመዋስ የሚችል ሁሉ በማምጣት ወደፊትና ወደኋላ ሸምጥ እየጋለቡ ያዳምቃሉ። የሸምጥ ግልቢያ የሚያስደንቅ ነበር። ይህም ከወላይታ ካመጣነው ባህላችን ሌላኛው ትንሹ ክፍል ነው።

ከሕዝቡ ብዛት የተነሳ የፈረስ ግልቢያው በብዙ ሰዎች ላይ ጉዳት በማድረሉ የዚያ ዓይነት ሥርዓት ተከልክሎአል። ከዋናው ጥምቀት አስቀድመን በወንዝ ዳር መንፈሳዊ መልዕክት እናስተላልፋለን። በሥነ ሥርዓቱ ላይ ደልማር እስቲቨንስ ይሰብኩ ነበር፣ ሌሎችም ንግግር ያደርጋሉ።



ስለ ጥምቀት ምንነትና አስፈላጊነት ካብራሩ በኋላ ወንጌልን ይሰብካሉ። በዕለቱ የሚያምን ባይኖርም በጣም ብዙ ሰዎች ግን ወንጌልን ይሰማሉ። የጥምቀት ሥነሥርዓት ብዙውን ጊዜ ልጆችን ይስብ ነበር። ብዙ ልጆችም መልካሙን ዜና በደንብ ይሰሙ ነበር። በምንሰብክበት በታ ሁሉ ወጣቶች ከአዋቂዎች የበለጠ ወንጌልን ለመስማት ፈጣኖች ናቸው። ከፍተኛ ፍላጐትም ነበራቸው።

በሰሜናዊ ሲዳማ ከመጀመሪያው ጥምቀት ሂያ የሚያህሉ ሰዎች ተጠምቀዋል። ያ ማለት ከእያንዳንዱ ማህበር አራት ወይም አምስት ሰዎች የተውጣጡ ሲሆን፣ ግማሾቹ ሴቶች ናቸው።

ከስብከት በኋላ የማጥመቁ ሂደት ይቀጥላል። ከወላይታ የመጡ የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎችና ሚስተር ደልማር እስቲቨንስ ለመጠመቅ የተዘጋጁትን አማኞች በጊዳቦ ወንዝ አጥምቀዋቸዋል። በዚያ በታ የተገኘው እያንዳንዱ ሰው ይዘምርና ይደሰት ነበር። ውኃው በጣም ሞልቶ ነበርና ምናልባት ወሩ ሐምሌ ይሆናል ብዬ እገምታለሁ።

ከሁለት ዓመት በኋላ ወየሳና እኔ የጊዳቦን ወንዝ ለመሻገር ስንሞክር በውኃ ልንወሰድና ልንሰምጥ ነበር። ሁለታችንም ወደ ማህበር ስብሰባ እንሄድ ነበር። ውኃው በድንገት ገፍቶን ብዙ መቶ ሜትሮች ከወሰደን በኋላ በአጋጣሚ በወንዙ ዳር ባገኘነው ሐረግ ተንጠላጥለን ራሳችን ከውኃው በመውጣት ድነናል። ለሞት ተቃርበን ነበር።

የሚከናወነውን የጥምቀት ሥነ-ሥርዓት ለመመልከት በወንዙ ዳር የተሰበሰቡት የአካባቢው ነዋሪዎች ምንም ተቃውሞ አያቀርቡም ነበር። ጥምቀት ሲባል ሁልጊዜ የሚመለከቱት ስለሆነ ለምደውታልና ምንም አይመስላቸውም ነበር። ከተጠማቂዎቹ ለአንዳንዶች ከቤተሰቦቻቸው ተቃውሞ ቢያጋጥማቸውም ለክፉ የሚሰጣቸው አልነበረም።

የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ለዚህ ዓይነት የጥምቀት ሥርዓት ሁልጊዜ ተደሳቾች አልነበሩም። ለምን እንደሆነም ይገባናል። በእነርሱ አዕምሮ ማጥመቅ የሚችሉት ቄሶች ብቻ ሲሆኑ፣ የሚያጠምቁትም ሕፃናትን ብቻ ነው። አዋቂዎችን በሚያጠምቁበት ጊዜ ውኃ ይረጩባቸዋል። የእኛን ጥምቀት ቢያማርሩና ቅሬታ ቢሰማቸውም ሌላ ሊያደርጉ የሚችሉት ነገር አልነበራቸውም።

በዚያን ጊዜ የጥምቀት ሥነሥርዓት እንዳበቃ የጌታን እራት ፤ቅዱስ ቁርባንን እንወስድም። ያ የሚወሰነው በቤተክርስቲያኒቱ ይሆናል። ለተጠመቁት ሁሉ ቅዱስ ቁርባን መውሰድ የመጀመሪያ ጊዜያቸው ይሆናል።

ይህ ለእኔ ልዩ ትርጉም የሚሰጠኝ ነበር። ምክንያቱም በዚያ ማህበር የመጨረሻዬን ቅዱስ ቁርባን በመውሰድ ስለምሳተፍ ነው። ሰዎች ከተጠመቁ በኋላ የጌታን እራት፣ ቅዱስ ቁርባንን በመስጠት ማገልገል የቤተክርስቲያን ሃላፊነት ነው።

ከመጀመሪያው ጥምቀት በኋላ ከቀድሞው ስብከት የበለጠ ታላቅ ፍላጐት ያላቸው ብዙ ሕዝቦች ያምናሉ። ሌሎች ሰባኪ ወንጌላውያን ከወላይታና አንዳንድ የሲዳማ ወንጌላውያን ከአስታ ማህበራት በመምጣት በሰሜናዊ ሲዳማ ይሰብኩ ነበር። የመጀመሪያው የጥምቀት ሥነሥርዓት ትልቅ ደረጃ የሚሰጠው ነበር። አዳዲስ ቤተክርስቲያኖችም ወደ ሌላ ዕድገት የሚሸጋገሩበት ነው። እነርሱም በተራቸው ሌላ ሽማግሌዎች አስመርጠው በጌታ እራት ፣ ቅዱስ ቁርባን አገልግሎት እንዲሳተፉ ያደርጋሉ።

እንዲህ ዓይነት ታላቅ ፍላጐት ብዙ ስብከትን የሚያመነጭና ብዙ አማኞችን የሚያመርት ዘዴ ሲሆን በተጨማሪም በክልሉ አዲስ ህብረት ነበር።

# ምዕራፍ ስምንት

# የቤተ ክርስቲያን ህብረት

## አዲስ ማህበር ተመሠረተ

ማህበር ማለት የቤተክርስቲያን ስብስብ ሆኖ የተመሳሳይ ቤተክርስቲያን አባላት አንድነት ነው። ከመልክአ ምድር ቅርበት የተነሳ የአስተዳደር መዋቅር ዕድገትና ጥንካሬ ለማበርከትም ችሏል።

በወላይታና በሲዳማ ሁለት ዓይነት ማህበሮች አሉ። ትልቁ ማህበር በወር አንድ ጊዜ የሚሰበሰብ ሲሆን፣ ብዙ ንዑሳን ማህበራትም በየወሩ ይሰበሰባሉ። የነበሩት ተወካዮች ከአካባቢው ማህበራት ሁሉ ይሰበሰባሉ ወይም ይገናኛሉ።

ተወካዮቹ ከግል ማህበራት ይልቅ ከንዑሳን ማህበራት የተውጣጡ ናቸው። የወርሃዊ ስብሰባዎች ጅማሬ በጣም ኢምንት የሆነና ዓይን ውስጥ የማይገባ ነው። በማህበሩ ዕድገት ላይ የተመሠረተ የማያቋርጥና ተለዋዋጭ ባህርይም የሚታይበት ሁኔታ ይኖራል።

አንዳንድ ጊዜ መዋቅሩን ማደስ የማህበራቱን ውጤት የበለጠ ተፈላጊ ያደርገው ነበር። ማህበሩ ትልቅም ይሁን ትንሽ ወንጌል ምን እንደሆነ በመረዳት ረገድ በጣም አስፈላጊውን ሚና ይጫወታል። ለግለሰብም ሆነ ለማህበር ወንጌልን መረዳት የበለጠ አስፈላጊ ነው። እያንዳንዱ አዲስ አማኝ ለመጀመሪያ የማበሩን ስብሰባ በሚካፈልበት ጊዜ እንዲህ ይሉ ነበር።



«ድንቅ ነው! ይህ በሺህ የሚቆጠር ሕዝብ ሁሉ በኢየሱስ የሚያምን ነው ማለት ነው?» ብዙውን ጊዜ አስገራሚ መበረታታት ይሰማቸው ነበር። በማንኛውም ጊዜ ከክርስቲያኖች ህብረት ጋር ስሠራ ወደ ማህበር ስብሰባ መጥተው እንዲካፈሉ እገፋፋቸዋለሁ። ያም እምነታቸውን ያሳድጋል፣ በፍጥነትም ነገሮችን ወደ መረዳት እንዲደርሱ ያደርጋል። ወዲያውም የሚሰጣቸው መልዕክት፣ «የዚህ ህብረተሰብ አካል ሆነሃል። እነዚህ አዳዲስ ወንድሞችህና እህቶችህ ናቸው» የሚል ነበር።

ማህበሩ በቤተክርስቲያን ህብረት ላይ ጠቃሚ ሚና መጫወት ይችላል። ከልምዱ እንደተረዳሁት አንዱ ካንዱ ጋር ተባብሮ የማይሠራ ማህበር ራስ ወዳድ ይሆናል።

ማህበሩ፣ ክርስቲያኖች አብረው እንዲሠሩና ሀሳብ ለሃሳብ እንዲለዋወጡ ሁኔታዎችን ያመቻቻል።

## አዳዲስ አማኞችና ማህበሩ

በሰሜናዊ ሲዳማ የመጀመሪያ ማህበር ህብረት የመሠረትነው በ1943 ዓ.ም አካባቢ ነበር። በአርቤ መስበክ በጀመርኩ ጊዜ ሌሎች የወላይታ ወንጌላውያን ይሰብኩ የነበሩበት ሦስት ቦታዎች ነበሩ።

በእያንዳንዱ ቦታ ጥቂት አማኞች ብቻ የነበሩ ሲሆን፣ ለመጀመሪያ እያንዳንዱን ማህበር ይመራ የነበረው የወላይታ ወንጌላዊ ነበር። በእያንዳንዱ ወር ከሦስት ማኅበራት የተውጣጡ ቡድኖች ሌላውን ይጐበኛሉ። ከወላይታ ያመጣነውን ባህል ስናስተዋውቅ ማህበሩ ሳይታሰብ በድንገት ይቀበል ነበር። ወርሃዊ ስብሰባ አለ ብሎ ማንም ግለሰብ አያስብም ወይም አያስተባብርም። ልክ እንደ እሁድ ቀን አምልኮት እያንዳንዱ ሰው አውቆ ሄዶ ይሳተፋል።

በሰሜናዊ ሲዳማ ጥቂት ማህበራት እንደተቋቋሙ ክርስቲያኖች በየወሩ ተሰባስበን መገናኘት ጀመርን። በየወሩ ለመዘመር ለመፀለይና እንዲሁም በጋራ ጉዳዮች ላይ ለመወያየት እንገናኝ ነበር። ከእያንዳንዱ ማህበር ወንጌላውያን በህብረት ተገናኝተው ስለ አንዳንድ ችግሮችም ይወያያሉ። የውጪ አገር ሚስዮናውያንም እንደ እንግዳ ሆነው የማህበሩን ስብሰባ ቢካፈሉም፣ በአስተዳደሩ መዋቅር ውስጥ ምንም ተሳትፎ አልነበራቸውም። የውስጥ አስተዳደር የግል ጉዳያችን ነው። በመጨረሻም እያንዳንዱ ማህበር የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎችን ከመረጠ በኋላ የተመረጡት ሽማግሌዎች ተሰብስበው ስለ ጋራ ጉዳዮች ይወያያሉ።

## የማህበሩ ዓላማዎች

ማህበሩ አራት ዓላማዎች ነበሩት፡፡ ምግብ ማቅረብ፣ የህብረት ጊዜ ማዘጋጀት፣ በጋራ እቅድ ማውጣትና ችግሮችን መካፈል ናቸው፡፡ ስብሰባው የሚጀምረው ቅዳሜ ማታ ሲሆን፣ በቀን አራት ጊዜ እንመገባለን፡፡ ወደ ማታ እንደደረስን መቆያ፣ ከምሽቱ 3 ሰዓት እራት፣ ጠዋት በነጋታው፣ ቁርስና እኩለ ቀን ላይ ምሳ ከተበላ በኋላ ሁሉም ተሳታፊዎች ወደየቤታቸው ይበታተናሉ፡፡

ገና ወደ ስብሰባው ቦታ እንደተደረሰ ሁሉም በእግሩ ተጉዞ የመጣ በመሆኑ የሁሉም ተሳታፊ እግር ይታጠባል፡፡ የአስተናጋጁ ቤተክርስቲያን አባላት የእንግዶቹን እግር አሽተው ያጥባሉ፣ ጥቂት ሰዎች በየግላቸው በቅሉ ቢጠቀሙም አብዛኛዎቹ ግን በእግራቸው ይጓዛሉ፡፡

በእያንዳንዱ የማህበሩ ስብሰባ ሁለት ትላልቅ ስብሰባ እናካሂዳለን፡፡ አንደኛው እኩለ-ሌሊት ሲሆን፣ ሁለተኛው በነጋታው ጧት ይካሄዳል፡፡ በመጨረሻም መላው አማኞችና ወንጌላውያን በህብረት ይሰበሰባሉ፡፡ ዝማሬውን የሚሰሙ የአካባቢው ነዋሪዎች የሚከናወነውን ሥነ-ሥርዓት ለማየት ይመጣሉ፡፡ ወዲያውም ወንጌልን ሰምተው ይመለሳሉ፡፡

ቤተክርስቲያን ወንጌላውያንን በመቅጠር በህብረት ትሰራለች፤ ትልቁ ማህበር ግን ሁል ጊዜ በሌላ አካባቢ ሄዶ የሚያገለግለውን ወንጌላዊ ይቀጥራል፡፡ እያንዳንዱ ቤተክርስቲያን ግን ለደመወዝ የሚሆነውን ገንዘብ በእኩል ያዋጣል፡፡

የአካባቢው ማህበር የግማሽ ጊዜ ወንጌላውያንን ይቀጥራል፡፡ የሚቀጠሩት ወንጌላውያንም በአካባቢያቸው ቃሉን እየሰበኩ ያገለግላሉ፡፡ እያንዳንዱ የአስተዳደር ዘርፍ ወንጌላውያንን በመቅጠር ይተጋል፡፡ ከጥንት ጀምሮ ለአካባቢው አማኞች ወንጌላውያንን መቅጠር ዋነኛ ተግባር ነው፡፡

በአጠቃላይ ለማህበር ስብሰባ ከየማህበራቱ የመጡት የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች በምሽትና ጠዋት ተሰብስበው ከየማህበራቸው ያጋጠማቸውን ችግሮች አቅርበው በጋራ ይወያያሉ፡፡

ስለ አገልግሎትና ስለ ገንዘብ አጠቃቀም፣ እንዲሁም ስለ እያንዳንዱ ማህበር አስተዳደር ለመወያየት ጊዜው ያኔ ነው፡፡ ስላሉት ችግሮች መወያየትና ስለ መፍትሄውም በስፋት መነጋገር የእረኝነትንና የመንፈሳዊ ትምህርት መርህን ይፈጥራል፡፡ ውሳኔያችን ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረተና በሰሜናዊ ሲዳማ ማህበራዊ ሕይወት አቅጣጫ እንዲይዝ የሚያደርግ ነበር፡፡



## ማህበሩን መገናኘት

በአርኪ ከመጀመሪያ አማኞች ጀምሮ ሁሉም የማህበሩ አካል ሆኗል፡፡ ከጅምሩ ጥቂቶች ብንሆንም እንኳን በህብረት ተሰብስበን እንመገባለን፣ እንፀልያለን፣ እንዘምራለን፡፡ ሌሎች ሰዎች የሚያቀርቡት ሃሳብ ቢኖርም በጋራ እንወያይባቸዋለን፡፡ በደንቡ የሚቀርብ ማመልከቻና የሚጸድቅ ነገር አልነበረም፡፡

በዚያን ጊዜ የተወሰኑ ወንጌላውያን በሰሜናዊ ሲዳማ ለመሥራት መጥተው ነበር፡፡ አላሮ ሃርዴዶ ፋንጉ በሚባል ቦታ ነበርና ብዙ ግንኙነት ከእርሱ ጋር የሰንም፡፡ ሌሎቹ በካሉ፣ ቂልቶ፣ ሌራ፣ ጉጂ፣ ሱላሞ፣ ኤቤሮ፣ ሾንጋ፣ ሳዴቦ፣ ታንቱ፣ ደቤራ፣ ቶሮ እና ጋዲሞ ይባላሉ፡፡

አንዳንዶቹ ብዙ አልቆዩም የእኔ ወንጌላዊነት ሥራ ከእነርሱ የተለየ በመሆኑ ከእነርሱ ጋር የምሠራው ብዙ ሥራ አልነበረም፡፡ ከወላይታ ወንጌላዊ ለመቅጠር ማንም አያስብም፡፡ በመጀመሪያው ትውልድ ቤተክርስቲያን ሁሉም አማኝ ሰባኪ ነበር፡፡ ነገር ግን ለመስበክ ሁልጊዜ የሚከፈል ዋጋ አለ፡፡

## የስብከት ዋጋ

በሰሜናዊ ሲዳማ እኛ የምንሠራውን ሥራ የማይወዱት ተቃውሞአቸውን ለማቅረብ ቀላል አልሆነላቸውም፡፡ የመንግሥት አስተዳደር ቅሬታንና ክስን በተገቢው መንገድ እየተቀበለ የሚያስተናግደው በሕጋዊ መንገድ ስተመዘገቡት ብቻ ነው፡፡ መመሪያው በገጠር ሕዝቦች ጉዳይ ጣልቃ የሚገባው በትንሹ ነው፡፡ ስለዚህ በአብዮታዊ ለውጥ ጊዜ እንኳን ከ1966-1983 ዓ.ም ከመንግሥታዊ አስተዳደር አንዳች ተቃውሞ አልደረሰብንም፡፡

የሲዳማ ህብረተሰብ የመልካሙን ዜና ስብከት የሚቃወምበት በቂ ምክንያት አልነበረውም፡፡ ሃይማኖት የግለሰብ ወይም የቤተሰብ ጉዳይ ነው፡፡ እያንዳንዱ ቤተሰብ በሃይማኖቱ ተደስቶ ይኖራል፡፡ ክርስቲያኖች የሲዳማን ባህላዊ ህብረተሰብ መረጋጋት በፍርሃት ስሜት የሚያዩት አይደለምና፡፡

## የተቃውሞው ዋና ምክንያት

አንዳንድ የመንግሥት ባለሥልጣናት በስብከታችን አልተደሰቱም፡፡ በኢየሱስ ማመን ግለኝነትን የሚያሳይ ስሜትና በግል የሚወሰን ውሳኔ ተደርጐ ይገመታል፡፡ ግን ከዚያ በጣም የበለጠ ነው፡፡ አንድ አማኝ የኢየሱስ ተከታይ በመሆን የኃይማኖታዊ መሪዎች ማለትም የቂሶች፣ የዲያቆናት፣ የሼኪዎች እና የቃልቻዎችን ስልጣን ጥያቄ ላይ እንዲወድቅበት ያደርጋል፡፡

አማኙ አንዱ የባህል ኃይማኖት መሪዎችን ስመጠየቅ ወኔ ሲያገኝ እና ጉብዝ ሲሆን የእነርሱን ትዕዛዝ ባስመቀበል የአካባቢው የመንግሥት ባለስልጣናት የሚያደርጉትን ብዙ ድርጊቶች ስመጠየቅ ሌላው ተጨማሪ እርምጃ ነበር:: ስምን? የሚባሰውን ጥያቄ በአካባቢው የሚገኙ የመንግሥት ባለሥልጣኖች መስማት የማይፈልጉት ነው:: አዳዲስ አማኞች ማመልከቻዎቻቸውን ወደ ፍርድ ቤት እንዲያቀርቡ አይሹም:: የባሕላዊ ሃይማኖት መሪዎችና የመንግሥት ባለሥልጣኖች እጅና ጓንት ሆነው ይሠሩ ነበር:: የባሕላዊ ኃይማኖት መሪዎች በአካባቢው የሚደረገውን ሁሉ ያውቃሉ:: የመንግሥት ባለሥልጣኖች ደግሞ ለሚያገኙት መረጃ ለባህላዊ ኃይማኖት መሪዎች የተለየ እንክብካቤ ያደርጉላቸዋል::

## ሁከት

የሃይማኖትና የፖለቲካ መሪዎች ቁጣቸውን ከሚወጡበትና ከተሳካላቸው መንገዶች አንዱ በግለሰብ በኩል ሁከት መፍጠር ነበር::

ይህ እንደ ሌሎቹ ማለትም እንደ ዓለማውያን ሰዎች በክርስቲያኖችም ዘንድ ቀላል አይደለም:: ምክንያቱም ዓለማውያን ከአማኞች ጋር በስካር ረብሻ አይሳተፉምና ነው:: ዳሩ ግን ክርስቲያኖችን በአካል አግኝተው ለማጥቃት መንገድ አግኝተዋል::

አንድ ቀን ጧት ከማህበሩ ስብሰባ ስመለስ የጥቃቱ ዒላማ ሆኜ ነበር:: በዚያን ቀን በማህበሩ ስብሰባ ካደርኩበት እሁድ ጧት በማለዳ ተነሳሁና ለአገልግሎት ለመድረስ ወደ ቤት እገሠግሥ ነበር:: በዚያ እሁድ በቤተክርስቲያን መገኘት አስብኘ ብዬ ወሰንኩኝ::

በሰሜናዊ ሲዳማ በእያንዳንዱ ወረዳ «ቆሮ» ተብሎ የተወከለ ሰው ነበር:: ይህም ቃል ከኦሮሚኛ ቋንቋ የተወረሰ ሲሆን፣ የአካባቢው ወረዳ አስተዳደር ተወካይ ተብሎ ይታወቃል:: እርሱም በዘመኑ በአማራው መንግሥትና በአካባቢው ሕዝብ መካከል ተወካይ ሆኖ ይሠራል:: «ባለታሪኩ የአፄ ኃይለሥላሴን መንግሥት «የአማራው» መንግሥት እያሉ ይጠራሉ» መንግሥት የራሱ ባለሥልጣኖች የነበሩት ሲሆን «ቆሮ» የተባለው ግን በሕዝቡ መካከል ሆኖ ቋንቋውንና ባህሉን ጠንቅቆ የሚያውቅ የመንግሥት ተወካይ ማለት ነው::

የአንድ ቆሮ ልጅ በእኔ ላይ ተቆጥቶ በመንገድ ያዘኝ:: ለካስ የእርሱን ሥልጣን በህዝቡ ያንቋሸሽኩበት ወይም የተፈታተንኩት መስሎት ኖሯል:: አንዳንድ ሰዎች የሚሠራውን ክፉ ሥራ በመቃወም ለምን? የሚል ጥያቄ ስለሚያነሱበት እኔን ይሰደበኝ እንጂ ሊመታኝ ሞክሮ አያውቅም ነበር::



በዚያን ጧት ግን ሰብቻዬ በመንገድ ስሄድ ያዘኝና ትንሽ ሁከት ከፈጠረ በኋላ በያዘው በወፍራም ዱላ ይደበድበኝ ጀመር:: እኔም የተመታሁበት አካሌ ሰንበር አውጥቶ ይደማ ጀመር::

ብዙ ከደበደበኝ በኋላ እየተራገመ ጥሎኝ ሲሄድ በሚቀጥለው ጊዜ ካገኘሁህ እገድልሃለሁ አለኝ:: እኔም በአቧራ ላይ ወድቄ እጆቼንና እግሮቼን እጥፍ ዘርጋ እያደረግኩ ምናልባት አጥንቴ ተሰብሮ እንደሆነ መፈተሽ ጀመርኩ::

ወደ ቤቴ ለመሄድ ባለመቻሌ ወደመጣሁበት ቅርብ ወደሆነው ወደ ማህበሩ ስብሰባ ተመለስኩኝ:: ማህበሩም ፀለዮልኝ አበረታታኝ:: እኔም ምስክር ስላልነበረኝ በሕግ ልከስሰው አልቻልኩምና ተደብድቤ ቀረሁ::

## መጽሐፍ ቅዱሶች

መጽሐፍ ቅዱስ ማለት አማኞች አዲስ ነፃነታቸውን ያወጁበት ግጭት ወይም ትንኮሳ በከፍተኛ ደረጃ የሚታይበትና አዲስ ነፃነትም ያተረፍንበት ነው::

የምንጠቀመው መጽሐፍ ቅዱስ በአማርኛ ቋንቋ የተጻፈ በመሆኑ ቀልብ የሚስብና ተቃውሞ የሚያባብስ ነበር:: ምክንያቱም በወቅቱ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን እምነት ተከታዮች በግዕዝ የተጻፉትን መጽሐፍቶች ስለሚጠቀሙ የበለጠ ትክክለኛ ነው ብለው ስለሚያስተምሩ ነው::

ነገር ግን የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ በንጉሥ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መብቱ የተከበረ ስለነበረ ከእነርሱ ግዕዝ መጽሐፍ የማይተናነስ መሆኑንም ያውቁ ነበር::

## ግዙፍ ገጽታ ወይም ምስል

ወንጌል እንደተሰበከ የሰሜናዊ ሲዳማ ሕዝብ በኢየሱስ ክርስቶስ ሲያምን ሥራችንም ከትንሹ ማህበር ጀምሮ እስከ ብሔራዊ የሃይማኖት ድርጅት ደረጃ እስከሚደርስ አድጓል::

ቀስ በቀስ አራት ደረጃ ያላቸው ህብረቶችና አስተዳደር ታይተዋል፤ የመጀመሪያው የአካባቢው ማህበር ነው:: ከመጀመሪያው ጀምሮ ራሱን በራሱ የሚያስተዳድር ክፍል ነው::

የመጀመሪያዎቹ አማኞች ወዲያውኑ ከማህበሩ ጋር እንደተዋወቁ የአካባቢው ራስን በራስ የማስተዳደሩ ሁኔታ ተነጣጥሏል:: እያንዳንዱ ማህበር የንዑስ ማህበራት አካል ነው:: በየወሩም ተወካዩን ወደ ትልቁ ማህበር ይልካል:: በአንዳንድ ቦታዎች ንዑሳን ማህበራት የወሩ ግማሽ ወይም የ15 ማህበር ተብሎ ይጠራል አንዳንዴም የክፍል ማህበራት ይባላሉ::

እነዚህ ንዑሳን ማህበራት የየራሳቸውን ተወካይ ወደ ወሩ ማህበር ወይም ወደ 30 ማህበር ጉባኤ በየወሩ ወደሚካሄድበት ስብሰባ ይልካሉ። ከዚያም ከትልቁ ማህበር ጋር የቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያን ተብለን እንጣመራለን። ያም ወደ 1962 ዓ.ም አካባቢ ብሔራዊ ሃይማኖታዊ ድርጅት የሆነው ነው።

# ምዕራፍ ዘጠኝ

# ከሚስዮኑ ጋር በሲዳማ!

## ሚስዮን

እኔ በክርስቶስ ባመንኩ ጊዜ ሚስዮን ማለት ሱዳን ኢንተርየር ሚስዮን ይባል ነበር። በኋላም ኤስ.አይ.ኤም በመባል ተለውጧል። እኔ ግን ሁልጊዜ የምጠራው በመጀመሪያ ስሙ ነው።

## የመጀመሪያ ግንኙነቶች

የእኛ ቤተሰብ ለመጀመሪያ ከሚስዮኑ የተገናኘው የእንጀራ እናቴ በሶዶ አጠገብ ወደሚገኘው ወደ ኦቶና ሚስዮን ሆስፒታል በሄደች ጊዜ ነበር። ኦቶና ስለሚኖሩት ስለ ውጪ ዜጎች አስቀድሜ ሰምቼ ነበር። እንደ እውነቱ ከሆነ ሆስፒታል እንዳላቸውና ለምን እዚያ እንዳሉ አይገባኝም ነበር።

ከሚስዮኑ ጋር የግል ግንኙነት ያደረግኩት ከጣሊያን ወረራ በኋላ ሲሆን፣ ዶክተር ናታን ባርሎው በሚሰጡት የጤና ረዳት ሥልጠና ለመሳተፍ እኔ ተመርጬ ነበር። ያንን ሥልጠና ማስተላለፍ ነበረብኝ። ምክንያቱም እግዚአብሔር አንድ ነገር እንድሠራ እንደጠራኝ አውቃለሁ። ስለ ጥሪዬ በሌላ ስፍራ እነግራችኋለሁ።

ቀጥሎም ዋልተር ኦህማን ሶዶ በሚገኝ ቤታቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጠና መስጠት ጀመሩ። በዚያ መጽሐፍ ቅዱስን ለመማር በሄድኩበት የአሜሪካን ሚስዮናውያንን ለመጀመሪያ ጊዜዬ አይቻቸዋለሁ። ከአምሳ ዓመት በላይ እርስ በርሳችን በጋራ ብዙ ሠርተናል።

## ሚስዮኑና ቤተ ክርስቲያን

እኔ በኢየሱስ ክርስቶስ ካመንኩ በኋላ የውጪ አገር ሚስዮናውያን ወንጌልን ለመስበክ ወደ ኢትዮጵያ እንደገቡ ሰማሁ። አብዛኛው ሕዝብ የሠሩትን ሆስፒታልና ት/ቤቶች ከማየት በስተቀር የሚስዮናውያኑ ዋና ዓላማ ወንጌልን መስበክ እንደሆነ አልተገነዘበም ነበር።

ወንጌልን ሰምተው የተቀበሉና ሕይወታቸው የተለወጠ የወላይታ ሰዎች ቤተክርስቲያንን መሥርተዋል። እኔ ክርስቲያን በሆንኩ ጊዜ አዳዲስ አማኞች



ተጽናንተው የራሳቸውን ማምለኪያ ቦታ ለአሁድ አምልኮት ያዘጋጃሉ ብሎ ማሰብ ያልተለመደ ሃሳብ ነበር።

የውጪ አገር ሚስዮናውያን በዱጉና አካባቢ ለመስበክ አይሳተፉም። ለወንጌላውያን ገንዘብ አይከፍሉም። የፀሎት ቤትም አይሰሩም፣ ከአካባቢ ማህበራት ጋር በአስተዳደር ጉዳዮችም አይሳተፉም።

እንደሰማሁትና እንዳየሁትም የውጪ አገር ሚስዮናውያን በመጽሐፍ ቅዱስ ዙሪያ ብቻ ይመላለሳሉ። ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን በሚገባ እንዲያውቁ ይፈልጋሉ። ስለዚህም የመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጠና ይሰጡ ነበር።

## ሚስዮን

በስብከታችን ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ «ማመን» የሚለውን ቃል እንጠቀማለን። ተመጣጣኝ ቃሉም «መምረጥ» የሚለው ሊሆን ይችላል። በምንሰብክበት ጊዜ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ እንዲያምኑ እንጋብዛለን። ምክንያቱም ከፍርድ የሚያድን እርሱ ብቻ ስለሆነ ነው።

መልካሙን ዜና ሰምተው ያመኑ ሰዎች ራሳቸውን አማኞች ብለው ቢጠሩ የሚያስደንቅ አይደለም። ግን ሌሎች ሰዎች ምን ብለው ይጠሩናል? ክርስቲያን የሚለው ቃል አስቀድሞ የተያዘ ስም ነው። በሲዳማና በወላይታ ክርስቲያን የሚለው ቃል ለኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ብቻ የተሰጠ ተደርጐ ይገመት ነበር። ዛሬም ቢሆን የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ተከታዮች ክርስቲያን ብለው የሚጠሩት የራሳቸውን እምነት ተከታዮች የሆኑትን ብቻ ነው። ለእኛ ለአማኞች ደግሞ ክርስቲያን ማለት ክርስቶስን ያመኑና የሚከተሉ በእግዚአብሔር የተመረጡ ሰዎች አንድነት ወይም ስያሜ ነው።

እኛም የውጪ አገር ሚስዮናውያን የሚጠቀሙበትን ተመሳሳይ መጽሐፍ ቅዱስ ስለምንጠቀም ሰዎች «ሚሽን» ብለው ይጠሩን ነበር። ከመንግሥት አስተዳደር ባለሥልጣኖች ጋር ስለ እኛ በሚነጋገሩበት ጊዜ የሚጠሩን «ሚሽን» ብለው ነው። ቃለ ሕይወት የሚባል ስም በ1961 ዓ.ም ስንገናጸፍ በስማችን ዙሪያ የነበረው ግራ መጋባት በግልጽ ሁኔታ ተስተካክሏል።

## ሚስዮኑና የእኔ ተልዕኮ

የእኔን ተልዕኮና የሚስዮኑን የሥራ ክፍል ምን እንደሆነ ለመለየት ከባድ ነው። በኦቶናና በአለታ ወንዶ ኤስ አይ ኤም የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ገብቼ ቃሉን እማር ነበር። በከፋ ክፍለ ሃገር አንድ ዓመት ያህል ከኤስ አይ ኤም ሚስዮን ጋር በህብረት ወንጌልን በማሠራጨት ሠርተናል።

አንዳንድ የውጪ አገር ሚስዮናውያን በአገልግሎቴ ጠቀሜታ ያለው ምሳሌነትን በማሳየት ተሳትፎ አድርገዋል:: ብዙዎቹ በመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት አስተማሪዎቼ ነበሩ:: መጽሐፍ ቅዱስን የማስተማር መዋቅሬን ያገኘሁት በሚስዮኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤቶች ውስጥ በመማሬ ነው::

በሲዳማ ስሰሠራሁት ሥራ ሚስዮኑ የተጫወተው ሚና ትንሽ ነበር:: የአስተዳደር ተሳትፎ አልነበራቸውም፣ የትም ብሄድና ብሠራ ምንም ግምት ውስጥ አያስገቡኝም:: ማናቸውም ቢሆኑ በግል አገልግሎቴ ጠለቅ ብለው እጃቸውን አያስገቡም ወይም አይሳተፉም::

ለአገልግሎቴ የገንዘብ አስተዋጽኦ አያደርጉልኝም:: ከውጪ አገር ሚስዮናውያን ፍፁም ደሞዝ ተቀብዬ አላውቅም:: ሚስዮኑም ለአገልግሎቴ ገንዘብ ሰጥቶኝ አያውቅም:: አልፎ አልፎ በእርግጥ የግል ስጦታ ያደርጉልኛል፤ ነገር ግን አበል ወይም ደመወዝ አልነበረኝም::

## ዳግመኛ በመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት

በሲዳማ ከሚስዮኑ ጋር ካደረግኩት ግንኙነቶች የመጀመሪያው ከሚስተር ደልማር እስቲቨንስ ጋር ነበር:: በሰባኪነቱና በወንጌላዊነቱ በማከናውነው ነገር ሁሉ በጣም ያበረታቱኝ ነበር::

በግንቦት ወር በ1938 ዓ.ም እርሳቸውና ባለቤታቸው ሜሪ ከጣሊያን ወረራ በኋላ ወደ ሲዳማ የመጡ የመጀመሪያዎቹ ሚስዮናውያን ነበሩ:: በዚያው ዓመት በህዳር ወር ከሆማቾ ወደ ወንዶ ተዛወሩ:: በዚያም ለአሥር ዓመት ያህል ሠርተዋል::

በ1942 ዓ.ም ሚስተር እስቲቨንስ በአለታ ወንዶ የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ከፈቱና እንድገባ ጋበዙኝ ያ ማለት ከአርሬ ወደ ዋሜ የተዛወርኩበት ወቅት ነበር:: የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ዓላማ በሰሜናዊ ሲዳማ ለአማኞች አዲስ ግንዛቤ የሚሰጥ ነበርና እርዳታ በመፈለግ ይወተውቱ ነበር:: ሚስዮኑ በምግብና በሌላ አስፈላጊ ነገሮች እንዲረዳቸውና የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ገብተው መማር እንዲችሉ ይፈልጉ ነበር:: ግን በዚያን ጊዜ ት/ቤት ገብተው ለመማር ብዙም የተነሳሱበት ወቅት አልነበረም::

ከወላይታ የመጣን ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት የምናውቀው ብዙ ልምድ ነበረን:: ለተወሰኑ ዓመታት ተሳክቶልንም ተከታትለናል:: በየሳምንቱ መጨረሻ ቀናት ከት/ቤቱ ወደ ዋሜ ለስብከት እሄዳለሁ::

በአለታ ወንዶ የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት በነበርኩ ጊዜ ወደ አፋራራ ሄጄ በቤተክርስቲያን እሰብክ ነበር:: በሰሜናዊ ሲዳማ አንዳንድ የማህበራት መሪዎች ከወላይታ የመጡ ሰዎች በወንዶ የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት



መማራቸው ትክክል አይደለም የሚል ስሜት ነበራቸው:: ምክንያቱም ለእነርሱ የመጣው ገንዘብ ለእኛ የሚሰጥ እየመሰላቸው ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ለመማር ከፈለጉ ወደመጡበት ወደ ወላይታ ሶዶ ሄደው መማር አለባቸው በማለት ይወተውቱ ነበር:: በገንዘብ አካባቢ ብዙ አለመግባባት ስለነበር ጭቅጭቁ ሥር እየሰደደ በመምጣቱ ምክንያት ሚስተር እስቲቨንስ የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤቱን ለመዝጋት በቅተዋል::

## በአለታ መስበክ

በአለታ ወንዶ የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት በነበርኩ ጊዜ በደቡባዊ ሲዳማ በብዙ ቦታዎች ወንጌልን ሰብኬአለሁ:: ቤራ የሚባለው ቦታ በጣም የማስታውሰውና እግዚአብሔር ትልቅ ስራ የሰራበት ጊዜ ነበር::

እዚያ ማህበር ከመሠረቱት ሰዎች መካከል እኔም ተሳታፊ ነበርኩ:: ዶኮ በሚባለው ሌላ ቦታ አዳዲስ አማኞችን በመርዳት አዲስ ማህበር የመሠረትኩበት ነበር:: ለአጭር ጊዜ ከከምባታ የመጡ ወንጌላውያንም የነበሩ ይመስለኛል:: የከምባታና የወላይታ ወንጌላውያኖች በአለታ በተለያዩ ቦታዎች ሠርተዋል:: በተመሳሳይ ወቅትም ወደ አርሬ በመሄድ እየጐበኘሁ ወደ ዋሜም እየሄድኩ እሰብክ ነበር:: በማንኛውም ቦታ ቋሚ ቁርኝት አልነበረኝም:: በደቡባዊ ሲዳማ በየወሩ ሠላሳ ማህበር ተብሎ የሚታወቅ ጉባኤ ይካሄድ ነበርና ወደ ማህበሩ ስብሰባ በምንሄድበት ጊዜ ወንጌልን ላልሰሙት በየቦታው የማሰማበት አጋጣሚ ነበረኝ::

እኔ በወንዶ የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት በነበርኩ ጊዜ የገንዘብ እርዳታ አገኝ ስለነበር የደቡባዊ ሲዳማ ማህበር መሪዎች በእነርሱ ሥር ያለሁ እየመሰላቸው ወደተለያዩ ቦታዎች ሄጄ እንድሰብክ ይልኩኝ ነበር::

እኔ ምንም ተቃውሞ አልነበረኝም:: ማንም ቢጋብዘኝ ወይም ቢልከኝ ወንጌልን መስበክ እፈልጋለሁ:: ሂዳ የሚባለው ሌላው ቦታ ሲሆን አዳዲስ አማኞችን ረድቼ ማህበር የመሰረትኩበት ነበር:: በአፋራራ መኖር ከጀመርኩ ወዲህ በአለታ ለመስበክ ያደረግኩት ግንኙነት አልነበረም::

## ለ3ኛ ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት

ሚስተር ዳልማር እስቲቨንስና ባለቤታቸው ሜሪ ወንዶን ለቅቀው ሲሄዱ በ1949 ዓ.ም ጆርጅና ዶሪቲ ምድልተን ተተኩ:: እነርሱም ለመሥራት ካቀዱት አንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤትን ዳግመኛ መክፈት ነበር::

በዚያን ወቅት ሚስዮኑ የገንዘብ እርዳታ የሚባለውን ነገር ሁሉ አቆመ:: እንዲያውም ሚስዮኑ እያስከፈለ ማስተማር ጀመረ:: ነገር ግን የደቡባዊ ሲዳማ ማህበር መሪዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ለሚማሩት ተማሪዎች የገንዘብ

እርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው በማሳሰብና ግትር ብለው በመከራከር በሚስተር ምድልተን ላይ አደሙባቸው።

በመሪነት ሥልጣን የነበሩት ሰዎች በማደማቸውና እልህ ውስጥ በመግባታቸው ከአካባቢያቸው አንድ ወይም ሁለት ተማሪዎች ብቻ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት መጥተዋል። የተቀሩት አብዛኛዎቹ ወንጌላውያን ከወላይታ የመጡ ናቸው።

በአለታ ወንዶ የቀለም ት/ቤት የተሠራው በብሎኬት ሲሆን የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት የከብቶች ጋጣ የመሰለና ጨለምለም ያለ ስለነበረ የዝቀተኛነት ስሜት ደግሞ ይሰማን ነበር። ብዙውን ጊዜ በዓመት ከ10 ተማሪ አንበልጥም ነበር።

በእርግጥ ከወላይታ መጥተው በመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት የሚማሩት አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ስለ ወላይታ ድርሻ በአስቸኳይ ለፊ ውይይት ጀመሩ። የሲዳማ ማህበር የወላይታ ወንጌላውያን ከእንግዲህ አያስፈልጉንም ብሎ ወስኖ ነበር። ይህንን የሰሙት የወላይታ ማህበር መሪዎች አብዛኛዎቹን የወላይታን ወንጌላውያን ከሲዳማ እንዲወጡ አድርገዋል። እኔ ከእነርሱ የማገኘው ደመወዝ ባለመኖሩ ያ ውሳኔያቸው እኔን የጐዳኝ አልነበረም። የዚያ ውሳኔ አፋጣኙ ውጤት ግን ት/ቤቱ ለሁለተኛ ጊዜ እንዲዘጋ አድርጓል።

## ለ4ኛ ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት

በሚያዝያ ወር በ1958 ዓ.ም ፒተርና ማሪዩን ክላሴን የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤትን ዳግመኛ ለመክፈት ወደ ወንዶ መጡ። የሲዳማ ማህበራት የመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጠናን ከምንም የበለጠ ትኩረት ሰጥተው እንዲከታተሉ ብዙ ነገሮችን አከናውነዋል።

ከቀለም ትምህርት የበለጠ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርትን መማር የሁሉም ክርስቲያኖች ትኩረትና ዓላማ መሆን አለበት በማለትና በዕድሜያቸውም ወጣቶች ያልሆኑ ሰዎች ወደ ቀለም ት/ቤት እንዳይሄዱ ተስፋ በማስቆረጥ እንዲያውም በሚስዮኑ የቀለም ት/ቤት እንዳይመዘገቡ ይከለክሉ ነበር።

ከመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ያልተመረቀ የቤተክርስቲያን መሪ ሲሆን እንደማይችል በማስተማር ይተጉ ነበር። በተጨማሪም የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት ያልተከታተለ ሁሉ ቤተክርስቲያንን መምራት እንደማይችል የሲዳማ ማህበራት መሪዎች መመሪያና ደንብ እንዲያወጡ በማሳሰብ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል።

ሚስተር ክላሴንና ሚስዮኑ ብዙ ገንዘብ በማውጣት በጣም ውብ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት በአለታ ወንዶ አሠርተዋል፣ የተሠራውም



የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ለክርስቲያኖች መንፈሳዊ ዕድገት አስፈላጊ መሆኑን ሁሉም ተገንዝቧል።

እኔም ዳግመኛ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ገባሁ። ፒተር ክላሴንንም ያገኘሁት ያን ጊዜ ነበር። ከነበረንም ግንኙነት የተነሳ ወንጌላዊ ሆኜ ወደ ከፋ ክፍለ ሃገር እንድሄድ ነገሮችን አመቻችተውልኛል።

በሚያዝያ ወር በ1960 ዓ.ም ሚስተር ግሬይና ባለቤታቸው ወንዶን ከመልቀቃቸው በፊት ፓውልና ላይላ ባስኪ በወንዶ የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ለመሥራት መጡ። ከዚያም እስከ ሐምሌ 1964 ዓ.ም ድረስ ቆይተዋል።

ከ1961-1963 ዓ.ም በተደጋጋሚ በመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት በማሳለፍ በ1964 ዓ.ም ተመርቄአለሁ። መጽሐፍ ቅዱስን በመማር የብዙ ሰዎች ሕይወት ሲለወጥ ከማየቴም በላይ፣ ቃሉን ተምሮ ለመጨረስ እንደሚይቻልም ለማስተዋል ችያለሁ።

## ከሚስዮኑ ጋር በጅማ

ከ1960-1961 በከፋ ወንጌልን ለመስበክ የሚያስችሉ ብዙ አጋጣሚዎች የነበሩ ይመስላል። የውጪ አገር ሚስዮናውያን የአገር ውስጥ ወንጌላውያንን ወደ ከፋ ክፍለ ሃገር ገብተው እንዲሰብኩ ይጠይቁ ነበር።

ከኤስ.አይ.ኤም ሚስዮናውያን በተለይም ሚስተር ክላሴንና ሚስተር ግሬይ ከሲዳማ ወደ ከፋ ወንጌላዊ ለመላክ ፈልገው ነበር። በወቅቱ ብሩስና አግነስ ሆል የሚባሉ ባልና ሚስት ሚስዮናውያንም እዚያ ነበሩ። ከሲዳማ ወደ ከፋ ለመሄድ ፍቃደኛ የሆነ አልነበረምና እኔ ሲዳማ ባልሆንም እንኳን ለመሄድ ፍቃደኛ መሆኔን ገለጽኩኝ። ምክንያቱም ከወላይታ ወደ ሲዳማ ስመጣ ጌታን እንደታዘዝኩ፣ አሁን ደግሞ ጌታ ከሲዳማ ወደ ጅማ የሚሄድ ሰው ሲፈልግም ሌላ ሰው ፈቃደኛ ባይሆንም እኔ መሄድ ነበረብኝ።

በዚያን ጊዜ ሚስተር ተድ ቪር የሚባል የኤስ.አይ.ኤም ሚስዮናዊ በጅማ ሃላፊ የነበረ ሲሆን፣ እኔ ጅማ በምደርስበት ጊዜ እርሱ ወደ ቦንጋ ሄዷል። ገና እንደደረስኩ ኤድ ጆንስ ከሚባለው ሚስዮናዊ ጋር ተገናኘሁ። እርሱና ባለቤቱ ማኪ ወደ ጂማ የገቡት በጥር ወር 1962 ዓ.ም ሲሆን፣ በመስከረም 1964 ዓ.ም ወደ ጉባ እስኪዛወሩ ድረስ በጅማ ለሁለት ዓመት ያህል ሠርተዋል። ሚስተር ጆንስ በተገናኘኝ ጊዜ በጣም ደስ አላቸውና ወደ ቦንጋ ለመሄድ እንደሚረዱኝ ገለጹልኝ።

እኔም ወደ ቦንጋ ደርሼ ለከፋ ሕዝብ ወንጌልን ለማድረስ የምችልበትን ቀን እጠብቅ ጀመር። ከውጪ አገር ሚስዮናውያን የከፋ ክፍለ ሀገር ሕዝብ ወንጌልን ለመስማት ምን ያህል መንፈሳዊ ጥማት እንደነበረው ለምቼ ነበር።

ወደ ቦንጋ ስሄድ ሚስተር ቴድ ቪርን ከቦንጋ ሲመለስ በመንገድ አገኘሁት፣ ስከፋ ሕዝብ ተልዕኮዬ መልካሙን ተመኝቶልኝ ወደየአቅጣጫችን ሄድን።

## ከሚስዮኑ ጋር በቦንጋ

ወደ ቦንጋ እንደገባሁ የግንኙነት መስመራችን የተቋረጠ መሆኑን ተገነዘብኩ ያለሁበት አገር ከሲዳማ እንደ ሰማይ በሆነ ርቀት በከፋ ክፍለ ሀገር ውስጥ ነው። እናም ማንም አልፈለገኝም።

ስሟን የማላስታውሳት ሚስዮናዊ ሴት የእኔን እዚያ መሄድ በስሜቷ አልወደደችም፣ ተደሳችም አልነበረችም። ሴትየዋ ለሁለትና ለሦስት ቀን በቤቷ በቁም እሥር እንደቆየችና በጣምም እንደፈራች እኔም እዚያ መስንበት ስደህንነቴ አስጊ መሆኑን ነገረችኝ። እዚያ አገር ወንጌልን እንዳልሰብክም አጥብቃ ለመነችኝ።

«እዚህ በቦንጋ ብዙ ችግር እየደረሰብን ነውና እባክህ ለማንም ወንጌልን አትስበክ፣ እዚህ በመቆየትህ ትንኮሳና ጠብ ለመጫር ምክንያት ትሆንብናለህ፣ ነገ ጧት በአውቶብስ ተሳፍረህ በቀጥታ ወደ ጅማ መሄድ አለብህ» ብላ ነገረችኝ።

እኔም በጉዳዩ በይበልጥ ሰመወያየት ነገ ጧት እመጣለሁ ብዬአት ሄድኩኝ። ሌሊቱን በአትክልተኛው ቤት እንዳድር ቦታ አመቻቸችልኝ። አትክልተኛውና ባለቤቱ ስለዚያች ሚስዮናዊ ሴት ባህርይ በስፋት ነገሩኝ። እኔም በጉዳዩ ከፀለይኩ በኋላ እንዳልሄድ ስመንኳት፣ እርሷ ግን ከውሳኔዋ የማትነቃነቅ ሆና በተቻለኝ ፍጥነት ከዚያ ወደ ጅማ እንድሄድ ነገረችኝ።

እኔም የበኩሌን ታሪክ ለመናገር ሞከርኩኝ «በእኔ ላይ ምንም ሃላፊነት እንዲሰማሽ አልፈልግም። ነገር ግን ወደ ሩቅ አካባቢ የሚመራኝ ሰው ፈልጊልኝ፣ የሚመጣውን ሁሉ እኔ እቀበላለሁ። በቦንጋ ስለማልቆይ ለእኔ አትጨነቂ ወደ ከፋ የመጣሁበት ዓላማ ወንጌልን ለመስበክ ስለሆነ ወደ ጅማ ከተማ ስመመለስ አልፈልግም» አልኳት።

ሴትየዋ በጽሞና እያዳመጠችኝ ፊቷን ስመለከት በቆመችበት ደርቃ ቀረች። «በዚያን ምሽት በአንድ የቤተክርስቲያን ሽማግሌ ቤት አደርኩኝ» ለረዥም ጊዜያት ስንወያይ ሌሊቱን አሳለፍን፣ ምን ማድረግ እንደምፈልግ በሚገባ ስሰውየው አስረዳሁት። ነገር ግን ሰውየው ያመጣው ለውጥ አልነበረም። ሚስዮናዊቷ ሴት የተናገረችውን ሃሳብ የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች በአንድ ድምፅ ደገፉ።

ሴትየዋ ሃሳብ ግትር ነበረችና የአካባቢ ቤተክርስቲያን መሪዎችም ሃሳባቸው ተመሳሳይ ሆነ። ሊረዳኝ የፈለገ ማንም አልነበረም። ሁሉም በተቻለኝ ፍጥነት



ወደ ጅማ እንድመለስ ይገፋፉኝ ነበር። በሃሳባቸውና በምክራቸው በጣም ተከፋሁ። ነገር ግን ሌላ ምርጫ ስላልነበረኝ ወደ ጅማ ለመመለስ ተገደድኩ፤ በቦንጋ ምንም ሳልሰራ አምስት ቀን ካሳለፍኩኝ በኋላ በአውቶቢስ ተሳፍሬ ወደ ጅማ ተመለስኩኝ።

## ወደ ጅማ መመለስ

በ1962 ዓ.ም በጅማ ከተማ ዙሪያ በገጠሩ አካባቢ ስድስት ትናንሽ ቤተክርስቲያኖች ነበሩ። በየማህበራቱ ውስጥ የነበሩት አብዛኞዎቹ ሰዎች አሮሚኛ ተናጋሪ ገበሬዎች ናቸው።

ወደ ጅማ እንደተመለስኩ ሚስተር ተድ ቪር ባየኝ ጊዜ በጣም ተስፋው ጨለመ። ያን ጊዜ ሚስተር ተድ ቪር የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ዳይሬክተር ነበር። ከሲዳማ ቤተክርስቲያን የተላክሁ እንደመሆኔ የአገር ውስጥ ወንጌላዊ ሆኜ ለዓመት እዚያ ክፍለ ሀገር መቆየት እንደነበረብኝ ስለሚያውቅ ወደ ሲዳማ ተመልሼ እንድሄድ አልፈለገም።

ስለዚህ በጅማ ለዓመት ያህል እንድሠራ ነገረኝ። እዚያው ከፀጋ የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ተማሪዎች ጋር እንዳድር መኝታ አዘጋጀልኝ። ምግቤንም ከተማሪዎቹ ጋር እንድመገብ አደረገ።

ቀን ቀን ተማሪዎቹ ወደየክፍላቸው ገብተው ይማራሉ፣ እኔም ወደ ስብከቴ እወጣለሁ። በጅማ ለአንድ ዓመት ሙሉ በየቀኑ ለስብከት እወጣ ነበር። ጥቂት ሰዎች ብቻ በኢየሱስ ክርስቶስ ቢያምኑም ተስፋ አልቆርጥም ነበር። አንዳንድ ጊዜ ትንንሽ ቤተክርስቲያኖችን ለመጐብኘት እሄዳለሁ። በዚያ ዓመት በኢየሱስ ክርስቶስ አምነናል የሚሉ ጥቂት ሴቶች ነበሩ።

ዛሬ በከፋ ክፍለ ሃገር የቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያን አስገራሚና ከፍተኛ የዕድገት ለውጥ እያሳየ ነው። በአንድ ዓመት በጅማ ቆይታዬ የዘራሁት የቃሉ ዘር መብቀል መጀመሩን ሰምቼ በጣም እደሰታለሁ።

አንድ ቀን ሚስተር ቪር እንዲህ አለኝ፡-

«ሶርሳ አንድ የምጠይቅህ ጥያቄ አለኝ፣ አንድ ጊዜ እንኳን መሪ ስጠኝ ብለህ ጠይቀኸኝ አታውቅም፣ ለምንድን ነው? ወደ ጅማ የሚመጡት ወንጌላውያን ሁሉም መሪ እንድሰጣቸው ይጠይቁኛል፣ መሪ የማትሰጠን ከሆነ ለብቻችን ወጥተን የምንሰብክበት መንገድ አይታየንም ይሉኛል» አለኝ።

እኔም መልሼ፣ «መንፈስ ቅዱስ ይመራኛል፤ ፀልዬ እወጣለሁ፣ የምገናኛቸውን ሰዎች መንፈስ ቅዱስ ያመጣልኛል። እኔም ወዲያው ወንጌልን እሰብካለሁ። መሪ ለምን እፈልጋለሁ?» አልኩት። እርሱም ፈካ ብሎ የደስታ ሳቅ ሣቀ።

በጅማ የሚኖሩ ሰዎች ከተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገራት እየሄዱ የኖሩ ናቸው:: በአካባቢው ሕዝቡ የሚነጋገረው ቋንቋ ኦሮሚኛ ቢሆንም እኔ ችግር አልገጠመኝም፣ ምክንያቱም በከተማው ሁሉም ሰው በአማርኛ መግባባት ስለሚችል ነው::

በጅማ ብዙውን ጊዜ ለሰዎች የማልታይ ስላደረገኝ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ:: ዘወትር በግሌ ወንጌልን ለመስበክ በከተማ ውስጥ በምዘዋወርበት ጊዜ ማንም ተቃውሞኝ አያውቅም:: ዓመት ሙሉ እዚያ ስቀመጥ ስብከቴን ለማቆም የሞከረም አልነበረም::

ሙስሊሞች የራሳቸው ሃይማኖት እንዳላቸው ይናገሩ ነበር:: ስለ እስልምና ሃይማኖታቸው ሲነግሩኝ በሚጀምሩበት ጊዜ በጽሞና አዳምጣቸዋለሁ:: ሃይማኖታቸው ስለ ምን እንደሆነ ግን በፍፁም አይገባኝም:: እኔ ግን በሲዳማ እሰብክ የነበረውን ተመሳሳይ ቃል በጅማም እሰብክ ነበር:: እያንዳንዱን መልዕክቴን በሚቻለኝ መንገድ በግልጽ ለማብራራት እሞክራለሁ::

አብዛኛውን ጊዜ ረዥም መልዕክት እንዳስተላልፍ ሰዎች ጊዜ አይሰጡኝም:: ዳሩ ግን በአጭር ጊዜ ውስጥ የወንጌልን መሠረታዊና አቢይ አስፈላጊነት እነግራቸዋለሁ::

በ1ኛ ቆሮ. 15፥3-8 ላይ፣ «እኔ ደግሞ የተቀበልሁትን ከሁሉ በፊት አሳልፌ ሰጠኋችው እንዲህ ብዬ፡- መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ፣ ተቀበረም፣ መጽሐፍም እንደሚል በሦስተኛው ቀን ተነሣ ለኬፋም ታየ በኋላም ለአሥራ ሁለቱ፤ ከዚያም በኋላ ከአምስት መቶ ለሚበዙ ወንድሞች በአንድ ጊዜ ታየ፤ ከእነርሱም የሚበዙቱ እስከ አሁን አሉ አንዳንዶች ግን አንቀላፍተዋል፤ ከዚያም በኋላ ለያዕቆብ ኋላም ለሐዋርያት ሁሉ ታየ፤ ከሁሉም በኋላ እንደ ጭንጋፍ ለምሆን ለእኔ ደግሞ ታየኝ::»

በሐዋ. ሥራ 4፥12 ላይ ደግሞ፣ «መዳንም በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና » ይላል::

የኤስ.አይ.ኤም ሚስዮን እጅግ ብዙ ትራክቶችን ያሳትም ነበር:: እኔም አንዳንድ ጊዜ ለሰዎች ትራክቶችን ባድልም የበለጠ በጣም አስፈላጊ የሚመስለኝ በአንደበቴ መናገር ነው:: ማንኛውንም ሥነ ጽሑፍ እየሸጥኩ ጊዜዬን አላባክንኩም፣ ምናልባት የሽያጭ ሥራን ለማከናወን የንግድ ፍቃድ ያስፈልገኝ ነበር::

የእኔ አቢይ ተግባር ሁልጊዜ ወደ ሰዎች ቤት እየሄድኩ በግልና በቡድን ለማገኛቸው ሰዎች ወንጌልን ማስተማር ነው:: በዚያን ዓመት በመቶዎች ብቻ ሳይሆን በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ወንጌልን ለመስማት ችለዋል::



በጅማ በነበረኝ አገልግሎቴ የምኖረውና የምዘዋወረው በከተማ ውስጥና አካባቢ ነው:: ምክንያቱም ወንጌልን በአማርኛ ቋንቋ ለማስራጨት ስለምችል ነው:: አንዳንድ ጊዜ ብቻ ወደ ገጠር እየሄድኩ ማህበራትን እጐበኛለሁ ነገር ግን ያ ጊዜዬን የሚሻማኝ አልነበረም::

በጅማ ቆይታዬ አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት አልተመሠረቱም ነበር፡ በመጨረሻ ግን ብዙ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ እንዳመኑና ጥቂት የማይባሉ ቤተክርስቲያኖች እንደተመሠረቱ ሰምቻለሁ::

## ወደ በንጋ መመለስ

በጅማ በነበርኩበት ዓመት መጨረሻ ላይ ብዙ ነገሮች ተሰውጠዋል:: በ1963 ዓ.ም አሌክስና ትሬሽያ ፌሎውስ ወደ በንጋ ተዛወሩ:: ሲሳው በፀጋ የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ዛሬም በማስተማር ላይ የሚገኙት ኤድ ጆንስ ወደ በንጋ ተመልሼ ወንጌልን እንድሰብክ መፈለጋቸውን ገለጹልኝ::

ከሚስተር ፌሎውስ ጋር እኔ ወደ በንጋ እንድመለስ ተስማሙ:: እዚያ ጅማ እንድቆይ የተወሰነልኝ ጊዜ ግን አልፏል:: ወደ በንጋ ስንዝ በአውቶቢስ ውስጥ ለሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል እናገር ነበር:: ከስብከቴ በኋላ ከተሳፋሪዎች መካከል አንዱ ከበደ የሚባለው ወደ እኔ መጥቶ «የት ይሄዳሉ?» ብሎ ጠየቀኝ::

«እኔ የመጣሁት ከሲዳሞ ክፍለ ሃገር ነው:: የተላክሁ ወንጌላዊ ነኝ:: በከፋ ክፍለ ሃገር ወንጌልን ለመስበክ መጥቻለሁ» አንተስ ማን ነህ? አልኩት:: እኔ የጤና ረዳት ነኝ የምኖረውም በከፋ ክፍለ ሃገር ጫና በሚባል ከተማ ውስጥ ሲሆን፣ የኢሉባቦር ክፍለ ሃገር ድንበር አጠገብ ነው:: በአካባቢው የፈንጣጣ ወረርሽኝ በመባመት ላይ በመሆኑ ክትባት ለማምጣት ወደ ጅማ መጥቼ መመለሴ ነው አለኝ::

እዚህ አካባቢ ወንጌል እንዲሰበክ እፀልይ ነበር:: እባክዎ አብረውኝ ለመሄድ ይፈልጋሉ? ሲል ጠየቀኝ:: «እኔም አስቀድሜ ለሚስተር ፌሎውስ ማሳወቅ እፈልጋለሁ:: ሃሳብህን ግን እደግፋለሁ» አልኩት::

ወዲያው ሄጄ በአውቶቢስ ውስጥ ያጋጠመኝን ለሚስተር ፌሎውስ ስነግራቸው፣ «ልጄ እግዚአብሔር ይባርክህ በፍጥነት ሂድ» አሉኝ:: ከበንጋ ወደ ተራራማው አካባቢ ሁለት ቀን ሙሉ በእግር መንዝ ነበረብን:: ከበደ የሚሠራበት ቦታ ጫና ለሚባለው ከተማ ቅርብ ነበር:: በደረስን ጊዜ በቀላሉ ሊቆጠር የማይቻል ሕዝብ የፈንጣጣን ክትባት በአንድ ቦታ ተሰብስቦ ይጠባበቅ ነበር:: እኔም አጋጣሚውን ተጠቅሜ በየቀኑ በመቶዎች ለሚቆጠር ሕዝብ ደጋግሜ ወንጌልን መስበክ ቀጠልኩኝ:: እያንዳንዱ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ

ለማመን ይፈልግ ነበር:: ለመጀመሪያ ጊዜ አራት ሺህ የሚያህሉ ሰዎች ክርስቶስን ተቀብለው ተመዝግበዋል::

## ወደ ከፋ እንድመለስ መጋበዜ

በአካባቢው የነበሩት ሰዎች ተመልሼ በመካከላቸው እንድኖርና ወንጌልን መስበኬን እንድቀጥል ጋበዙኝ:: ይህ የሚሆን ከሆነ ሁለት ነገሮችን ማድረግ አሰብኝ አንደኛ ከሲዳማ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ድጋፍ ማግኘት ነበረብኝ:: ምክንያቱም ከሲዳማ ወደ ጅማ የላኩኝ እነርሱ ስለነበሩ ካለ እነርሱ ፍቃድ በጅማ ለመኖር መወሰን ተገቢ ስላልሆነ ነው::

ሁስተኛ የጳውሎስን እናት /ባለቤቴን/ ከሲዳማ ወደ ጅማ ማምጣት አሰብኝ አልኩኝ::

ወዲያው ወደ ሲዳማ ተመለስኩኝ:: በዚያን ጊዜ በሲዳማ የቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያን ኘሬዚዳንት አቶ ኃይሉ ሐሜሶ ነበር:: ወደ ከፋ ክፍለ ሃገር ወንጌላዊ ሆኜ እንድሄድ የሚደግፍ መሆኑን፣ ነገር ግን የማህበሩ ሽማግሌዎች ውሳኔውን ማጽደቅ እንደሚገባቸው አቶ ኃይሉ አመላከተኝ::

የማህበሩ ሽማግሌዎች ከወር እስከ ወር ምንም መልስ ሳይሰጡኝ ቆየሁ:: በወሩ የማህበሩ ስብሳቢ ቦርድ ዘንድ ቀርቤ ወደ ከፋ እንድመለስ ድጋፍ እንዲሰጡኝ ጠየቅኳቸው:: በየወሩ የሚሰጠኝ መልስ:- «እየተነጋገርን ነው ቆይ፣ ምናልባት በሚቀጥለው ወር መልስ እንሰጥሃለን» የሚል ነበር:: በመጨረሻም ጥያቄዬን ከአጀንዳቸው ፍቀውት መልስ እንደነፈጉኝ የአብዮታዊ ንቅናቄ ለውጥ ገባ::

## መልካም ዜና ከከፋ

በተከታዮቹ ዓመታት ውስጥ ብዙ ሺ ሰዎች ክርስቲያኖች ሆኑ፣ አያሌ ቤተክርስቲያኖችም ተመሠረቱ:: አብሬአቸው ብሆንና እግዚአብሔር እየሠራ ያሰውን አገልግሎት ብካፈል በጣም እወድ ነበር:: ዳሩ ግን እኔ ወደ ከፋ ክፍለ ሃገር እንድመለስ የእግዚአብሔር እቅድ አልነበረም::

ሩት ክሬመር ከሚባሉት በከፋ ክፍለ ሃገር ስለ ቤተክርስቲያን ዕድገት ጥሩ ዜና ለምቻለሁ:: ፀልዩላቸዋለሁ፣ አብሬም የደስታቸው ተካፋይ ነበርኩኝ:: በምዕራብ ኢትዮጵያ እግዚአብሔር ስለሠራውና በመሥራትም ላይ ስላለው ታላቅ ሥራ አነስተኛ ተሳትፎ ለማድረግ በመቻሌ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ::



# በራስ መተማመን በያናሴ

በስሜናዊ ሲዳማ /በያናሴ/ አካባቢ የሚገኙት ክርስቲያኖች በአስታ ወንዶ የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት እየሄዱ መማር ነበረባቸው:: ይህ ሁኔታ በያናሴ አካባቢ የምንገኘውን ምዕመናን ሁሉ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም እንደምናገኝ ይሰማን ነበር:: ነገር ግን በአፋራራ የራሳችንን የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት በከፈትን ጊዜ ከሲዳማ አቢይ ማህበር ተነጥለን ራሳችንን በራሳችን የምናስተዳድር ማህበር ልንሆን ችለናል::

የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት እንደ ሚስዮን ጣቢያ ሆነልን:: ከስሜናዊ ሲዳማ አንዱ ከመሳው የሲዳማ ማህበር ቦርድ መሪዎችና ተወካዮች መካከል ነበር::

አቶ ኩማሎ የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት የሠራንበትን መሬት መስጠት ብቻ ሳይሆን በደቡባዊ ሲዳማ አብያተ ክርስቲያናት ዓይን እኩልነትን እንጐናጸፍ ዘንድ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጐልናል::

እኔ በመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት አስተምሬ አላውቅም፤ ለማስተማርም ፍላጐት የለኝም:: ዓስሙ ዳንቦዊ በመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ከሚያስተምሩት ሰዎች አንዱ ነው::

ዓስሙ ጥሩ አስተማሪና ጥሩ ወንጌላዊም ነው:: ለ30 ዓመት ያህል አስተማሪ ሆኖ አገልግሏል:: በስሜናዊ ሲዳማ ክፍል በእግሩ ወደ ላይና ወደ ታች እየተዘዋወረ ወንጌልን አሰራጭቷል:: አሁንም በታማኝነት ከሚያገለግሉ ስዎች መሐከል አንዱ ነው::

## የወላይታ ጉብኝቶች

በወላይታ ቢያንስ ሁለት ጊዜ የተራዘመ ጉብኝት አድርጌአለሁ:: አንጼ ኳየር ይዤ ሄጃለሁኝ:: ገንዘብ ለመቆጠብ ብለን የተጓዝነው በእግር ነበር:: የእኔ ዓላማ በአንዳንድ የወላይታ አብያተ ክርስቲያናት ለመዘመርና ቃሉን ለመስበክ ነበር:: እዚያም ለአንድ ወር ያህል የቆየን ይመስለኛል::

ከ1966-1983 በአብዮታዊው ለውጥ ወቅት በወላይታ ጥቂት ጉብኝቶች አድርጌአለሁ:: ጉብኝቶቼ በአስፈላጊው ወቅት ነበርና በአገልግሎቴ ጥቂት የረዳሁ ይመስለኛል::

ስምኦን ዳና የቅርብ ወዳጄ ነበር:: እርስ በርሳችን ስብዙ ዓመት እንተዋወቃለን:: ስለራሱ ሃሳብም እየተወያየን ብዙ ለዓቶችን አሳልፈናል:: የሚያስተምረውን ትምህርት ካለመረዳት የተነሳ በማህበራት አካባቢ ብዙ አለመግባባቶች ተፈጥረው ነበር:: እርሱም ሃሳቡን ካልተረዱት ሰዎች ጋር ሰላም ለመፍጠር ተግቶ በመሥራት ላይ መሆኑን አረጋግጦልኛል:: በሌላ

አጋጣሚ ታስሮ በነበረ ጊዜ በወላይታ ከአንዳንድ ቤተክርስቲያን መሪዎች ጋር በአገልግሎት ይሳተፍና ይረዳቸው ነበር።

የተወሰኑ ቡድኖች አቶ መርኪና መጃን አስረውታል። ያሰሩትም ምክንያት ሰዎችን እየሰበሰበ በእብዮታዊው መንግሥት ላይ ለማሳመጽ ያሴራል የሚል የውሸት ሴራ ነበር። በአውራጃ የነበረውን የፖለቲካ ሹም እውቅ ነበር። በአለታ ወንዶ ተማሪ በነበረ ጊዜ እኔ በግል እረዳው ስለነበር ከእርሱ ጋር ቀጠሮ ይዤ ስለ አቶ መርኪና መታሰር የሚያውቀው ጉዳይ እንዳለ ጠየቅኩት። እርሱም በፍፁም አልሰማሁም አለኝ። እኔም ሰዎች ያቀረቡበት ክስ ሁሉ የውሸት ክስ ነው አልኩት። እርሱም ከከሳሾቹ ጋር በቡና ቤት ተገናኝቶ ስለ ችግሩ አነጋገራቸው።

ከከሳሾቹ ጋር መነጋገር በጀመርን ጊዜ ሹሙን ጓደኛዬን በሰዎች ፊት መርኪና የታሰረበት ክስ ከፖለቲካ ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው መሆኑን በማስረዳት ለማሳመን ችያለሁ። ወዲያው ክሳቸውን በማንሳት ባለሥልጣኖቹ አቶ መርኪና ከእሥር እንዲፈታና ወደ ቤቱ እንዲሄድ አደረጉ።

## ከሲዳማ ምዕመናን ጋር የነበረው ችግር

ሚስተር ግሬይ ወንዶ በነበሩ ጊዜ ከሰሜናዊ ሲዳማ ማህበራት መሪዎች ጋር ከፍተኛ ጭቅጭቅ ነበረብኝ። ዋናው ምክንያት መጽሐፍ ቅዱስ የማይደግፈውን ተግባር እየሠሩ ስመለከት በዝምታ ማለፍ ስላልቻልኩ ነበር። እነርሱ ስህተታቸውን ይፋ እንዳላወጣባቸው ቢያስፈራሩኝም እኔ ግን የጉዳዩን አሳሳቢነት በማህበራት ስብሰባ ከማንሳት አልተቆጠብኩም።

አንድ ጊዜ በአብያተ ክርስቲያናት ማህበር ስብሰባ ላይ ከመሪዎች አንዱ የሆነ አቶ ጅፋሮ ተነስቶ፡- «ሁላችንም እንደምናውቀው በአዲስ መሬት ሥራ በምንጀምርበት ጊዜ ከጉረቤታችን በሬ ተውሰን እናርሳለን። አንዴ ማሳውን እርሰን ካለሰለስን በኋላ በሬ ገዝተን ራሳችንን እንችላለን። ከዚያም የተዋስነውን በሬ ለባለቤቱ እንመልስለታለን»።

በቤተክርስቲያንም ተመሳሳይ ተግባር ይከናወናል። አሁን እኛ አድገናል። የወላይታን ወንጌላውያን ወደ አገራቸው የምንልክበት ጊዜ አሁን ነው። ከእንግዲህ በኋላ እዚህ እንዲሠሩልን አንፈልግም አለ።

አቶ ጅፋሮ እኔን በስም ባይጠቅስም ሁሉም ሰው ግን ስለማን ለመናገር እንደፈለገ ያውቅ ነበር። ከዚያም ከወላይታ አብያተ ክርስቲያናት ሥራ አመራር ቦርድ ከእንግዲህ ወዲህ በሲዳማ ለመሥራት አይችልም የሚል ደብዳቤ ጽፈው ላኩ። እኔም ወደ ወላይታ ሄድኩ። ይህንን ትዕዛዝ የሚሽረውን ደብዳቤና ማረጋገጫ ከወላይታ ማህበራት ሥራ አመራር ቦርድ ማምጣት እንደሚገባኝ ገመትኩ። ወደ ወላይታ በመጓዝ ላይ እንዳለሁ በመንገድ ላይ



«በእውነት ሐዋርያው ጳውሎስ ሁለተኛውን የቆሮንቶስ መልዕክት በጻፈ ጊዜ የደረሰበት ተመሳሳይ ሁኔታ ነበር? በማለት በወቅቱ ጳውሎስ እንደተሰማው ተሰምቶኝ ነበር።» ወደ ወላይታ በደረስኩኝ ጊዜ አስቀድሜ ወደ ኦቶና ደርሼ ሚስተር ማክሊላንድ ከሚባለው ሚስዮናዊ ጋር ለመገናኘት ወሰንኩኝ።

እርሱም ደብዳቤውን አነበበ። በዚህ ጉዳይ ላይ እኔ ብዙም ልረዳህ አልችልም። ለቦርዱ አቅርብና የሚሉህን ከእነርሱ ብትሰማ ይሻላል አለኝ።

ወዲያው ወደ ቦርዱ ሄጄ ለቀጠሮ ተራ ያዝኩኝ ደብዳቤዬን ለመስጠት ስፈልግ አጣሁት፣ በፍፁም ለማግኘት አልቻልኩም። ትንሽ ቦርሳ በእጄ ይገር ነበርና የትም እንዳልጣልኩ አውቃለሁ። የት እንደጠፋ ባላውቅም ደብዳቤው ጠፍቶብኛል። ያ ደብዳቤ እንዳለኝ ሚስተር ማክሊላንድ አንብቦት ነበርና እርሱ እንዱ ምስክር ነበር። በኋላም በሃሳቤ ለቦርዱ መሪዎች የምናገረውን አሰላሰልኩኝ። «ሚስተር ማክሊላንድ ደብዳቤዬን አይቶታል። ደብዳቤ እንዳለኝ እርሱ ያውቃል። እባካችሁ መልሱን ለሰሜናዊው ሲዳማ ማህበራት ቦርድ ደብዳቤ ጻፉና አስታውቁልኝ» ብዬ ለመንኳቸው እነርሱ ግን ምንም አላደረጉልኝም።

የቦርዱ አባሎች ምንም ላለማድረግ ወሰኑ። ዳግመኛ ወደ ሲዳማ ተመልሼ ግልባጭ ደብዳቤ እንዳመጣ ነገሩኝ በጣም ግራ ተጋባሁ።

ወደ ሲዳማ እንደተመለስኩ፣ ሚስተር ግሬይን ለማነጋገር ወሰንኩኝ። እርሱም ተመሳሳይ ሁኔታ አጋጥሞት እንደነበረ በማውሳት ምክሩን ለገሠኝ። ለጆሮዬ የሚያስደስት ሳቁን እወድለታለሁ። መልሶም «ሶርሳ አንተና ባለቤትህ ወላጆቻችሁ በሕይወት አሉ?» ሲል ጠየቀኝ።

እኔም እርሷ እንደ እናቴ ነች፣ እኔም እንደ አባቷ ነኝ ብዬ መለስኩለት በመልሴም በጣም ሣቀ። ይህን ደብዳቤ የጻፉልህ የሲዳማ አብያተ ክርስቲያናት ማህበር መሪዎች ናቸው ወይስ የሰሜናዊ ሲዳማ ማህበር መሪዎች ብቻ ናቸው? እስቲ እንመርምር አለኝ።

የሲዳማ አብያተ ክርስቲያናት ማህበር ቦርድ አባላት ስለተጻፈልኝ ደብዳቤ በሰሙ ጊዜ በጣም ተቆጡ። ሌሎቹ ወደ ወላይታ እንድመለስ መሞከራቸው ለምን እንደሆነ ገብቷቸዋል። ለማህበሩ ስብሰባ የመጡት የሰሜናዊ ሲዳማ ማህበር ተወካዮች እኔን ወደ ወላይታ ለመመለስ ያሰቡትን ሃሳብ ለማንሳት ተሰማሙ።

ወዲያው ሌላ እንግዳ ነገር ተከሰተ። ወደ ቤት እንደገባሁ የጠፋብኝን ደብዳቤ በቦርሳዬ እጥፋት ውስጥ ተጠቅልሎ ገብቶ ኖሮ ቦርሳውን ሳራግፈው በመሬት ወድቆ አገኘሁት። ከዚያ ወዲህ መቼም ብዙ ዓመት አልፏል። በነዚያ

ዓመታት ውስጥ በሰሜናዊ ሲዳማ ብዙ ኪሎ ሜትሮችን በእግሬ እየተመላለስኩ ወንጌልን አሰራጭቻለሁ።

ብዙ ክርስቲያኖችም አዳዲስ ቤተክርስቲያን እንዲመሠርቱ ረድቻቸዋለሁ። እግዚአብሔር ወደ ወላይታ እንድመለስ ያልፈለገ ይመስለኛል።

# ክፍል ሦስት

# የማያወላውል አቋም

የክፍል አንድ ታሪኬ ወንጌልን ላልሰማ ለእያንዳንዱ ሰው ቃሉን እንድሰብክ ጌታ አምላኬ ስለሰጠኝ ራዕይ የሚያወሳ ነበር። በተጨማሪም ይህንን አገልግሎት ለማከናወን ስላስቻለኝ ጽኑ እምነትና ለመልካም ውጤት ያበቃኝን ልበ ሙሉነት ገልጨላችኋለሁ።

በመጨረሻው ታሪኬ ስለ ሦስተኛው የአገልግሎቴ አካል ልነግራችሁ እፈልጋለሁ። «አቋም» ይህ ማለት በግሌ ብዙ ሌላ ነገሮች ከመስራት ይልቅ አንድን ነገር ለመስራት የወሰንኩበት መሰረታዊ ምርጫ ማለት ነው። ይህንን ምርጫዬን ከወጣትነት ዕድሜዬ ጀምሮ እያከናወንኩ አለሁ።

## የጤና ባለሙያ

የኤስ.አይ.ኤም ሚስዮናውያን በወላይታ ለመኖር ከመመለሳቸው በፊት ሊጉበኙን መጡ። የወላይታን ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለመርዳት ሚስዮናውያኑ ካደረጉት ነገሮች አንዱ የቤተክርስቲያን አካሎችን በተሻለ መንገድ ማደራጀት ነበር።

ቤተክርስቲያን በአስራ አምስት ክፍሎች መደራጀት እንዳለባት ሃሳብ ያቀርቡ ነበር። ይህንን ለማድረግ ያነሳሳቸው ዋናው ምክንያት በቤተክርስቲያን አንድና ሁለት ሰዎች ብቻቸውን ከሚመሩ ብዙ ሰዎች የመሪነት ድርሻ እንዲኖራቸው ለማድረግ ነው።

በ1937 ዓ.ም የኢትዮጵያ መንግሥት ለኤስ.አይ.ኤም ሚስዮን በኦቶና ሆስፒታል እንዲሰሩ ፈቀደ። ከመንግሥት ጋር የነበራቸው ውል የጤና ባለሙያዎችን ለማስልጠን ነበር። የጤና ባለሙያዎቹም ከሰለጠኑ በኋላ በዚያው ሆስፒታል ውስጥ ይሰሩና ልምድ አካብተው ወደ ገጠር አካባቢ በመሰማራት ለሕዝቡ የጤና አገልግሎት ይሰጣሉ። የውጭ አገር ሚስዮናውያን ስለሚሰጥኑት ሰዎች ከቤተክርስቲያን መሪዎች ጋር ይነጋገሩ ነበር።



የቤተክርስቲያን መሪዎችም የመጀመሪያዎቹን አምስት ሰዎች መርጠው ለጤና ባለሙያነት ስልጠና እንዲያቀርቡ ተወሰነ። የመጀመሪያዎቹ አስራ አምስት ለልጣኞች ከአስራ አምስት ክፍለ ማህበራት ውስጥ ከምትገኝ ቤተ ክርስቲያን አንድ አንድ ሰው እንዲመርጡ ወሰኑ።

የዱጉና ወረዳ ቤተክርስቲያን መሪዎች በስብሰባቸው ላይ እንድገኝ ጠሩኝና፦ «ሶርሳ ሱማሞ በሚስዮኑ ሆስፒታል ውስጥ ዶክተር ናታን ባርሎ የሚሰጡትን የጤና ባለሙያነት ስልጠና እንድትወስድ መርጠንሃል። ስልጠናው ሁለት ዓመት ያህል ይፈጅብሃል። ከዚያም በሆስፒታል ውስጥ ትሰራለህ» አሉኝ። እኔም «አመሰግናለሁ በጉዳዩ እንድፀልይበት ጊዜ ስጡኝ። ሌሎች ሰዎችንም አማክሬ ሐሳባቸውን እቀበላለሁ፣ በሁለት ሳምንት ውስጥ መልስ እሰጣችኋለሁ» አልኳቸው። በሰጠኋቸው ምላሽ ተደንቀው ለመቆየት ተስማሙ።

## ሁለት መንገዶች

ወደ ኦቶና ሰመንዝና ሚስስ በርገስተን የሚባሉትን ሴት ሚስዮናዊ ለማነጋገር ወሰንኩኝ። በዚህ ጊዜ የምሻውን ምክር ይሰጡኛል የሚል ስሜት አደረብኝ። ወዲያው ወደ ኦቶና ደረስኩና ለሚስስ በርገስተን ፦

«እግዚአብሔር የጠራኝ ወንጌላዊ እንድሆን ነው ብዬ ንግግሬን ጀመርኩ። ወንጌልን ላልሰሙት ማሰማት እንደሚገባኝ ከማውቀው ውጪ ጥሪው ምን እንደሆነ አላውቅም። የት እና እንዴት እንደማከናውንም አላውቅም። የዱጉና ወረዳ ቤተክርስቲያን መሪዎች በዶክተር ናታን ባርሎው የሚሰጠውን የጤና ባለሙያዎች ስልጠና እንድወስድ መርጠውኛል። ምናልባት በዚሁ መንገድ የወንጌል ሰባኪ ለመሆን እችል እንደሆን አላውቅም። ይህንን የጤና ባለሙያነት ስልጠና ለመውሰድ ፍቃደኛ ከሆንኩ እግዚአብሔር የሰጠኝን ጥሪ እንዳላከናውን ግጭት ይፈጥርብኝ ይሆን? » አልኩኝ።

ሚስስ በርገስተን ፈገግ ብለው «ሶርሳ እግዚአብሔር የጠራህ ምን ልታደርግ ነው?» አሉኝ። እኔም መልሼ «እግዚአብሔር የጠራኝማ ወንጌልን ላልሰሙት ሰዎች እንድሰብክ ነው»አልኳቸው።

እርሳቸውም «በሆስፒታል መስራት በጣም አስፈላጊ ነው። በወላይታ ብዙ ሕዝብ የሕክምና እርዳታ ይፈልጋል። በሆስፒታል የሚሰሩ ሰዎች ሁልጊዜ ስራ የሚበዛባቸው ናቸው። በሽተኞችን እያነጋገሩ ብዙ የሕክምና ተግባር ስለሚያከናውኑ ወንጌልን የሚሰብኩበት ጊዜ አይኖራቸውም። በእርግጥ በሆስፒታል ብትሰራ ገንዘብ ይከፈልሃል። ወንጌላዊ ወይም ሰባኪ ብትሆን ብዙ ገንዘብ አይኖርህም። ነገር ግን እግዚአብሔር ወንጌላዊ እንድትሆን እስከጠራህ

ድረስ ከጤና ባሰሙያነት ስልጠና ይልቅ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት መግባትን መምረጥ አለብህ» አሉኝ፡፡

ሐሳባቸው ትክክል መሆኑን በልቤ አውቃለሁ፡፡ ሰጤና ባለሙያነት ስልጠና ወደ ሆስፒታል ከመሄድ ይልቅ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ለመግባት እፈልግ ነበር፡፡ ከሁለት ሳምንት በኋላ ለዱጉና ወረዳ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች «እግዚአብሔር አንድ ስራ ሰጥቶኛል፤ ሌላ ስራ መደረብ አልችልም» አልኳቸው፡፡ እጅግ በጣም ጥሩ የሆነ እድል እንዳመለጠኝ ነግረውኝ ያንን ዕድል ለሌላ ሰው ሰጡ፡፡ ከሁለት ወር በኋላ ሚስተር አህማን ወደከፈቱት የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ገባሁ፡፡ ከሁለት ዓመት በኋላም ወንጌላዊ ሆኜ ወደ አንድ ቦታ ለመሄድ ተዘጋጀሁ፡፡

# ምዕራፍ አስር

## ዋጮ

ዋጮ አንድ ትንሽ መንደር ሲሆን ችብችብ ያሉ ቤቶች የሌሉበት አካባቢ ነው፡፡

## ሁለተኛ ሙከራዬ

በአቶና የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ሰባኪ ስለመሆን ምንም አልተማርኩም፡፡ ጣሊያን ወደ ሀገራችን በገባ ጊዜ የኤስ.አይ.ኤም ሚሲዮናዊያን ስራቸውን እንዴት እንደሚያከናውኑ ወይም እንደሚያካሂዱ ሰምቻለሁ፡፡ ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወሩ ብዙ ጊዜ እንደሚያሳልፉ አውቃለሁ፡፡

በወላይታ ውስጥ ደግሞ የመጀመሪያዎቹ አማኞች ለሳምንትና ለወር ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወሩ እንደሚሰብኩ አውቃለሁ፡፡ በሰሜናዊ ሲዳማ ግን ምን ማድረግ እንደሚገባኝ የሚነግረኝ አልነበረም፡፡ እኔ የምሰራውን ተመሳሳይ ስራ የሚሰራ ማንም አልነበረም፡፡ የሚሰራው መንፈስ ቅዱስ ፤ ቃሉና እኔ ነበርን፡፡ የእውነትን ቃል ከሰበክሁ በኋላ ዘሩ መብቀል በሚችል ቦታ እንደሚወድቅ ፅኑ እምነት ነበረኝ፡፡

## ዳግም መስፈር? ለምን?

በዋጮ ዳግመኛ የሰፈርኩበት ምክንያት በአካባቢው ለሚኖሩት ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ለመስበክ ስለምፈልግ ነው፡፡

በአንድ ቦታ ረግቼ እያስተማርኩ ክርስቲያኖችን እያበረታታሁ የምቀመጥ አለመሆኔን አውቅ ነበር፡፡ በአርኬ ቆይቼ ቢሆን ኖሮ አዳዲስ ምዕመናንን ለብዙ ጊዜ ለመርዳት እችል እንደነበር ለመገንዘብ ችያለሁ፡፡ከልምዴ



እንደማውቀው ክርስቲያኖች ለብቻቸው እንዲሰሩ ቢተዉ የበለጠ በፍጥነት እንደሚያድጉ ተረድቻለሁ፡፡

ምናልባት የበለጠ አስፈላጊ የሚሆነው ስራቸው መሆኑንና የእኔ ሥራ አለመሆኑን ሲረዱ ከዚያ አገልግሎትም ሙሉ ሀላፊነት የሚሰማቸው መሆኑን ሲገነዘቡ ነው፡፡እኔ ወንጌላዊ ስሆን እነርሱ የቤተክርስቲያን ተካዮች ናቸው፡፡

በዚያን ጊዜ የሰብከት አገልግሎቴን ለማከናወን በአንድ ቦታ ተቀምጬ ከዚያ እየወጣሁ ለመስበክ ትኩረት አልሰጥም ነበር፡፡ያ ዘዴ የመጣልኝ በአርኬ ቋሚ ቤት ሰርቼ በተቀመጥኩበት ጊዜ ነበር በአርኬ ቤት ሰርቶን እርሻ ማረስ በጀመርን ጊዜ እዚያ ለመቆየት እቅድ አልነበረንም፡፡

## አርኬ ካሉት ጋር መገናኘት

የመኖሪያ አቅጣጫ መለወጥ ማለት በአርኬ ካሉት ክርስቲያኖች ጋር እንዳንገናኝ አላደረገንም፡፡ ዋጮ ከአርኬ የአንድ ሰዓት ተኩል ያህል ብቻ በእግር ያስኬዳል፡፡

ስለዚህ በየጊዜው ለአገልግሎትና ለቤተክርስቲያን ጉዳዮች ከዋጮ ወደ አርኬ እመላለሳለሁ፡፡ ስለዚህ ከአርኬ ክርስቲያኖች ጋር የቅርብ ግንኙነት አለን፡፡

ነገር ግን በአርኬ ያሉት ምእመናን በማንኛውም መንገድ እኔን ለማማከር ግዴታ አልነበራቸውም፡፡ ለራሳቸው ጉዳይ የራሳቸውን ውሳኔ ይወስናሉ፡፡ በየሳምንቱ እሁድ ምዕዋት ይሰበስባሉ፡፡ ገንዘቡን እንዴት እንደሚጠቀሙበት እራሳቸው ይወስናሉ፡፡ዋና አስፈላጊው ነገር በህብረተሰቡ መካከል ወንጌልን መስበካቸውና በቤተክርስቲያን ውስጥም ማስተማራቸው ነበር፡፡

## ለምን ዋጮ?

ወደ ዋጮ ለመሄድ ባቀድኩ ጊዜ እዚያ ምንም ክርስቲያኖች አልነበሩም፡፡ ወደዚያ ከመዛወሬ አስቀድሜ በአካባቢው ደጋግሜ እየተመላለስኩና እየሰበክሁ እንደነበኘሁት፣ ወንጌልን መስማት የሚገባቸው ብዙ ሰዎች እንዳሉ አውቃለሁ፡፡ እና እዚያ ሄጄ ለመስበክ ከፍተኛ ፍላጎት ነበረኝ፡፡

እዚያ እንድሄድ ማንም አላሳሰበኝም፤ ለመሄድም ምንም ራዕይ አልነበረኝም፡፡ ነገር ግን እዚያ ለመሄድ ትክክለኛ ጊዜ መሆኑ ተሰምቶኝ ወዲያው ለመዛወር አቀድኩኝ፡፡ በአርኬ ላሉት ምእመናን ሀሳቤን ሳካፍላቸው በጣም ደገፉኝ፡፡ በተዛወርንም ጊዜ ሁሉ ነገር የተሳካ እንዲሆንልኝ ተባብረውኛል፡፡ በአርኬ ካሉት ምዕመናን መካከል ለዋጮ ታዋቂ የሆነ ሰው አቶ ሆርዶፋ ብቻ ነበር፡፡ እርሱም ወደ ዋጮ እንድዛወር ፍላጎት እንዲያድርብኝ ምክንያት ሆኖልኛል፡፡ ያም ምናልባት የእግዚአብሔር ዕቅድ

ስለሆነልኝ ይመስለኛል። ሆርዶፋ በዋጮ ብዙ ሰው ስለሚያውቅ አስፈላጊ ሁኔታዎችን አመቻችቶልኛል።

ቤት የምሰራበትን መሬት የሚሰጠኝን ሰው አግኝቶልኛል። እኔም የእርሻን መሬት እፈልግ ነበር። የሚከራይ መሬት ከተገኘ ከባለመሬቱ ጋር ምርቱን እኩል ለመካፈል መዋዋል ያስፈልጋል። በዚያን ጊዜ መሬት ለመጠቀም ገንዘብ አይከፈልም።

በዋጮ አካባቢ ወንጌልን ለመስበክ በምዘዋወርበት ጊዜ ሆርዶፋ አብሮኝ ይሄዳል። በአርኬ አካባቢ ካሉት የበለጠ በዋጮ ያሉት ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ ለማመን የቀና ልብ ያላቸውና የተዘጋጁ ናቸው።

አሁንማ በሲዳሚኛ መስበክ ችያለሁ። ባህሉንም አውቄአለሁ። ስራዬን በተመለከተ የተለወጠ ነገር የለም፤ አሁንም ከቦታ ወደ ቦታ የምዘዋወር ሰባኪ ነኝ። ቀዝር በሚኖርበት ጊዜ በቀጥታ ወደዚያ እሄዳለሁ። ሰዎች እርሻቸውን በሚያርሱበት ጊዜ ወይም እህላቸውን በሚያጭዱበት ጊዜ ቆም እንላለን። ሰዎች ሲዘምሩ እንሰማለን ዝማሬያቸውን ስንሰማ በህብረት እያረሱ መሆናቸውን እናረጋግጣለን ወዲያው ወዳሉበት ሄደን እንሰብካለን።

በየትም ሰፈር ስንዘዋወር ክፍት ቤት ካገኘን «እዚህ ቤት» ብለን እን ጣራለን። በሩ ክፍት ከሆነ ሰዎች በቤት ውስጥ አሉ ማለት ነው።ሴቷ ምግብ ታዘጋጃለች፣ ሽማግሌዎች በአረፍት ላይ ሲሆኑ ይችላሉ፣ የታመመ ሰው በቤት ውስጥ ሊኖር ይችላል። ያን ጊዜ ገብተን እንፀልይላቸዋለን፣ ቃሉንም እንሰብካለን። ሁሉም በደስታ ያስተናግዱን ነበር።

በአካባቢው ወንጌልን እየሰበክን በምንዘዋወርበት ጊዜ ለመጀመሪያ የተገናኘን ሰው ኦሮሞ ይባላል። እርሱም በእርሻው የተዋጣለትና እጅግ ብዙ ከብቶች ያሉት ነው። በሲዳማ የአንድ ሰው ሀብት የሚለካው በከብቶቹ ብዛት እንጂ በጥሬ ገንዘብ ከምችት አልነበረም።

ኦሮሞ ለመጀመሪያ ስናገኘው ቤት ይሠራ ነበር። በባሕሉ መሠረት ሰጥቂት ሰዓቶች በስራው እናግዘዋለን፣ ያም እርስ በራሳችን የበለጠ እንድንተዋወቅ ረድቶናል።

## ቤት መስራት

እንደ ሌላው የገጠሩ ኢትዮጵያ ሕዝብ በሲዳማም ቤት የሚሠራው በህብረት ነው። በአካባቢው የሕብረተሰቡ አካሎች ማንኛውንም ሥራ በህብረት ይሠራሉ።

የቤት ግንባታ ቦታ ለእኔ ወንጌልን ለመስበክ ፍፁም የሚስማማኝ አጋጣሚ ነው። በአንድ ጊዜ ምናልባት ከሀያ የማያንሱ ሰዎች ተሰብስበው የቤቱን



ግንባታ ያከናውናሉ።በስራቸው አይጣደፉም፣ ተረጋግተው በመስራት ለመጠጥ ረዘም ያለ ሰዓት ይወስዳሉ። ያ ለእኔ ቃሉን ለመስበክ ጥሩ አጋጣሚ ይፈጥርልኛል።

ለኦሮሞ ወንጌልን የሰበክሁት ለመጀመሪያ በዚሁ ዓይነት ሁኔታ ነበር።ሰዎች ቃሉን በሰሙ ጊዜ ይቅርታ ምን እንደሆነ ይገነዘባሉ። ሰዎች በሰይጣን ፍርሀት የታሰሩ በመሆናቸው በኢየሱስ ክርስቶስ ብታምኑና ሰይጣንን ብትክዱ ለኃጢአታችሁ ይቅርታ ታገኛላችሁ ብዬ እነግራቸዋለሁ። እያንዳንዱ ሰው በእውነት ከኃጢአት እስራት መፈታት ይፈልጋል። ዋናው ጥያቄ ያንን ኃላፊነት ማን ይሸከማል? የሚል ነው። ሁሉም እንደሚገነዘቡት የብዙዎቹ ሰዎች አማራጭ አሁን በሰይጣንና በኃጢያት እስር ውስጥ ነኝ፣ ቢሆንም ቶሎ የሚገድለኝ አደጋ ውስጥ አይደለሁም። ነገር ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ካመንኩኝ ደግሞ ሰይጣን በጣም ጠንካራ ስለሆነ በእኔ ላይ ቁጣውን ያወርድብኛል። እኔና ቤተሰቤን ከብቶቼንም ሁሉ ሊገድልብኝ ይችላል ብለው ይሰጋሉ።

በዚያን ዕለት ይሁን ወይም በሌላ ጊዜ በትክክል በማላስታውሰው ጊዜ ኦሮሞ ከመላው ቤተሰቡ ጋር በኢየሱስ ክርስቶስ አመነ።

## ከመጀመሪያዎቹ አማኞች አንዱ

እንደ ብዙዎቹ የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ኦሮሞም ካመነበት ቀን ጀምሮ ከእምነቱ የማይነቃነቅ ጠንካራ አማኝ ነበር። ባለቤቱም ትጉህ አማኝ ነበረች። ነገር ግን ብዙም ሳትቆይ ታማ ሞተች፤ ልጆቻቸውም በሙሉ በክርስቶስ አምነዋል።

የኦሮሞ ቤተሰብ በቂ ገንዘብ ስላላቸው ልጆቻቸውን በተለያዩ የንግድ ዘርፎች አሰማርተዋቸዋል። እንዳንዶቹ ልጆች በእምነታቸው አልዘለቁም።

## በዋጮ እርሻ ማረስ ጀመርን

ኦሮሞ ቤት የምሰራበትንና በቆሎ የምዘራበትን መሬት ሰጠኝ። በአርኬ ከሚገኘው እርሻዬ ምርት ስለምሰበስብ ወደ ሌላ አካባቢ ብዛወርም እንኳን ከቀድሞ እርሻዬ በቂ እህል አገኛለሁ።

በእያንዳንዱ ህብረተሰብ ሰዎች የከብት መንጋዎቻቸውን በአንድነት ያሰማራሉ። የእኛንም ከብቶች ከሌሎች ሰዎች ከብቶች ጋር አቀላቅለን እናሰማራለን፤ ተራችን ሲደርስም የሁሉንም ከብቶች እኛ እናግዳለን።

ኦሮሞ ለእርሻ በሰጠኝ መሬት ላይ ጎመንና የስኳር ድንች ተክልኩበት። በዚያ አካባቢ የቡና ዛፍ ፍሬ እስከሚሰጥ ከሦስት ዓመት በላይ ስለሚቆይ ቡና መትከል የተለመደ አይደለም።

ነገር ግን አሮሞ የቡና ዛፍ እንድተክልበትና ከዋጮ ብሄድ እንኳን ፍሬውን መልቀም እንደምችል ነግሮኝ ፈቀደልኝ:: በአርኬ ተክለን የመጣነው እንሰት ስላለን በጥሬ ገንዘብ ምግብ አንሸምትም::

ዋነኛው የገቢ ምንጫችን ከእርሻችን የምናገኘው ሰብልና ከብቶቻችን ናቸው:: በዋጮ በነበርኩ ጊዜ የሲዳማ ማህበር ቦርድ ጥቂት ገንዘብ ይሰጠኝ ነበር:: ነገር ግን ከወላይታ የማገኘው ገንዘብ አልነበረም::

በትክክል ካስታወስኩኝ በዚያን ጊዜ አያሌ የወላይታ ወንጌላውያን ወደ አገራቸው ለመመለስ የወሰኑበት ጊዜ ነበር:: ምክንያቱም እንደሚመስለኝ እኔ በሰሜናዊ ሲዳማ ለመስራት በመወሰኔ የሲዳማ ማህበር ቦርድ በየወሩ ትንሽ ትንሽ ገንዘብ ስለሚከፍለኝ ተሰምቷቸው ሊሆን ይችላል::

## ክርስቲያኖች ቤተ ክርስቲያንን ይመሰርታሉ

በየቀኑ ወንጌልን ለመስበክ በአካባቢው በምዘዋወርበት ጊዜ ሰዎች የእውነትን ቃል ሰምተው በኢየሱስ ክርስቶስ ያምናሉ:: ለሰዎች ወጣ ብዬ መስበክ በመቻሌ ትልቅ እርካታን አግኝቻለሁ:: አንድ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በሚያምንበት ጊዜ እኔም ከሰማይ መላእክት ጋር አብሬ እደሰታለሁ::

"እንዲሁም ንስሐ ከማያስፈልጋቸው ከዘጠና ዘጠኝ ጻድቃን ይልቅ ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በሰማይ ደስታ ይሆናል" (ሉቃስ 15:7)

የሰሜናዊ ሲዳማ ማህበራት በጨቅላ እድሜ ውስጥ ነበሩ፤ የቤተክርስቲያን መሪዎች ወንጌላውያንና የማህበራቱ ተወካዮች በየወሩ ይሰበሰባሉ:: አሮሞንና ሌሎቹን ክርስቲያኖች ወዲያው በክርስቶስ እንዳመኑ ወደዚያ ስብሰባ እወስዳቸው ነበር::

ወዲያው ከቤተክርስቲያን አገልግሎት በፊት የማህበሩ አባሎች ይሆናሉ:: በእኔ እምነት ማመንና የክርስቶስ መሆን ሁለቱም የተያያዙና የማይነጣጠሉ ናቸው:: በጊዜው መጠመቅ ማለት የበለጠ የቤተክርስቲያን አካል መሆን ማለት ነው::

አሮሞ ትልቅ የሆነ የሲዳማ ባህላዊ ቤት ነበረው:: እኛም በቤቱ ውስጥ በየሳምንቱ ሐሙስ ጠዋት መሰብሰብ ጀመርን:: ተጨማሪ ሰዎች እስኪያምኑ ድረስ እርሱና እኔ ወደ አርኬ እየሄድን እናመልክ ነበር:: በየሳምንቱ ግን ተጨማሪ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ እያመኑ በየሐሙስ ጠዋት ስብሰባችን ላይ መብዛት ጀመሩ::

ከጥቂት ጊዜ በኋላ የራሳችንን ፀሎት ቤት መስራት ቻልን:: ዋጮ በገባን በዓመታችን የመጀመሪያውን ቤተክርስቲያን መሰረትን:: ዛሬ በአካባቢው ብዙ ወንጌላውያን አሉ:: አዳዲስ ክርስቲያኖች ሁሉም ለጎረቤቶቻቸውና



ለጓደኞቻቸው ቃሉን ይሰብኩ ነበር:: ብዙዎች ወንጌልን ሲሰብኩ ብዙ ሰዎች ያምናሉ:: ስለዚህም የዋጮ ቤተክርስቲያን ትልቅ ሆኗል::

## የክርስቲያን ቤት?

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የማምለኪያ ቦታቸውን ቤተክርስቲያን ብለው ይጠራሉ:: በሲዳማ ክርስቲያኖች እንደሌላው የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገር የራሳቸውን ማምለኪያ ቦታ የፀሎት ቤት ብለው ይጠራሉ::

## (የተርጓሚው ማብራሪያ)

«የእግዚአብሔር ቃል እንደሚያስተምረን ቤተክርስቲያን ማለት ሰዎች ተሰብስበው የሚያመልኩበት ሕንፃ ማለት አይደለም:: ቤተክርስቲያን ማለት ክርስቲያኖች ራሳቸው ናቸው:: አንድ ክርስቲያን የቤተክርስቲያን አካል ነው::

በሐዋ. ሥራ 14:27 ላይ «በደረሱም ጊዜ ቤተክርስቲያኑን ሰብስበው .......» ይላል፣ የሰበሰቡት ክርስቲያኖችን እንጂ ህንፃውን እንዳልሆነ ግልፅ ነው::

በሐዋ ሥራ 15:3 «ቤተክርስቲያኑም በመንገድ እየረዳቸው ......» ይላል፤ ይህም የሚያመለክተው ክርስቲያኖቹ እንደረዱዋቸው ነው:: በተጨማሪም ቤተክርስቲያን በክርስቶስ ደም የተዋጀች ነች የሐዋ. ሥራ 20:28 ያንበቡ»::

አምልኮት የሚለውን ቃል ስሐሙስ ጧትና ለእሁድ ስብሰባ አይጠቀሙም::ሁል ጊዜ የፀሎት ጊዜ ነው ብለው ያምናሉ:: ያም ከእግዚአብሔር መገናኘትና ድምጹን መስማት ማለት ነው:: ዝማሬ ፀሎት ነው፣ ቃሉን መስበክም የፀሎት አካል ነው::

የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን እምነት ተከታዮች የሚያመልኩበት የተለየ ህንፃ አላቸው:: ተከታዮቻቸውም ወዲያው በፍጥነት ለየት ያለ ሕንፃ ያስገነባሉ::

የአሮሞ ቤት ለእኛ ቅርብና ምቹ የህብረት እና የአምልኮ ቤት ነበር:: ነገር ግን የፀሎት ቤት ብለን አንጠራውም:: በሌሎቹ የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገራት እንደሆነው ሁሉ የሲዳማም ሰዎች ትልቅ ቤት አስፍተው ስለሚሰሩ እንደ አመቺነቱ እሁድ እሁድ ለመሰብሰብ ይጠቀማሉ::

በሲዳማና በወላይታ የሚገኙ ክርስቲያኖች ግን የማምለኪያ ቦታ ቤተ ክርስቲያን የማለት ልምድና ፍላጎት የላቸውም:: ነገር ግን እግዚአብሔርን የሚያመልኩበት ቦታ ለሁሉም አስፈላጊ እንደሆነ ያምናሉ::

## የመጀመሪያ ጥምቀት በዋጮ

በዋጮ ስራ ጀምረን ዓመት እንደቆየን አሮሞና ቤተሰቡ ከመጀመሪያዎቹ ተጠማቂዎች መካከል ነበሩ። የጥምቀት ሥነ–ሥርዓት በየወቅቱ በሰሜናዊና በደቡባዊ ሲዳማ ይካሄድ ነበር።

በማንኛውም ጊዜና ቦታ ጥምቀት ይኖራል ከተባለ መጠሙቅ የሚፈልጉ ሁሉም ሄደው ስለ ጥምቀት የሚቀርብላቸውን ቃለ መጠይቆች ካለፉ ይጠመቃሉ። የዋጮ አካባቢ ጥምቀት የት ቦታ እንደነበር ባላስታውሰውም ምናልባት በሼሎ አካባቢ በነበረው ትንሽ ወንዝ አጥምቀው ይሆናል ብዬ እገምታለሁ።

## የስብከት ቀደምትነት

በሰሜናዊ ሲዳማ የተገናኘሁአቸው ሰዎች ክርስቲያኖች ሊሆኑ የቻሉት ወንጌል ስለተሰበከላቸው ነው። በሕልምና በራዕይ በኩል ተነግሮኝ በኢየሱስ ክርስቶስ አመንኩ የሚል ሰው አይታወሰኝም።

የእግዚአብሔር ኃይል የሰዎችን ህይወት የሚለውጠው ቃሉ ተሰብኮላቸው ሲያምኑ ነው።ሰዎች በክርስቶስ የሚያምኑት ወንጌል ተሰብኮላቸው ነው።ምናልባት ከሌሎች ብዙ ቦታዎች የተሻለ በሲዳማ የህይማኖት ጉዳይ ግልፅ በመሆኑ፣ ሰዎች የምንሰብከው ስብከት ምን እንደሆነ መልእክቱን ለመረዳት ችግር አልነበረባቸውም።

በመንፈሳዊ ህይወት እንዲኖሩ ያደረጋቸው እግዚአብሔር እንጂ በዘር ሐረግ ተያይዞ የመጣ አለመሆኑን እንነግራቸዋለን። መፍራት የሚገባቸውም ሰይጣንን ሳይሆን የሁሉ ፈጣሪ የሆነውን እግዚአብሔርን ብቻ ነው።በቀድሞ ህይወታቸው መኖር የሚቀጥሉ ከሆነ የሰይጣን ባሪያዎች ሆነው እንደሚቀሩም እንነግራቸው ነበር።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝ መሆኑን እናስተምራለን። ኢየሱስ ክርስቶስ የሰይጣንን ኃይል በሞቱና በትንሳኤው ድል እንዳደረገው እናበስራለን።ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአታቸውን ሁሉ ይቅር እንደሚላቸው እንነግራቸዋለን። ስለዚህ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው ከሰይጣንና ከፍርድ ያመልጡ ነበር።

በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑበት ምክንያት የሚያድናቸውና አዲስ ህይወት የሚሰጣቸው እርሱ ብቻ ስለሆነ ነው። ኑሮ በሲዳማ ቀላል አልነበረም። በእያንዳንዱ ሰው ውስጥ መንፈሳዊ አመለካከት ሊገመት የማይቻልና የማያቋርጥ የራሱ የሆነ መጠይቅ አለው። በየጊዜው ለሰይጣንና ለሞቱት ሰዎች የሚደረግ ስጦታ ከባድና አሰልቺ ነበር (ለሞቱት ሰዎች ወይፈን እየታረደ ልመና ይቀርባል ፣ በመቃብሮቻቸው ላይ ማርና ወተት



የማፍሰስ ባህል ነበር።) ሰዎች ከዚህ ባህል ለመውጣት ይፈልጋሉ። ስለዚህ ስብከታችን በእንደዚያ ጭለማ ውስጥ ለነበሩት ሰዎች ትልቅ የምስራች ነበር።

## የጎሳ (የዘር) ሀይማኖተኞች

የጎሳ ሀይማኖተኞች ሀይማኖታቸው በዋናነት የጎሳ መሰረት ባላቸው ሰዎች የተወሰነ ነው።በዋጮ አካባቢ ያሉ ሰዎች በክርስቶስ ከማመናቸው በፊት የጎሳ ሀይማኖተኞች ነበሩ።

የህይወትን፣የሞትንና ከሞት በኋላም ስለሚሆነው ሁሉ የሚተረጉሙትና የሚቀበሉት በሲዳማ ሕዝብ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተያያዘ በመጣው እምነት ነው። አንዳንዶቹም ለስም ብቻ ያሉ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች የነበሩና በኦርቶዶክስ ሀይማኖት ስር ተጠምቀው በአንገታቸው ማህተብ (ክር) ያሰሩ ናቸው። ቢሆንም ህይወታቸው ያልተለወጠና በሰይጣን ፍርሀት የተሞላ ነበር።

አንዳንዶቹን የሙታን መንፈስ ይቆጣጠራቸዋል፣ያሰቃያቸዋልም። ጥቂቶቹ ከሰይጣን ፍርሀት ነጻ የሚወጡ እየመሰላቸው የእስልምናን ሀይማኖት ሰመከተል እየሞከሩ ነበር። ሙስሊሞች ሆነው ከነበሩት መካከል አንድ ቤተሰብ በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው ጠንካራ ክርስቲያኖች በመሆን በዋጮ ቤተክርስቲያን ብዙ ዓመት በጠንካራ አባልነት ኖረዋል።

## ፈውስ

በሲዳማ ውስጥ ከበሽታ ከመፈወስ ይልቅ ከሰይጣን ፍርሀት ነፃ የመውጣት ጉዳይ የበለጠ ትኩረት የሚሰጠው ነው። ክርስቲያኖች በሽታን በሁለት ዋና ዋና መንገዶች ይመለከቱታል። በመጀመሪያ ሕመሙ ከሰይጣን የመጣ ከሆነ በኢየሱስ ክርስቶስ ሲያምኑ ይፈወሳሉ። ይህ የተለመደ ሁኔታ ነው። በሚያምኑበት ጊዜ እንዲፀለይላቸው አጋጣሚ ያገኛሉ እና የህይወት ለውጥ ያስገኝላቸዋል።

በእርግጥ ከስጋዊ በሽታ ለመፈወስ ብዙ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ አያምኑም። እኔ ከስጋዊ በሽታ ትፈወሳላችሁ ብዬ አልሰብክም፣ሌሎችም ይሰብካሉ ብዬ አልገምትም።

## ተቃውሞ

በዋጮ የሚገኙ ክርስቲያኖች ተቃውሞ ምን እንደሆነ ብዙ አልተለማመዱም። አንዳንድ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ በማመናቸው የቅርብ ቤተሰቦቻቸው በጣም ይቆጣሉ፣ ምክንያቱም ለውቃቢው የሚቀርቡትን

መስዋዕቶች ሁሉ ስለሚያቋርጡ ውቃቢው ይቆጣናል ወይም ይቀጣናል ብለው ስለሚፈሩ ነው::

ህብረተሰቡ በሙሉ የእኔን ስብከት አይቃወምም፤ ለአዳዲስ አማኞችም ሆነ ለክርስቲያኖች ህብረት የማስተላልፈውን መንፈሳዊ መልዕክት ህብረተሰቡ አይቃወምም::

## እረኞች

ለመጀመሪያ አዳዲስ ክርስቲያኖችን የሚንከባከብና የሚጠብቅ ሰው አደራጃለሁ:: ያም እረኛ ይባላል:: ጊዜዬን የማሳልፈው ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወርኩ ወንጌልን በማሰራጨት ስለሆነ በሃላፊነት ቦታ እንዳልቆይና ፍላጉት እንዳይኖረኝ አድርጉኛል:: በማህበሩ ዕድገት ላይ የሚቀጥለው እርምጃ ሰዎችን መሾምና ለተለያዩ ማህበራት ሥራዎች ጊዜያዊ ሃላፊነት በመስጠት ለዚህ አልግሎት ብቁ የሆኑትን ሰዎች መምረጥ ነበር::

ሦስተኛው ደረጃ ብዙውን ጊዜ እረኛ የሚለውን ቃል ባንጠቀምም እረኞችን /ሽማግሌዎችን/ በየማህበራቱ እናስመርጣለን፤ በምርጫው ቀን ከአጠቃላይ ማህበር መሪዎች ሽማግሌ ለመሆን የሚመረጡ ሰዎች ማሟላት ስለሚገባቸው መስፈርቶች ለማብራራትና ለማስመረጥ በመካከላቸው ይገኛሉ::

የሚመረጡት ሰዎች ስም ዝርዝር ለቤተክርስቲያኑ አባሎች ይገለጣል:: ከዚያም ምዕመናኑ መምረጥ የሚፈልጉትን ሰው ይመርጣሉ:: ምርጫው ከመጀመሩ በፊት የሚመረጡት ሰዎች የዕውቀት ደረጃቸውና በህብረተሰቡ መካከል ስላላቸው መልካም ምስክርነት ለምዕመናኑ ማብራሪያ ይሰጣሉ::

## ገንዘብ

በየሳምንቱ እሁድ ለአምልኮት ስንሰበሰብ አራት ነገሮችን እንፈጽማለን:: ምንም ቁጥራችን ያነሰ ቢሆንም እንኳን መዘመር፣ መፀለይ፣ ቃሉን መስበክና ምፅዋትን መሰብሰብ የተለመዱ ናቸው:: ምፅዋትን ስንሰጥ ከስብከትና ከፀሎት እኩል አስፈላጊ መሆኑን እናምናለን::

አዳዲስ ክርስቲያኖች የእሁድን አምልኮት መሳተፍ እንደጀመሩ ምፅዋትና አሥራት መስጠት እንዲለማመዱ እናበረታታቸዋለን:: ለአሥራትም ከሰብል ምርታቸው በቆሎ፣ ቡናና ከብቶችን እንዲሁም ጥሬ ገንዘብን እንዲሰጡ እናበረታታለን::

ለሃይማኖታዊ ጉዳዩች የሚሰጡት ሁሉ ለምን እንደሚሰጡ ያውቃሉና አዲስ ሃሳብ አይሆንባቸውም:: ሁልጊዜ ከቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች አንዱ ገንዘብ ያዥ ሆኖ የሚመረጥ ሲሆን፤ ሁለተኛውም የተሰበሰበውን ገንዘብ



ወጪና ገቢውን ይመዘግባል፤ ምናልባት ስለዚሁ ጉዳይ ከተግባሩ መናገሩ ይቀልላል::

ማህበሩ በሚሰበስበው ገንዘብ ከሚያከናውናቸው ነገሮች አንዱ የትርፍ ጊዜ ወንጌላዊ መቅጠርና ለእርሱ መክፈል ነው:: ወንጌላዊው በየወሩ ጥቂት ገንዘብ ይከፈለዋል:: ለአጠቃላይ ማህበሩም የተወሰነ ገቢ ይደረግና ቀሪው ገንዘብ ለቤተክርስቲያን አስፈላጊ ጉዳዮች እንዲውል ይደረጋል::

ብዙውን ጊዜ የምፅዋት ገንዘብ ለድሆች ይሰጣል፣ ነገር ግን ጥሬ ገንዘብ ከመስጠት ይልቅ ምግብ ገዝቶ መስጠቱ ይመረጣል::

ከዚህ /ከዋርጮ/ ማህበር በየወሩ ገንዘብ ተቀብዬ አላውቅም:: እነርሱ ሊሰጡኝ ቢፈልጉ እንኳ የእኔ መቀበል ራሴን በራሴ እየረዳሁ መስበክ የሚለውን የግል መመሪያዬን መቃወምና መቃረን እንዳይሆንብኝ ገንዘብ አልቀበልም::

ይህ ልምድ መቼ እንደተስፋፋ ባላውቅም በየወሩ እሁድ የጌታን እራት /ቅዱስ ቁርባን/ እንወስዳለን፣ በዚያን ቀን የሚሰበሰበውን መባ አንዳንድ ጊዜ ለእኔ ይሰጡኝ ነበር::

ገንዘብን በዚሁ መንገድ መጠቀም መቼ እንደተጀመረ አላውቅም:: ምናልባት ከወላይታ ያመጣነው ባህልና ከሲዳማ የወጣ ባህል ተጣምሮ ሊሆን ይችላል::

## ልጆች

በሰሚናዊ ሲዳማ አገልግሎታችን ዓመታት ውስጥ እግዚአብሔር ስምንት ልጆች ሰጥቶናል:: የመጀመሪያ ልጃችን ራሔል በህፃንነቷ ሞታብናለች:: ቀጥሎም ጳውሎስና ሣራ ተወለዱ:: ከእነርሱ በኋላ የተወለደችዋም አስቴር በአራት ዓመቷ ታማ ሞታብናለች:: ተከታዮቹ አራት ልጆቻችን ሳሙኤል፣ ታደለች፣ ኃይለ የሱስና አማኑኤል ናቸው::

## የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት

በዋርጮ በማገለግልበት ጊዜ ሚስተር እስቲቨንስ በአለታ ወንዶ የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ለመክፈት ወሰኑ:: እኔም ሄጄ እንድገባ የፈለጉኝ ሲሆን ጊዜውም 1947 ዓ.ም ወደ ዋርጮ ከተዛወርኩ ከዓመት በኋላ ነበር::

በዚያን ጊዜ አብዛኛዎቹ የሲዳማ ተማሪዎች ሚስዮኑ የሚሰጣቸውን ዕርዳታ በማቆሙ ምክንያት ተቋርጠው ትምህርታቸውን ያቆሙበት ወቅት ነበር:: በመጨረሻም በዚያ መጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት የወላይታ ልጆች ብቻ

እንዲማሩ ሆነ:: እንደ እውነቱ ከሆነ የሲዳማ መሪዎች እኛ በወንዶ የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት መማራችንን አልወደዱትም::

የሲዳማ ቤተክርስቲያን መሪዎች ከሚሰዮኑ ገንዘብ የምናገኘውን መቃወም ብቻ ሳይሆን፣ ከሲዳማ ወደ ወላይታ እንድንገባ ነግረውናል:: የወላይታ ወንጌላውያን ሲዳማን ለቅቀው ወደ ወላይታ የገቡትም ያን ጊዜ ነበር:: በጊዜው የነበሩ የሲዳማ መሪዎች የወላይታን ወንጌላውያን አንፈልግም ብለውም በግልጽ አሳውቀዋል::

በአለታ ወንዶ የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ለሁለት ዓመት የቆየሁ ይመስለኛል:: ትምህርቴን አጠናቅቄ ከአለታ ወንዶ ወደ ለሜናዊ ሲዳማ የተመለስኩት በ1949 ዓ.ም ነበር::

በአለታ ወንዶ የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት በነበርኩ ጊዜ ወደ ዋጮ ለስብከት አገልግሎት በየሳምንቱ ዓርብ እሄድ የነበር ሲሆን፣ አልፎ አልፎም ወደ ሺሎ እሄድና አገለግል ነበር::

## አፋራራ

በአለታ ወንዶ የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት በነበርኩ ጊዜ በአፋራራ አካባቢ በስብከት አገልግሎት ተሳትፌአለሁ፤ በአፋራራ አካባቢ በዚያን ጊዜ ብዙ ክርስቲያኖች እንዳልነበሩ ይታወሰኛል::

አፋራራ በአጠቃላይ ለእኔ አዲስ አልነበረም:: በአርኬ ወንጌልን እሰብክ በነበረ ጊዜ በዚያም አካባቢ እዘዋወር ስለነበር አንዳንድ ሰዎችን አውቃለሁ:: በዋጮ ሌሎች ሰዎችም ይሰብኩ ነበር:: ከአርኬ የበለጠ በዋጮ መንፈሳዊ አገልግሎታችን የበለጠ አድጓል:: ሰዎች ፈጥነው በክርስቶስ ያምኑ ነበር፤ የጥምቀት ሥነሥርዓትም ሳይዘገይ ይካሄዳል:: የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎችም ወዲያው ይመረጡ ነበር::

በአፋራራ ማገልገል በጀመርኩ ጊዜ ከዋጮ ማህበር ጋር የጠበቀ የወዳጅነት ግንኙነት ነበረኝ:: ሚስተር እስቲቨንስ ወደ አለታ ወንዶ የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት በወሰዱኝ ጊዜ በሚስዮኑ ግቢ ውስጥ እንድንኖር አደረጉ:: ነገር ግን ትምህርታችንን ስንጨርስ ወደ ዋጮ ቤታችን ከመመለስ ይልቅ በአፋራራ መኖር ጀመርን::

አስቀድሜ ከኖርኩባቸውና ከሠራሁባቸው ሁለት ቦታዎች አፋራራ ለየት ያለ ነበር:: ለሃያ ዓመታት ያህል በአፋራራ ኖረናል:: አፋራራ ለሁሉም አቅጣጫ መካከለኛ ቦታ በመሆኑና ለመጓጓዣም ምቹ በመሆኑ ወደ ፈለግኩበት አካባቢ በመዘዋወር ወንጌልን ሳልሰማው ሕዝብ እሰብክ ነበር::



ወንጌላዊ ሆኜ የብላቴን ወንዝ ተሻግሬ ወደ ሲዳማ እንደገባሁ በአፋራራ ለሰባት ዓመት አገልግዬ ነበር:: መንፈስ ቅዱስ እየመራኝ በመዘዋወር የማደርገውን አገልግሎት በብቃት በመወጣት እስከ ሕይወቴ መጨረሻ አገለግላለሁ::

# ምዕራፍ አሥራ አንድ
# አፋራራ

በአሁኑ ጊዜ አፋራራ በአዋሣና በይርጋለም መካከል ከሰሜን ወደ ደቡብ በተዘረጋው አውራ ጎዳና ላይ ችምችም ያሉ ቤቶች ተሠርተውበት ያለ መንደር ነው::

ቤተሰቤና እኔ በዚህ ቦታ ለሃያ ዓመታት ያህል ኖረናል:: ያም ከ1948-1968 ዓ.ም ማለት ነው:: በነዚያ ሁለት አሥርት ዓመታት አፋራራ ለአገልግሎታችን መሠረታዊ ቤታችን ሆኖልናል::

## ወደ አፋራራ መዛወር

አፋራራ ከዋጮ በስተምስራቅ በእግር አምስት ሰዓት የሚያስኬድ ሲሆን፣ ከአለታ ወንዶ በስተሰሜን በእግር የሰባት ሰዓት መንገድ ነው:: ነገር ግን ወደ አለታ ወንዶ አዘውትሬ በእግሬ አልሄድም:: በ1950ዎቹ አካባቢ አውቶቢስ እናገኝ ነበር::

በአለታ ወንዶ ለሁለተኛ ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት በነበርኩበት ወቅት ሚስተር ምድልተን በመኪናቸው በየሳምንቱ ዓርብ ወደ አፋራራ ያደርሱንና እሁድ ከሰዓት በኋላ መጥተው መልሰው ወደ ወንዶ ይወስዱን ነበር::

በ1947 ዓ.ም በአለታ ወንዶ የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት በነበርኩ ጊዜ የአፋራራን አካባቢ እየጐበኘሁ ወንጌልን እሰብክላቸው ነበር:: በመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት በቆየሁባቸው ሁለት ዓመታት ቤተሰቤ በአለታ ወንዶ ሚስዮኑ ግቢ ይኖሩ ነበር:: ወንዶን ለቅቀን በወጣን ጊዜ ወደ ዋጮ ከመመለስ ይልቅ በአፋራራ ለመኖር ወሰንን:: አስቀድሜ አርኬ በነበርኩ ጊዜም የአፋራራን አካባቢ በየጊዜው እጐበኝና ቃሉን እሰብክ ስለነበር ለቦታው እንግዳ አልሆንኩም::

/ተዘዋዋሪ/ ወንጌላዊ ምናልባት በአንድ ቦታ ተወስኖ ለመኖር ይፈልጋል:: ምክንያቱም የሲዳማ እርሻ ሥራ ስለሚያስገድደው ነው:: ጥሩ ኑሮ ለመመሥረት ቡናና እንሰት መትከል ያስፈልጋል:: ሁለቱም ተክሎች ማለት እንሰት ለምግብነት የሚደርሰውና ቡና ፍሬ መስጠት የሚጀምረው ከተወሰኑ ዓመታት በኋላ በመሆኑ አንድ ቦታ መቆየት የግድ አስፈላጊ ይሆናል::

## የአሁን ሥራ ሁኔታ

ዛሬ በ1993 ዓ.ም አራት መቶ የሚሆኑ የተጉ አብያተ ክርስቲያናት በሰሜናዊ ሲዳማ ቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያን ሥር ይገኛሉ። አንዳንዶቹ በሚገባ የታወቁ ባይሆኑም አራት መቶ ማህበራት በየሳምንቱ እሁድ በየአካባቢያቸው ይሰበሰባሉ። በዚያ አካባቢ የቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያን ከብዙ ሃይማኖታዊ ድርጅቶች ብዙ ማህበራት ያሏትና የታወቀች ነች። ምናልባት በመቶዎች የሚቆጠሩ አብያተ ክርስቲያናት ከሌሎች ሃይማኖታዊ ድርጅቶች ጋር ተጣምረዋል። በሰሜናዊ ሲዳማ ዛሬ ቤተክርስቲያን ያልተመሠረተበት አካባቢ ብዙ አይደለም።

በሐዌላ አካባቢ ቤተክርስቲያኖች የሌሉበት አካባቢዎች ቢኖሩም፣ ወንጌላዊያኖች እየተላኩ ወንጌልን እየሰበኩ ነው። በሐዌላ በጣም ብዙ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ አምነዋል። ዛሬ በሐዌላና በማል*ጋ* ሰባት ቤተክርስቲያኖች አሉ። ከሰሜን ወደ ደቡብ የሚያቋርጠው አውራ ጐዳና በተሠራ ጊዜ የአውራ ጐዳናው ሠራተኞች ጊዜያዊ ሰፈር ወይም ካምፕ የነበረው ቱላ በሚባል ትንሽ ከተማ ውስጥ አንድ ቤተክርስቲያን አለ። የሲዳማ ቃለ ሕይወት ዛሬ በሰሜን ከአዋሳ ከተማ አልፎ በሚገኘው ጥቁር ውኃ ድረስ ደርሶ ተመሥርቷል።

በመጀመሪያ ወደ ሰሜናዊ ሲዳማ በመጣሁ ጊዜ ከአፋራራ በስተደቡብ በሚገኘው በሸበዲኖ ወረዳ ምንም ቤተክርስቲያን አልነበረም። በአሁኑ ጊዜ ግን ብዙ ቤተክርስቲያኖች ይገኛሉ።

ለምሳሌ ሺፋ በሚባል አካባቢ አራት የቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያኖች አሉ። እነርሱንም አንደኛ፣ ሁለተኛ ፣ ሦስተኛና አራተኛ ሺፋ ብለን ሰይመናል።

በሰሜናዊ ሲዳማ የቃለ ሕይወት ማህበራት በአራት ክፍለ ማህበራት ኅብረት ተብለው ተደራጅተዋል ። እነርሱም አርፌ፣ አፋራራ፣ ሃሊሌ፣ እና ጐርቤ ይባላሉ። ሁሉም ወደ አርባ ቤተክርስቲያኖች አሏቸው። ካለፈው ሁለት ዓመት ወዲህ የአርፌ አካባቢ ማህበራት ተደራጅተው ራሳቸውን በራሳቸው ለማስተዳደርና ለመታወቅ እየጣሩ ናቸው።

## የመጀመሪያው አማኝ

በአፋራራ አካባቢ ከመጀመሪያ አማኞች አንዱ ባላ ይባላል። እርሱ ከወላይታ የመጣ ሲሆን፣ በሲዳማ መኖር ከጀመረበት ጊዜ ሁሉ በሥራው ስኬታማ ሊሆን አልቻለም። ከአፋራራ ወደ አርኬ ተዛውሮ በቅርባችን ይኖር ነበር። በኋላም ከእኛ ጋር ወደ ዋጮ ተዛውሮ ሲኖር እዚያው ታሞ ሞቷል። እርሱ ከመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች አንዱ ቢሆንም ቤተክርስቲያን ለመመሥረት ግን እግዚአብሔር የተጠቀመበት ሰው አልነበረም።



## የቤተ ክርስቲያን አምድ /ምሰሶ/

በአፋራራ የመጀመሪያ ታላቅ ልምዶ ገና ትንሽ እንደቆየን አንድ ሽማግሌ ሞተው ታላቅ የቀብር ሥነሥርዓት ነበር። ምክንያቱም ሟቹ ሽማግሌ በወረዳው ሁሉ በብዙ ሰዎች የሚታወቁ ስለነበር ነው። በአካባቢው ያሉት ብዙ ሰዎች ለቀብሩና ስባት ቀን ለቆየው የለቅሶ ሥርዓት ተሰብስበው ነበር።

የሞቱት ሰው ክርስቲያን ባይሆኑም ከልጆቻቸው መካከል አንዳንዶቹ ክርስቲያኖች ነበሩ። በለቅሶው ቀናት ለተሰበሰበው ሕዝብ በተደጋጋሚ የእግዚአብሔርን ቃል ለመስበክ አጋጣሚ አግኝቻለሁ።

እስከዚያው ደረጃ ድረስ በአፋራራ አካባቢ ያሉት ሰዎች ቃሉን ቢሰሙም እንኳን በኢየሱስ ክርስቶስ ለማመን አልወሰኑም ነበር። የምናገረውን ያዳምጣሉ፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለተነገራቸው ቃል ይወያያሉ፣ ዳሩ ግን ለመወሰን አልተዘጋጁም ነበር።

አንድ ቀን አቶ ቱምቻ የሚባሉ ሽማግሌ ቆሙና ጥቂት እንደ መዝናናት ካሉ በኋላ በኢየሱስ ክርስቶስ ለማመን መፈለጋቸውን ገለጹ። ስለ እምነታቸውም መሰከሩ።

ነገር ግን በወቅቱ አቶ ቱምቻን በግል አልተገናኘሁአቸውም፤ የት አካባቢ እንደሚኖሩም አላወቅኩም ነበር። ጥቂት ሳምንቶች ካለፉ በኋላ ግን አገኘሁአቸው። በቤታቸውም ጥቂት ቀናት አሳለፍኩኝ። ያን ጊዜ ወንጌልን በስፋት አስተምሬ በቤታቸው ቤተክርስቲያን ተመሠረተች። የአቶ ቱምቻ በእምነታቸው መሰወጥ ወንጌልን በስፋት ለመስበክ በር ከፍቶልናል። ምክንያቱም ከእርሳቸው ቀጥለው ብዙ ወጣቶች በክርስቶስ ኢየሱስ ለማመን ችለዋልና።

ባራሣ የተባለው ሰው በዚያን ወቅት በክርስቶስ በማመን የታወቀ ወንጌላዊ ሆኗል። ቀጥለውም ቶርባ እና ኩማሎ የተባሉ ሌሎች ሰዎች በጌታ አመኑ። ኩማሎ በኢየሱስ ክርስቶስ ያመነው በ1950 ዓ.ም ይመስለኛል።

## አፋራራ እንደ ማዕከል

በአፋራራ መኖሪያዬን ከመሠረትኩ በኋላ እግዚአብሔር በዚያ ገጠር አካባቢ ከአንድ መቶ በላይ የቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያን ማህበር ለመመሥረት አስችሎኛል። ሰራሴ ማስታወስ የምሻውና አንባቢዎቼም እንዲገነዘቡልኝ የምወደው ቤተክርስቲያንን የሚመሠርቱት ክርስቲያኖች እንጂ ሚስዮናውያን፣ ወንጌላውያንና የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ብቻ አይደሉም። የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎችና ወንጌላውያን ግን ክርስቲያኖችን በቃሉ የማሳደግና በመንፈሳዊ እግራቸው እንዲቆሙ የማድረግ ሃላፊነት አለባቸው።

እግዚአብሔር የተለያዩ ሠራተኞችን ለሥራው መርጧል፣ሾሟልም። አዳዲስ ቤተክርስቲያኖች፣ የአካባቢው ሰዎች የሥራ ትጋት ውጤቶች ናቸው። አቶ ኩማሎ በሰሜናዊ ሲዳማ ለቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያን እንደ አባት ሆኗል። በክርስቶስ ካመነበት ጊዜ ጀምሮ ጥብቅ ወዳጆች ብቻ ሳንሆን ወንድማማቾችም ሆነናል።

የአፋራራ አካባቢ ማህበር ፀሎት ቤት ከመሥራቱ በፊት በኩማሎ ቤት ይሰበሰብ ነበር። ከብዙ ጊዜ ቆይታ በኋላ ብዙ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ አምነዋል። በመብዛታቸውም ምክንያት ሰፊ ፀሎት ቤት ለመሥራት ፈልገዋል።

በቅርብ ጊዜም ስፋቱ አሥር ሜትር ጐኑ አርባ ሜትር የሆነ የቆርቆሮ ክዳን ቤት ለመሥራት በቅተዋል። ለዚህ ቤተክርስቲያን ዕድገት ምክንያት የሆነው አቶ ቶርባ ቶሞጮ ነው። እርሱም ከማህበሩ የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኝ ወንጌላዊ ሲሆን፣ ምን ጊዜም ደከምኩ ሳይል ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወረ ወንጌልን ለመስበክ በመቻሉ በእርሱም ታላቅ አገልግሎት ብዙ ሕዝብ በኢየሱስ ክርስቶስ ሊያምን ችሏል።

## ቋሚ እርሻ

በሲዳማ እርሻ ማለት ላሞች፣ እንሰትና ቡና ነው። ከብቶቻችንን ወደምንዛወርበት አካባቢ ይዘን መሄድ እንችላለን። ነገር ግን ቡናና እንሰት ለማምረት የተወሰኑ ዓመታት መጠበቅ ያስፈልጋል።

በዋጮ ከተቀመጥኩና ከተለማመድኩ በኋላ በሲዳማ እርሻ ስመጀመር ቡናና እንሰት ለመትከል ቋሚ ቦታ ማግኘት አስፈለገኝ። በአፋራራ ቋሚ ሆኜ ለመኖር የፈለግኩበትም ምክንያት ስለዚህ ነው።

በአርፌ በነበርኩ ጊዜ እንዲሁም በዋጮና በአለታ ወንዶ የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት በነበርኩ ጊዜ ያረባሁአቸው በርካታ ላሞች ስለነበሩኝ ከመካከላቸው አንድ ወይም ሁለት ላሞች ሸጬ መሬት ለመግዛት ወሰንኩ። ከብቶቼን በመሸጥ ሦስት መቶ ብር አገኘሁና መሬት ገዛሁበት። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በአፋራራ ኗሪ ሆኜ እንሰትና ቡና በመትከል ባለንብረት ሆኜ መኖር ጀመርኩ።

## ዓለሙ ዳንቦዌ

ዓለሙ ዳንቦዌ በአፋራራ ከመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች አንዱ ነው። በ1953 ዓ.ም በክርስቶስ ኢየሱስ ባመነ ጊዜ መቶ በመቶ የተለወጠ ሲሆን፣ በአካባቢው ቤተክርስቲያን አምድ ይሆኑ ዘንድ እግዚአብሔር ከመረጣቸው ሰዎች አንዱ ነው።



በኢየሱስ ክርስቶስ እንዳመነ ወንጌልን መስበክ የጀመረ ሲሆን ከአርባ ዓመት በላይ በወንጌል ስብከት አሳልፏል። በቤተክርስቲያን፣ በማህበራት ስብሰባዎችና ሰዎችን በሚያገኛቸው ቦታዎች ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል ያስተምራል።

ዓለሙ በጣም ትጉህና ታታሪ ተማሪ በመሆን በቀለም ት/ቤትና በመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት በአለታ ወንዶ በቂ ዕውቀት ለማካበት ችሏል። በ1969 ዓ.ም የሰሜናዊ ሲዳማ ማህበር የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት በከፈተ ጊዜ ዓለሙ አስተማሪ ሆኖ እስከ ዛሬ በመሥራት ላይ ነው።

በመንፈሳዊ ነገሮች ሁሉ ባለው ትጋትና ሰዎችን በቀላሉ ለመግባባት ባለው ችሎታ በአብዮታዊ ለውጥ ወቅት ተዘግቶብን የነበረውን የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤታችንን በ1972 ዓ.ም ለማስከፈት የቻለና ከፍተኛ ሚና የተጫወተ ታላቅ አገልጋይ ነው።

ዓለሙን ላለፉት አርባ ዓመታት እግዚአብሔር እንዴት እንደተጠቀመው ሳስብ ጥልቅ የሆነ እርካታ ይሰማኛል። የእግዚአብሔር ቃል ዘር በሕይወቱ ከመዘራቱ የተነሳ ተዘዋዋሪ ወንጌላዊ ሊሆን ችሏል። መቼ እንደሆነ ባላስታውስም ወንጌልን ከሰበኩላቸው ብዙዎች መካከል ብቸኛ ታታሪና ትጉህ ሰባኪ መሆኑን በተግባር አስመስክሯል።

## ማጠቃለያ

በአፋራራ በኖርኩባቸው ሃያ ዓመታት ውስጥ የትና መቼ ወንጌልን እንደሰበክሁ ለመግለጽ ያዳግተኛል፤ ምንም ማስታወሻ በጽሑፍ አልያዝም። ብዙውን ጊዜ ሁኔታዎች ተከናውነው ዓመታት ካለፉ በኋላ ካልሆነ በስተቀር የሥራን ዕድገት ወዲያው ለመመልከት አይቻልም።

ብዙ ተግባሮች የተጠላለፉ በመሆናቸው ለመለያየት የማይቻል ነው። በዘፈቀደ የተሠራ ጥቂት ምሳሌ ልስጣችሁና ከዚያም በራስ አገዝ ወንጌላዊነት አገልግሎቴ ስምንት የተደባለቁ መመሪያዎቼን እዘረዝራለሁ።

## ምድረ ገነት

ወንጌልን ለመስበክ ከተዘዋወርኩባቸው ቦታዎች አንዱና የትንሹ ህብረተሰብ አካባቢ ምድረ ገነት ይባላል። ይህ ቦታ ከአፋራራ ጥቂት ኪሎ ሜትር ርቆ ከሰሜን ወደ ደቡብ በተዘረጋው አውራ ጐዳና በስተምሥራቅ በኩል ያለ መንደር ነው። በመጀመሪያ ማንም ወደዚያ እንድሄድ አላሳሰበኝም ወይም አልወሰደኝም። አንድ ቀን ከቤት ወጣሁና የምድረ ገነትን መንደር ለመጐብኘትና የሚሰማኝ ካገኘሁም ቃሉን ለመስበክ ሄድኩኝ። በመጀመሪያ ጉብኝቴ ሁለት ሰዎች በክርስቶስ አምነዋል። ወዲያውም በትንሽ ቤት መሰብሰብ

ጀመርን። መጻፍና ማንበብ የሚችሉ ጥቂት ሰዎች ስለነበሩ መጽሐፍ ቅዱስን እያነበቡ በህብረት መፀለይ ጀመሩ።

የእግዚአብሔር መንፈስ እንደረዳቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚያነብቡትን ክፍል አንዱ ለአንዱ በማስረዳት ይማማሩ ጀመር። እኔም እሁድ እሁድ እየመጡ በአፋራራ እንዲሰበሰቡና እንዲያመልኩ አበረታቸዋለሁ።

አንዳንድ ክርስቲያኖች አማርኛ መፃፍና ማንበብ አይችሉም ነበር። የመጽሐፍ ቅዱስ ባለቤት መሆንና ማንበብን መማር ከፍተኛ ጥቅሞች ናቸው። ስለዚህ እኔ ፊደል በማስተማር ጊዜዬን አሳልፋለሁ። አንዳንዴም ሌሎች እንዲያስተምሩ ሁኔታዎችን አመቻቻለሁ።

በተከታታይ ሳምንቶች እየተመላለስኩ ከመንፈሳዊነቴም በላይ መደበኛ ስብሰባዎችን በየሳምንቱ ሐሙስ እየተሰበሰቡ እንዲፀልዩ አበረታታሁአቸው። የሐሙስ ጧት የፀሎት ስብሰባ ሁልጊዜ ለእሁድ ስብሰባ መሠረት የሚጥል ነው።

በዚያን ወራት ሌሎች ክርስቲያኖችና እኔ በአካባቢው ስብከታችንን እንቀጥላለን። በእነርሱ በኩል አዲስ ቤተክርስቲያን ለመትከል መፈለጋቸው በግልጽ ይታይ ነበር። እና በአንድ ወቅት አሥራ ስድስት ሰዎች በአንድ ጊዜ በኢየሱስ ክርስቶስ አምነዋል።

አዳዲስ ክርስቲያኖች በየሳምንቱ ሐሙስ ጧት ተሰባስበ የመፀለይን ልምድ ከቀሰሙ በኋላ ከሌሎች ምዕመናን ጋር እንዲተዋወቁ ይደረግና የእሁድን ስብሰባ መካፈል ይጀምራሉ። ደን ጊዜ ወደ ሌላ አካባቢ ስለምዘዋወር ተከታታይ ጉብኝት ማድረጌን እገታለሁ። እኔ አስተምሬ ወደ ጌታ የመለስኳቸውን ክርስቲያኖች ሌላው ሃይማኖታዊ ድርጅት ይህ የእኛ ከተማ ስለሆነ ለምዕመኖቻችን ት/ቤት እየሠራንላቸው በመሆኑ እናንተም ወደ እኛ ተመለሱ በማለት ይሰብካቸው ጀመር። መወሰኑ የእኔ ጉዳይ ባይሆንም እነዚያ ያስተማርኳቸው ክርስቲያኖች በሃሳባቸው ተነድተው ወደሌላ ኃይማኖት በመግባታቸው መንፈሴ ሳያዝን አልቀረም።

## ሰዎች እንዴት ያምናሉ?

ሰዎች የሚያምኑበት ምክንያት ፍፁም የማይለወጠው የእግዚአብሔር ቃል ተሰብኮላቸው ስለሰሙ ነው። ስብከት ለእኔ ብቻ ሳይሆን ለሚያምኑት ሁሉ ከፍተኛ ጥቅም ነበረው። ላላመኑት የሚተላለፍ ስብከት በቤተክርስቲያን ውስጥ ሳይሆን በህብረተስቡ መካከል ነው።

የማያምኑት ሰዎች ቃሉን ለመስማት ወደ ቤተክርስቲያን እንዲመጡ አይጠበቁም። ነገር ግን ወደእሉብት ህብረተሰብ መካከል በመሄድ የእውነትን



ወንጌል የማሰማት ግዴታ አለብን። አዳዲስ ክርስቲያኖች ወደ ቤተክርስቲያን ሄደው በእሁድ ስብሰባ ይሳተፋሉ። ምዕመናኑም አዳዲሶቹን እንዲተዋወቁአቸው ይደረጋል። ነገር ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑት ሁሉም በራሳቸው ውሳኔ እንጂ በግፊት መሆን የለበትም።

እኔና አብረውኝ የሚያገለግሉት የት መስበክ እንደምንችል ወይም የት መስበክ እንደሚገባን እናውቃለን ፤ የቦታ ርቀትም አያግደንም። አንዳንድ ጊዜ ረዥም መንገድ እንጓዛለን። አንዳንዴም አጭር መንገድ እንሄዳለን።

ለአገልግሎት ብዙውን ጊዜ እኔ ለብቻዬ እዘዋወር ነበር። ቶርባና ዓለሙ አብረውኝ በሚሄዱበት ጊዜ ደስታዬ እጥፍ ድርብ ይሆናል። ከአፋራራ ቅን አገልጋይ ባራሳ የሚባለው ወንጌላዊ ነው። እርሱም በብዙ የተለያዩ ቦታዎች ሰብኳል።

በሰሜናዊ ሲዳማ ብዙ ቤተክርስቲያኖች እንዲመሠረቱ ምክንያት የሆኑት ክርስቲያኖች ንግዳቸውንና የግል ጉዳዮቻቸውን ከማስቀደም ይልቅ ቃሉን ለመስበክ ስለሚሰማሩና በየሳምንቱ እሁድ የሚሰበስቡትን የምዕዋት ገንዘብ ለሚያገለግሉት ወገኖች ስለሚደጉሙ ነው። ይህን በማድረጋቸው ገንዘባችንን ስለምንከፍል አንሰብክም ብለው አያስቡም። ነገር ግን የሚቀጥሩትን ወንጌላዊ በአካባቢያችን ህብረተሰብ መካከል ክርስቲያኖች ባለመኖራቸው ሄደህ እንድትሰብክ እንፈልጋለን ላንተ የሚያስፈልግህን እኛ እናሟላልሃለን ማለትን ያስቀድማሉ።

## አንደኛ ሞሮቾ

ሲመሠረት ተባባሪ የሆንኩት ሌላኛው ቤተክርስቲያን አንደኛ ሞሮቾ የሚባለው ነው። ሞሮቾም ከአፋራራ በስተሰሜን ደቡብ በዋናው አውራ ጐዳና ዳር ያለው መንደር ነው።

ሌቃ የሚባለው ሰው በሞሮቾ አጠገብ የሚኖርና በሰይጣን እሥራት ውስጥ የሚገኝ ነበር። አንድና ሁለት ጊዜ ተገናኝቼው ስለነበር መስክርኩለትና ወደ አፋራራ መጥቶ በኢየሱስ ክርስቶስ አመነ። ሚስቱ ሙታንን የሚያናግር መንፈስ አለኝ የምትል ነበረች። በቤታቸው ለየት ባለ ክፍል ውስጥ ሆና የሰይጣን መንፈሷን ታስተናግድ ነበር። ለብዙ ጊዜ ወንጌልን ብሰብክላትም የሰይጣን መንፈስ ለረዥም ጊዜ ሲታገላት ኖራለች።

ባለቤቷ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመኑ ይሞታል ወይም አንዳች ክፉ ነገር ይደርስበታል ብላ ስትጠብቅ ከዕለት ወደ ዕለት በመልካም ሕይወት መመላለሱን ስትመለከት ቆይታ በመጨረሻ እርሷም በኢየሱስ ክርስቶስ ለማመን ወሰነች።

ብዙዎቻችን በአካባቢው ወንጌልን ስለምንሰብክ አያሌ ሰዎች በክርስቶስ በማመናቸው ትልቅ ማህበር ተመሠረተ:: በሞሮቾ አካባቢ የሚገኙት ምዕመናን ሁለተኛ ሞሮቾ ብለው በመሰየም ሌላ ቤተክርስቲያን ስመመሥረት በሂደት ላይ ናቸው::

ይህ ቦታ ስምንቱን መመሪያዎቼን በተግባር ላይ እንዳውልና አገልግሎቴን መልክ እንዳስይዝ ምሳሌ ሆኖልኛል::

## ስምንት የተዋሃዱ አካሎች

በአፋራራ በምሠራበት ጊዜ በሥራዬ ላይ ስምንት የተዋሃዱ አካሎችን ማየት ጀምሬአለሁ:: አንዳንድ ጊዜ አንዱ ከአንዱ የተቀራረበ ክፍተት ቢኖረውም፣ ሁሉም የማይለያዩ ናቸው:: ስለ እያንዳንዱ ብነግራችሁ ከ1950-1970 ዓ.ም ድረስ የተከናወነውንና ቅደም ተከተሉን የያዘውን ሥዕል ለማቅረብ አለመቻሌ ለምን እንደሆነ ትረዳላችሁ::

## 1. እርምጃ /ግብገ

ከሁለቱ በአንደኛው መንገድ አዲስ ሥራ ተጀምሯል:: እኔ ወደ አንድ ቦታ እሄድና ሰዎችን ሳገኝ አነጋግራለሁ ወይም አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ወደ ስፈራቸው ሄጄ ወንጌልን እንድሰብክላቸው ይጋብዙኛል::

የመጀመሪያው ግንኙነቴ ከአዲስ ሰው ጋር ይሆናል:: ሰውየው ክርስቲያን ሊሆንም ላይሆንም ይችላል:: ነገር ግን በአካባቢው ወንጌል እንዲሰበክ የሚፈልግ ይሆናል::

የእግዚአብሔርን ቃል ለመዝራት ወደ አንድ ቦታ በምሄድበት ጊዜ «እዚህ ቦታ ቤተክርስቲያን እመሠርታለሁ» ብዬ ተናግሬ አላውቅም:: እንደዚህ ዓይነት ሃሳብ በአዕምሮዬ አይመጣም:: የእኔ ከፍተኛው ፍላጐት ወንጌልን ለሰዎች መስበክና የእውነትን ቃል የሰሙ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ ሲያምኑ መርካት ነው:: እኔ ብሰብክና ሰዎች በክርስቶስ ቢያምኑ ቤተክርስቲያንን እንደሚመሠርቱ አውቅ ነበር:: ላለፉት አርባ ዓመታት የሠራሁት በዚሁ መንገድ ነው:: በአንድ ጊዜ በተለያዩ ሥፍራዎች ለአገልግሎት እሳተፋለሁ:: የሚታወሰኝ አንድ ጊዜ ወንጌልን በለኩ፣ በአምቦንሳ፣ በሃዌላ፣ በዳዬቾና በሾሸ እሰብክ ነበር:: ነገር ግን በአራትና በአምስት ቦታዎች ማህበራት ሲመሠረቱ ባሉበት ከሰዎች ጋር ቅብብሎሽ የመፍጠር ሁኔታ አልነበረም::

ቤተክርስቲያን እንደተመሠረተች ከአካባቢው ምዕመናን መካከል መንፈሳዊ ሥራውን በሃላፊነት ለመሥራት ያበረታታና ያስተዋውቅ ነበር:: በአንድ ወቅት አቦንሳ በሚባል ቦታ የሚኖረው ሻላሞ የሚባለው ሰው ወደ ቤቴ መጣ:: ወደ አቦንሳ አብሬው እንድሄድና ለአካባቢው ነዋሪዎች ወንጌልን እንድሰብክ



ጠየቀኝ:: እርሱ የመስበክ ችሎታው አነስተኛ በመሆኑ ነበር እኔን አብሬው እንድሄድ የጠየቀኝ::

ለመጀመሪያ እንደደረስኩ ለአራት ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ስሰብክ አራቱም ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ አመኑ:: እሁድ ዕለት ለአምልኮት ወደሚቀርባቸው ቤተክርስቲያን እንዲሄዱ አደረግን::

ሻላሞም ወደ ቤቱ እንዲመጡና በየሳምንቱ በሚካሄደው የፀሎት ህብረት እንዲሳተፉ አበረታታቸው:: እነርሱም ወዲያው በደስታ መሳተፍ ጀመሩ:: ሻላሞ መጽሐፍ ቅዱሱን ሲያነብ ያገኘውን ፍሬ ሃሳብ ያካፍላቸው ነበር:: ለተወሰኑ ወራቶች በየሳምንቱ ሐሙስ እየተሰበሰቡ ከቆዩ በኋላ በስፈሩ የእሁድ አምልኮትን እንዲጀምሩ ማህበሩ ፈቀደላቸው:: በሃዌላም ቤተክርስቲያን የተጀመረው በተመሳሳይ መንገድ ነው:: ጥቂት ሰዎች ወደ ገጠሩ አካባቢ ሄደን እንድሰብክ ወሰዱኝ:: ላገኘን ሰው ሁሉ ወንጌልን መስበክ ጀመርን፣ የተወሰኑ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ አመኑ::

ስለ ደዬቾ ቤተክርስቲያን ብናነሣ፣ በለኩ ከተማ የሚማር ተማሪ ወደ እኔ መጥቶ በዚያ አካባቢ ሄጄ ወንጌልን እንድሰብክ ጠየቀኝ:: አንዳንድ ጊዜ ተጋብዤ እሄዳለሁ፣ ሌላ ጊዜ ራሴን ጋብዤ እሄዳለሁ:: የግል መመሪያዬ ግን ሰብቻዬ እየተዟዟርኩ ወንጌልን መስማት የሚያስፈልጋቸውን ሰዎች መቃኘትና ማስተማር ነው::

## 2. ስብከት

በሰሜናዊ ሲዳማ አዳዲስ ቤተክርስቲያኖች የተመሠረቱት በክሊኒክ፣ በት/ቤቶች፣ በውኃ ቁፋሮ ወይም ማንበብንና መጻፍን በማስተማር ሂደት አይደለም:: እነዚህ ነገሮች የመጡት ከወደኋላ ነው:: ህብረተሰቡ በሙሉ እነዚህን ነገሮች ይፈልጋል:: ወዲያውም በክርስቶስ ያመኑት ህብረት ይፈጥራሉ::

በሰሜናዊ ሲዳማ የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት የተመሠረቱት በወንጌል ስብከት ብቻ ነው:: ከመጀመሪያው ጀምሬ ደጋግሜ እንደተናገርኩት አዳዲስ ክርስቲያኖች ሁሉም ሰባኪዎች ናቸው:: በተከታታይ ወንጌልን ለመስበክ ብቃት የሌላቸው መስሎ ከታያቸው ሌላ የሚረዳቸውን ሰው በመውሰድ አብረው በመተጋገዝ ይሠራሉ::

የሰዎችን ትኩረት የሚስብ ዓይነት መልዕክት የሚጠብቅ ማንም አልነበረም:: እግዚአብሔር ቃሉን በምልክቶችና በድንቆች ያጸናል:: በክርስቶስ ያመኑት ሰዎች ሕይወት ይለወጣል:: በኢየሱስ ማመንም አዲስ ሕይወት የሚያስገኝ መሆኑን ሰዎች ይገነዘባሉ::

ከሰይጣን እሥራትና ከመንፈሱ በመፈታት ነፃነትን ይጐናፀፋሉ:: በሰሜናዊ ሲዳማ ስናገለግል በቆየንባቸው ረዥም ዓመታት በዚሁ ሁኔታ በማስተማር የድንቅና የተአምር ሥራውን ለማየት ችለናል::

## 3. ከሙያ ወደ ንስሐ

በትክክል አንዳንድ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ ለማመን ሲወስኑ የመንፈስ ቅዱስ ሰውጥን ባይለማመዱም እኔን በፍፁም አያስጨንቀኝም:: የማልጨነቅበት ምክንያት የሰዎችን ሕይወት የሚሰውጠው የእግዚአብሔር ቃል እንጂ የእኔ ስላልሆነ ነው:: በእግዚአብሔር ቃል መሠረት በኢየሱስ ክርስቶስ ካመኑ እንደሚሰወጡ አውቃለሁ::

አንዳንድ ሰዎች ከእምነታቸው በኋላ መንፈሳዊ ለውጥ ካላሳዩ ምንም ቢናገሩና ልብ የሚነካ ፀሎት ቢፀልዩ እንኳን ከልባቸው አምነዋል ለማለት አይቻልም::ከልባቸው ባለማመናቸው የሕይወት ለውጥ ሲያጡ ምን ዓይነት ስም እንደሚሰጣቸው ይጨንቀኛል:: እንደዚያ ዓይነት ሕይወት ከልብ ያልሆነና ታማኝነት የጐደለው ነው:: በሌላ መልኩ ሰዎች ከኃጢአታቸው ነፃ ለመውጣት ይሻሉ:: በሙሉ ልብ በኢየሱስ ክርስቶስ ካላመኑ መንፈስ ቅዱስ ሕይወታቸውን አይለውጥም:: ምክንያቱም በፍፁም ሙተው የሚገባቸውን የኃጢአት ዓይነት ሰውረው ስለሚያስቀምጡ ነው:: በ2ኛ ቆሮ. 5÷17 ላይ «ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፣ ሁሉም አዲስ ሆኖአል» የሚለው ለእኔ በጣም ግልጽ ነው:: ውሳኔ ማለት ውጫዊና የሰዎች ምኞት ማመልከቻ ነው:: እንደዚያ ዓይነት ውሳኔ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ይሁን ወይም የሰዎች መገፋፋት እኔ ላውቅ አልችልም:: ለእኔ አስፈላጊው ነገር ንስሐ ነው፤ የባህርይና የቃል ገለጻ ማለትም «ሕይወቴ ተለውጧልና አዲስ ፍጥረት ነኝ» የሚለውን ቃል ከሰውየው ከራሱ አንደበት ስሰማ በትክክል መንፈስ ቅዱስ እየሠራ ነው ማለት ነው እናም በጣም እደሰታለሁ:: በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሕይወታቸው የተሰወጡ ሰዎች የቤተክርስቲያን መሥራቾች ይሆናሉ:: የእኔ ተግባር ለሰዎች ወንጌልን መስበክ ስለሆነ የመለወጡን ሥራ ለመንፈስ ቅዱስ እተዋለሁ::

## 4. ማበረታታት

የቤተክርስቲያን መሥራቾችንና በአካባቢው ምንም ቤተክርስቲያን ባልተመሠረተበት አካባቢ አዳዲስ አማኞችን ማበረታታት ለእኔ ወንጌልን ከመስበክ ለይቼ የማላየው አገልግሎት ነው::

ለብዙ ስዓቶች በእግሬ እየተመላለስኩ ህይወቱ ከተሰወጠ ሰው ወይም ሴት ጋር ተቀምጬ ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምራቸዋለሁ:: እያንዳንዱ ሰው መበረታታት ይፈልጋል:: የአማርኛ ፊደል ማንበብ የማይችሉ ከሆነ በተቻለኝ



ፍጥነት ሳስተምራቸው የምችለውን አደርጋለሁ:: አንዳንድ በዕድሜያቸው የገፉ ወንዶችና ሴቶች አማርኛ የማይናገሩት ፊደል መማር አይፈልጉም:: በአንዳንድ አካባቢ ግን የሚማሩ አዛውንቶች አሉ::

አብሬአቸው ተቀምጬ መጽሐፍ ቅዱስ አነብላቸዋለሁ፤ ከምንባቡም ማብራሪያ እየሰጠሁ አስረዳቸዋለሁ:: በመታዘዝ ልብ መጽሐፍ ቅዱሳችንን ካጠናን መንፈስ ቅዱስ ያስተምረናል:: በዚሁ በማያደናቅፍ ዘዴ እያስተማርን መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን እንመሰክራለን:: ዋናው አስፈላጊው ትምህርት የወንጌልን መሠረት ለመማር መፈለግ ነው:: ያንን መልዕክት ለሌሎቹ ለማስተማር እንዲችሉ እፈልጋለሁ:: «ብዙ ሰዎች የመሰከሩለትን ከእኔም የሰማኸውን ሌሎችን ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ» (2 ጢሞ. 2÷2):: ይህ ጥቅስ ተግባራዊ መሆን አለበት:: በአካባቢው ህብረተሰብ መካከል ላላመኑት ወንጌልን መስበክ ውጤታማ ሲሆን የሚችለው የተሰበከሉትና ያመነው ሰው እውነተኛ የተለወጠ ሕይወት መኖር ሲጀምር ነው:: ስለዚሁ በከፍተኛ ደረጃ እንነጋገርበታለን:: አዳዲስ ክርስቲያኖች ማቃናት የሚገባቸውና ሁልጊዜም ለመተግበር የሚፈልጉት ነገር ይኖራል:: ነገር ግን ምንጊዜም መንፈስ ቅዱስ አስተማሪያቸውና መሪያቸው ነው::

## ማዋቀር /ማቀላቀል/

ክርስቲያኖች ከእሁድ አገልግሎት ጋር ተያያዥነት ከሌላቸውና በየሳምንቱ እሁድ ከክርስቲያኖች ጋር ህብረት የሌላቸው ከሆነ ምን ተብለው ይታሰባሉ? በየእሁድ ተሰብስቦ መፀለይ የእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ለውጥ ማረጋገጫ ነው ብዬ አምናለሁ:: በብዙ መንገዶች አዳዲስ አማኞች ከነባር ክርስቲያኖች ጋር ሲሰበሰቡ ሰይጣንን በመካዳቸው የህብረተሰቡን አስተሳሰብ ለመስወጥ ይችላሉ:: በክርስቶስ ማመን ግልጽ የሆነ ማህበራዊ እይታ ነው:: እሁድ መቼም ምን ጊዜም ለአምልኮ ለመሰባሰብ የተለየ ቀናችን ነው::

የተለየ መንፈሳዊ ጥቅም እንዲያገኝ አዲሱን ክርስቲያን ወደ ማህበራት ህብረትና ስብሰባ እወስደዋለሁ:: አዲስ ክርስቲያን የማህበሩ አባል ከሆነ ማህበሩ ወደሚሰበሰብበት ቦታ ሁሉ እየተወከለ ሊሄድ ይችላል:: ብዙውን ጊዜ በግሌ የአስተዳደር ችግሮችን ከአካባቢዬ ማህበራት ተለማምጄአለሁ:: ምክንያቱም ሁላችንም የጋራ ግብ አለን እንጂ የግል አጀንዳ አልነበረንም:: የእኔ ድርሻ የትም ቦታ በማንኛውም ጊዜ የምችለውን ማድረግ ነው::

## 6. ጥምቀት

በወላይታም ይሁን በሲዳማ ጥምቀት ማለት ወደ ክርስቲያኖች ህብረተስብ መግቢያ መንገድ ነው:: ጥምቀት ከውጪ የሚታይና ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ሲያምን ከዓለማውያን ህብረተሰቡ የመለየት ምልክት ነው:: በእኔ እምነት

ጥምቀት በግል የሚፈፀም ሥርዓት ብቻ ሳይሆን፣ ያመነ ህብረተሰብም ጥቅሙን ተረድቶ የሚሳተፍበት ነው፡፡ አንድ ሰው ክርስቲያን ከሆነ በኋላ የማህበሩ አባል ይሆናል፡፡ የማህበሩም መሪዎች ስለ ጥምቀት ነገሮችን ስለሚያመቻቹ እኔን አይመለከተኝም፡፡ ነገር ግን የማህበሩ አባሎች ከመጠመቃቸው በፊት በእምነታቸው ስለማይጠነክሩ መጠመቅ እንደሚገባቸው አጠንክሬ አበረታታቸዋለሁ፡፡

ከወላይታ ወደ ሲዳማ ካመጣነው ባህላችን አንዱ ቅዱስ ቁርባን ነው፡፡ በክርስቶስ አምነው ያልተጠመቁ ሰዎች የጌታን እራት /ቅዱስ ቁርባንን/ አይወስዱም፡፡ ያልተጠመቀ ሰው በቤተክርስቲያን ውስጥ በምንም አገልግሎት አይሳተፍም፡፡ አያዘምርም፣ በፀሎት ፕሮግራም አይመራም፣ አይሰብክም፡፡ እረኛና መሪም ሊሆን አይችልም፡፡ አንድ አማኝ ለመጠመቅ ፍቃደኛ ካልሆነ በድርብ ሕይወት መመላለሱን ወይም ዓለማዊነቱን ሙሉ በሙሉ አለመተውን ያመለክታል ማለት ነው፡፡

በጥንት ጊዜ እያንዳንዱ ምዕመን ይጠመቅና በአዲሱ አካባቢው የአገልግሎት ተግባር ያከናውን ነበር፡፡ በመጨረሻም በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ ሲያምኑ ውጤቱ ግልጽ እየሆነ ይመጣል፡፡

# 7. እረኞች/ሽማግሌዎች

የመጀመሪያ ሃላፊነቴ የነበረው አዳዲስ ክርስቲያኖች አንዱ ሌላውን እንዲንከባከብ ማበረታታትና ስለ አዲሱ መንፈሳዊ ሕይወታቸው ጉዳይ ማወያየት ነው፡፡ የእኔ ተሳትፎ ከየማህበሩ ጋር በሚኖረኝ ቅርበት ይወሰናል፡፡ አዲስ ማህበር ለመመሥረት ሃላፊነት ካለብኝ እረኞችና ሽማግሌዎች የሚሆኑትን ሰዎች እመርጣለሁ፣ ያም ለአገልግሎት የሙከራ ጊዜያቸው ይሆናል፡፡

ከመጀመሪያው ጥምቀት በኋላ ማህበሩ ለቤተክርስቲያኑ አገልግሎት አራት ሰዎችን የቤተክርስቲያን እረኞች ወይም ሽማግሌዎች አድርጐ ይሾማል፡፡ ምንም እንኳን ማህበሩ አነስተኛ ቢሆንም፣ የሽማግሌዎችና የእረኞች ጠቀሜታ በትንሹ አይገመትም፡፡ የእኔ ጠቀሜታና ድርሻ ምን እንደሆነ ስለማውቅ ሌሎቹም የእኔን አዲስ ማህበር ለመመሥረት ያለኝን የተለየ የአገልግሎት ሥፍራ ለማወቅ ችለዋል፡፡ የአስተዳደር ድርሻዬ ልክ ጳውሎስ በቆሮንቶስ እንደነበረው ድርሻ ዓይነት ነው፡፡ ለሰዎች ከእግዚአብሔር ቃል አስተምራቸዋለሁ፤ ቀጥሎም የራሳቸውን ውሳኔ እንዲወስኑና እንዲተገብሩ እጠይቃቸዋለሁ፡፡

እኔ በማህበሩ የገንዘብ ጉዳይ እጄን አላስገባም፡፡ በመጀመሪያው ስብሰባችን የተሰበሰበውን የመጀመሪያ የምፅዋት ገንዘብ ከነበሩት ሰዎች አንዱ ይይዝ



ነበር፡፡ አስቀድሜ ከመጽሐፍ ቅዱስ ስለ ስጦታና ስለ ታማኝነት አስተምሬአቸዋለሁ፡፡ ለገንዘብ ትኩረት መስጠት ማለት ለአንድ ማህበር በቀላል የሚታይ አይደለም፡፡

ለብዙ ዓመታት ብዙ ወንጌላውያን በአዳዲስ ቤተክርስቲያኖች አስተዳደርና ገንዘብ ጉዳይ እየገቡ በመፈተናቸው የመጨረሻው ውጤታቸው መልካም ሳይሆን ቀርቷል፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ቦታዎች ላይ ጠለቅ ብሎ መግባት እግዚአብሔር የሰጠውን ታላቅ አገልግሎት ሊያጉድፍ ይችላል፡፡

# 8. መላቀቅ

መላቀቅ በቀስታ የሚሆን ነገር ነው ፤ከአዲስ ማህበር ጋር የመሆን ጉዳይ አይደለም፤ ነገር ግን በአንድ ቦታ የመገኘት ጉዳይ ነው፡፡ ነገሮች ሁሉ በጊዜው እየተስተካከሉ ሲሄዱ ማህበራቱ አብሬአቸው እንድቆይላቸው እምብዛም አይፈልጉም፣ ሊያጡኝም አይፈልጉም፡፡ ያልደረስኩባቸውና መድረስ የሚገባኝ ብዙ ቦታዎች ስላሉ ሄጄ ወንጌልን ማሰራጨት በጣም ያስደስተኛል፡፡ ወደኋላ የመዘግየት ጉዳይ ከባድ አልነበረም፡፡ በማንኛውም ጊዜ ነገሮች ያልተጠበቁ ሆነው ቢገኙና የቤተክርስቲያን ዕድገት ፈጣን ባይሆን ፍፁም አልጨነቅም፡፡ ምክንያቱም ቃሉን የማድረሱ ሃላፊነት የእኔና የማህበሩ ሲሆን፣ የሚያሳድገው እግዚአብሔር ስለሆነ ነው፡፡

እነዚህ ስምንቱ የአገልግሎት ውህዶች ቤተክርስቲያንን በመመሥረት ሂደት ልዩ ሚና እንድጫወትና መንፈስ ቅዱስ ወደ መራኝ ቦታ ሁሉ በነፃነት እንድመላለስ አስችሎኛል፡፡ በእያንዳንዱ ስምንቱ ውህዶች ያለኝ ድርሻ በጥቂቱ የተወሰነ ሲሆን፣ ለሠራሁት ሁሉ ያለኝ ዕውቅና ጥቂት ነው፡፡ ከማህበራት መሪዎች የማገኘው ምሥጋና ለእኔ አስፈላጊዬ አይደለም፡፡ እግዚአብሔር የፈለገውን ሁሉ ሠርቻለሁ እና ያ ለእኔ በቂዬ ነው፡፡ «እንዲሁ እናንተ ደግሞ የታዘዛችሁትን ሁሉ ባደረጋችሁ ጊዜ፡- የማንጠቅም ባሪያዎች ነን፣ ልናደርገው የሚገባንን አድርገናል በሉ» (ሉቃስ 17፥10)፡፡

## የሥራ ባልደረቦቼ

በአፋራራ አካባቢ ብዙ ጊዜያቸውንና ችሎታቸውን በተግባር ላይ ያዋሉ ወንጌልን ለማስማትና ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ እንዲያምኑ ከፍተኛ ተልዕኮአቸውን የተወጡ ሰዎች ነበሩ፡፡

ባራሳ ዮታ፣ ስምአን ዮታ፣ ኩማሎና ቶርባ የተባሉት ታዋቂ አገልጋዮች ናቸው፡፡ ቶርባና ዓለሙ ሁልጊዜ ከእኔ ጋር ስለብከት ይወጣሉ፡፡ ከሁሉቱም ወይም ከሁለት ከአንዳቸው ጋር ለአገልግሎት ስወጣ ሁልጊዜ እደሰታለሁ፡፡

ለሁላችንም ስብከት ማለት ዝም ብሎ መናገር ማለት አይደለም። ነገር ግን እኛ አዲስ ማህበር ለመመሥረት ከሚተጉት ቡድኖች መካከል ነን። ከላይ ስማቸውን የጠቀስኳቸውና ብዙ ሌሎችም ውድ ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን አዳዲስ ማህበራትን ለመመሥረት ተጠቅመዋል።

አዳዲስ ክርስቲያኖች እርሻ ለማረስና ቤት ለመሥራት የሌሎቹን ዕርዳታ ይፈልጋሉ ወይ? አዎን ይፈልጋሉ። እኛም እየሄድን እናግዛቸዋለን። ዛፍ በመቁረጥ፣ ጠርብ በመፍለጥ፣ ሣር በማጨድና የፀሎት ቤቱን በማልበስ ለቀናት ሳናቋርጥ እናግዛቸዋለን።

አዳዲስ ክርስቲያኖች የተዋሃዱበት አዲስ የክርስቲያን ህብረተሰብ በቃል ሳይሆን በተግባር የሚተጋገዝ መሆኑን በግልጽ እናሳያቸዋለን። ሰፊ ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን ያዋሉት ሰዎች ለአካባቢያቸው ህብረተሰብ በጣም አስፈላጊዎች መሆናቸውን በተግባር ያስመሰክራሉ። በሲዳማ ባህል ሰሀብታም ሰዎች ማንኛውንም ሥራ ማገዝ የተለመደ ሲሆን ከሁሉም ጋር በመግባባት መንፈስ ይሰራሉ።

## ራስን ማነሳሳት

ብቻዬን በመሥራቴ ምቾት ይሰማኛል። ይህም ማለት የራሴን ነገር ለመፈፀም በመፈለግ አይደለም። ነገር ግን ሁሉ ነገር ለሌሎቹ ተስማሚና ምቹ ሆኖላቸው ከእኔ ጋር እስኪወጡ ድረስ መጠበቁ መሄድ ወደሚገባኝ እንዳልሄድ ስለሚያደርገኝ ነው። ብዙውን ጊዜ የት እንደምሄድ ለማንም ሳልናገር እሄዳለሁ። አንዳንድ ጊዜ የማህበሩ መሪዎች አዲስ ማህበር ተመስርቶ ለሽማግሌዎች ምርጫ እስኪጠሩ ድረስ መቼ እንደተመሠረተ እንኳን አያውቁም።

የዚህ ምሳሌ ሲሆን የሚችለው በለኩ ቤተክርስቲያን የሆነው ነው። የለኩ ቤተክርስቲያን ተመሥርታ በደንብ እስክትቆም ድረስ የማህበራቱ የበላይ መሪዎች አላወቁም ነበር። በየሳምንቱ እሁድ በትንሿ ክፍል ውስጥ በስውር እንሰበሰብ ነበር። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሁለት ሌሎች ሰዎች በክርስቶስ አመኑና ተጨመሩ። እኛም እንዘምራለን፣ በህብረት እየፀለይን ቃሉንም እናጠና ነበር። አነስተኛ ጐጆ ሠርተን በሳር ከከደንን በኋላ እዚያ መሰብሰብ ጀመርን። ይህን ሁሉ የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ብቻ ሰምተዋል። ይህ ሁሉ ሲሆን እኔ በግሌ ያከናወንኩት አለመሆኑ መታወቅ አለበት።

## እሁድ

በአጠቃላይ እሁድ ቀን ውጪ ላሉት ሰዎች ሄጄ አልሰብክም። ብዙውን ጊዜ አዳዲስ ወደተመሠረቱት ቤተክርስቲያኖች በመሄድ በማስተማር እረዳቸዋለሁ እንጂ አልሰብክም።



አንዳንድ ጊዜ ከቤት ወጥቼ ሁለት ወይም ሦስት ቀን ውጪ እያገለገልኩ አሳልፋለሁ፣ ግን ብዙውን ጊዜ ያ አስፈላጊ አልነበረም። ልጆቼ እንኳን ለስብከት ከእኔ ጋር በፍፁም አይወጡም። በእርግጥ የቤተክርስቲያን አባሎች እንጂ ሰባኪዎች አይደሉም።

## ተቃውሞ

ሰው አስተምሮኝ ይሁን ወይም ራሴ ከመጽሐፍ ቅዱስ ተምሬ እንደሆን ባላውቅም ሰይጣን የሚያጠቃ ጠላት ስለመሆኑ ቅንጣት ያህል ጥርጣሬ አልነበረኝም። ሰይጣንን በመቃወም ትግል አልገጥምም፣ ነገር ግን እንዳያታልለኝና ከወጥመዱ እንዳያስገባኝ እጠነቀቃለሁ። ሰይጣንንማ እግዚአብሔር አሸንፎታል።

ሰዎች የእውነትን ወንጌል እንዳያሰራጩ ሰይጣን ለመከላከል ይሞክራል። ነገር ግን ከሰይጣን ኃይል አገኘን በሚሉ ሰዎች ሕይወት ታላላቅ ነገሮች ተከስተዋል። እግዚአብሔር የበላይ ነኝ በሚሉ ሰዎች ሕይወት ውስጥ ይሰራ ነበር። ማለትም በሰይጣን ኃይል ታስረው የነበሩትን ለውጦ የእርሱ አገልጋዮች እንዲሆኑ ሲያደርግ አይተናል።

ብዙ ቃልቻዎች ሞተዋል፣ ነገር ግን የሚሞቱት እኛ ስለረገምናቸውና እንዲሞቱም ስለ ጸለይን አይደለም፣ በተፈጥሮ ግዴታና በአጋጣሚ ነው። ወንጌልን እየሰሙ ስመታዘዝ ግን እምቢተኞች ነበሩ፣ ታዲያ በኢየሱስ ክርስቶስ ሳያምኑ ይሞታሉ። ቃልቻ ሞተ ተብሎ ሲሰማ እኔ ምንም አያስደንቀኝም። እግዚአብሔር ግን አንድ ልዩ ነገር እንደሚሠራ እጠብቅ ነበር።

ብዙ ቃልቻዎች በኢየሱስ ክርስቶስ አምነዋል። ስለ ሰይጣን ተቃውሞ ብዙ ጊዜ የማስበው አልነበረም። እንዲያውም ከሲዳማ ይልቅ በካናዳ ስለ ሰይጣን ተቃውሞ ብዙ ልምድ አግኝቻለሁ። በእርግጥ አንድ ነገር አውቃለሁ። አጋንንት የእግዚአብሔርን ቃል ይፈራሉ። የእግዚአብሔር ቃል ሰይጣን ሊቋቋመው የማይችል ኃይል አለው።

በአንድ አካባቢ አዳዲስ አማኞችን የሚያስቸግር ቃልቻ ነበር። ክርስቲያኖቹም ምን እናድርግ? ብለው ጠየቁኝ። እኔም መልሼ፣ «ፀልዩ፣ ቃሉን ስበኩ፣» አልኳቸው። ምክሬንም ተቀበሉኝና ለቃልቻው ቃሉን መስበክ ቀጠሉ። ሆኖም ግን በጌታ ለማመን አልፈለገም። አንድ ቀን በጣም ታመመና ክርስቲያኖችን አስጠርቶ ለማመን እንደሚፈልግ ነገራቸው፣ ነገር ግን ወዲያው ሞተ።

ሌላው ቃልቻ ምክር የሚቀበል ነበር። ብዙውን ጊዜ በሀብታሞች ቤት ይቆያል። ከሁለት ዓመት በፊት ወንጌል ልሰብክለት ፈልጌ የሚያመች

አጋጣሚ እፈልግ ነበር:: አንድ ቀን ሽክሬና አጃቢዎቹ በቤታችን ቡና እየጠጣን በነበርን ሰዓት በደጃፋችን ያልፉ ነበር:: እኛም አቁመነው ወደ ቤት እንዲገባና ቡና እንዲጠጣ ጋበዝነው:: ለመጀመሪያ ጊዜ ግትር ብሎ ለመግባት ባይፈልግም ትንሽ ቆይቶ ገባ:: ወደ ቤት እንዲገባ ለምን እንደጋበዝነው በልቡ ያውቃል:: ስለ ስብከታችን ከተሰያዩ ሰዎች የሰማ ሲሆን፣ ከእምነታቸውም የተነሳ የብዙ ሰዎች ሕይወት መለወጡንም ያውቃል:: እርሱ በሚያልፍበት ጊዜ የሰፈር ልጆች ሳይቀሩ ስለማይወዱት ይደበቁታል::

በኢየሱስ ክርስቶስ ለምን አታምንም? አሁን ከምትኖርበት ፍርሃት ነፃ መውጣት ትችላለህ:: ጌታ ኢየሱስ ሲያድንህና ሕይወትህን ሊለውጥ ይፈልጋል ብዬ ነገርኩት፣ ፍፁም ሊሰማኝ አልፈለገም፣ እንዲያውም ትንሽ መቆጣት ጀመረ:: ምርጫው ያንተ ነው፣ ፍርድ እንደሆነ የማይቀር ነው:: በኢየሱስ ክርስቶስ ብታምን አይፈረድብህም ብዬ ነገርኩት:: ስብከቴን በሰፊው ስቀጥል፣ ቤትህን ትቼልህ እሄዳለሁ፣ ቡናችሁንም አልጠጣም ብሎኝ ወዲያው ቆመና ወደ በሩ መራመድ ጀመረ:: አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔር ፍርድ ሳትሞት ይመጣብሃል፣ በኢየሱስ አናምንም ያሉ እጅግ ብዙ ሰዎች በሞት ተቀስፈዋል ብዬ ስነግረው የበለጠ ተቆጣ:: ጉጃሞ ብሎኝ ከቤቴ ወጣ በሲዳሚኛ ጉጃሞ ማለት ፈልፈላ ማለት ሲሆን፣ ያን ጊዜ ያ የስድብ ቃል ምን ማለት እንደሆነ አልገባኝም ነበር::

ጥቂት እርምጃዎችን እንደሄደ ቆመ:: ከአጃቢዎቹ ጋር ትንሽ ከተነጋገረ በኋላ ወደ ቤቴ አጠገብ ተመልሶ መጥቶ በሄዱበት ዱካ ላይ ምልክት አደረገ:: በእርሱ አስተሳሰብ በእኛ ላይ እርግማንን መስደዱ ነበር:: በቤታችን፣ በእርሻችንና በከብቶቻችን ላይ መቅሰፍት እንዲወርድብን ማድረጉ ነበር::

ሰዎች ያንን መዓት ለማውረድ ምንም ኃይል እንደሌላቸው ስለማምን ድርጊቱን ሁሉ በቸልታ አየሁት:: ከአሥራ አምስት ቀን በኋላ ግን ያ ቃልቻ በድንገተኛ ሕመም ሞተ::

ሌላውን ቃልቻ የጐበኘሁት ታሞ በአልጋው ላይ በነበረ ጊዜ ነበር:: ሄጄ ቃሉን እንድሰብክለትና እንድፀልይለት ፈቅዶ ጋበዘኝ :: እርሱ ሥልጣንና ተደማጭነት ስለነበረው ከህብረተሰቡ ብዙዎች እየቀረቡ ያማክሩት ነበር:: ነገር ግን ወንጌልን ከሰበክሁለትና ከፀለይኩለት በኋላ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለማመን ፈቃደኛ አልሆነም ነበር:: ከጥቂት ቀናት በኋላ እርሱም ሞተ::

በእነዚያ ሃያዎቹ ዓመታት ማለትም ከ1950-1970 ዓ.ም ድረስ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ብዙ ተቃውሞ አልደረሰብንም ነበር:: ነገር ግን አንዳንድ ካህናት ወይም ቄሶች የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ስለምንጠቀም ያላግጡብን ነበር:: ቢሆንም ቃሉን እንዳንሰብክ ሊያግዱን አልሞከሩም:: ዳኞቹ



የክርስቲያኖችን መልካም ምስክርነት ስለሚያውቁ ከዓለማውያን የሚሰነዘረውን ተቃውሞ አይቀበሉትም::

ክርስቲያኖች ወደ ፍርድ ቤት በሚሄዱበት ጊዜ አንዳንዴ የሚከስተው ዳኞቹ ወደ ውጪ አውጥተዋቸው ያለባቸውን ችግር ወደ ቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች እንዲያቀርቡ መክረው ችግሩን እዚያው ተወያይተው እንዲፈቱ ይልኳቸዋል::

## የከተማው ስብከት

በእነዚህ ሃያ ዓመታት በከተማው ውስጥ አልሰበክሁም:: እግዚአብሔር ወንጌልን እሰብክ ዘንድ የጠራኝ ቦታ ባለመሆኑ ነው እንጂ በከተማ መስበክን ተቃውሜ አልነበረም:: እኔ ካመንኩበት ጊዜ ጀምሮ ከቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያን ውጪ ስብኬ አላውቅም::

እንዲሁም በማህበራት ጉባኤ በኮንፈራንስ ንግግር አድርጌ አላውቅም፣ እግዚአብሔር ትልቅ ሙያ እንድሠራ ሰጥቶኛል፤ ሌሎች ከሚሠሩት የእኔ ግን የተለየ ነው:: እግዚአብሔር እንዲሠሩ የፈለጋቸው ሰዎች ሲሠሩ ሳይ ደስ ይለኛል:: እኔም በበኩሌ እግዚአብሔር የጠራኝን ሥራ እንድሠራ ፍቀዱልኝ እላቸዋለሁ፣ ሌላ ስመሥራት ምንም ፍላጐት የለኝም::

## በአብዮታዊ ለውጥ ወቅት

በአብዮታዊ ለውጥ ወቅት ከ1966-1983 ዓ.ም ድረስ ወንጌልን ለመስበክ ብዙ አጋጣሚዎች ነበሩኝ:: ከትልቅ ቡድን ጋር ለመሥራት አልሳተፍም ነበር:: ነገር ግን በአካባቢው እየተዘዋወርኩ መስበክን እመርጣለሁ:: ታዲያ በመጀመሪያዎቹ ዓመታት ታስሬ አላውቅም ወይም ወንጌልን እንዳልሰብክና አዳዲስ ክርስቲያኖችን ለማበረታታት መሰናክል የሆነብኝ አልነበረም:: በብዙዎቹ ላይ ሥቃይ እንደደረሰባቸው አውቃለሁ:: ለእኔ ግን ምንም ክፉ ነገር አልደረሰብኝም ነበር::

በመጨረሻም በአፋራራ ትልቅ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ተመሠረተ:: ስሙም ገብረ ክርስቶስ ይባላል:: በአንድ አጋጣሚ የመንግሥት ባለሥልጣኖች በቤተክርስቲያናቸው በነበረው ስብሰባ ምግብ እንድናቀርብ አዘዙን፣ ሳንወስድላቸው ስንቀርም ብዙ ችግር አድርሰውብናል::

ሁላችሁም እንደምታዩት ከኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ጋር ያለን ግንኙነት ሰላማዊ ሊሆን የማይችልበት ምክንያት ብዙ ነው:: በርግጥ በጋራ የምናከናውነው ነገር የለም:: ትምህርታቸውንና መንፈሳዊ አኗኗራቸውን አንደግፍም:: እኛ የምናደርገውንም እነርሱ አይወዱም:: በመካከላችን የአይጥና ድመት ባህርይ ይታይብን ነበር::